# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

**8ኛ ክፍል**



# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

### የተማሪ መጽሐፍ

# 8ኛ ክፍል


**ፀሀፊዎች**

መላኩ ጽጌ

ትጃኒ ምትኩ

**አርታኢ**

ግሩም ጥበቡ

ከበደ በቀለ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ እና ምስል ገላፃ**

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014 ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው፡፡ የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም፡፡

የስዕሎችን የቅጂ መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ


ምዕራፍ አንድ የስራ ላይ ስነምግባር................................1

ምዕራፍ ሁለት ባህላዊ ቅርስ....................................17

ምዕራፍ ሶስት ሰብአዊ እሴቶች..................................32

ምዕራፍ አራት አጭር ልቦለድ....................................45

ምዕራፍ አምስት የህዝብ ብዛት..................................62

ምዕራፍ ስድስት በረሃማነት......................................80

ምዕራፍ ሰባት የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ.......................95

ምዕራፍ ስምንት ሰላም..........................................108

ምዕራፍ ዘጠኝ የአየር ንብረት..................................122

ምዕራፍ አስር ተውኔት..........................................133

# መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" በሚል ትኩረት በመስጠት አዲስ ስርዓተ ትምህርት ቀርጾ አቅርቧል፡፡ በዚህ መሠረት በሥርዓተትምህርቱ ታይቶ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምር ተደርጓል፡፡ ከምርምሩ የተገኙ አቅጣጫዎች የተማሪዎቹን ደረጃ አለመመጠን፣ የትምህርቱ አንኳር ጽንሰሀሳቦች ግልጽ አለመሆን፣ ከይዘቱ መታጨቅ የተነሳ ለዓመቱ ከተመደበለት ክፍለጊዜ ጋር አለመመጣጠን እና ከተጓዳኝ ሥርዓተትምህርቶች አማራጭ ግብዓቶችን አለመጠቀም ናቸው፡፡ ስለሆነም የአፍመፍቻ ቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል፣ በአውድ የተደገፈ ለማድረግ፣ እና በመማር ላይ የተመሰረተ ትምህርታዊ ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ስርዓተትምህርቱ ተቀርጿል፡፡

ስርዓተትምህርቱን መሠረት በማድረግ የትምህርት መሣሪያዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንዱ በመሆኑ ይህ አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሓፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሊዘጋጅ ችሏል፡፡ መጽሓፉም ተማሪዎች ቢያንስ መጎናጸፍ ያለባቸውን ብቃት (Minimum Learning Competency)፣ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶችን፣ ተግባቦታዊ የመማር ዘዴን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት በቀድሞው የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ይሞላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

# መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ አስር ምዕራፎች አሉት፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ በስሩ ስድስት ንዑስ የትምህርት ክፍሎችን አካቷል፡፡ እነዚህም ትምህርት ክፍል አንድ ማዳመጥ፣ ትምህርት ክፍል ሁለት መናገር፣ ትምህርት ክፍል ሶስት ማንበብ፣ ትምህርት ክፍል አራት መናገር፣ ትምህርት ክፍል አምስት ቃላት እና ትምህርት ክፍል ስድስት ሰዋስው ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል በመርሃ ትምህርቱ በተደለደለው መሰረት በክፍለጊዜ ተከፋፍሎ የቀረበ ስሆን በስሩ መመሪያዎች፣ ትዕዛዛት፣ የመልመጃዎች፣ ተግባራት አካቷል፡፡ ከዚህ አኳያ የቋንቋ ክህሎች የተደራጁት በቅድመ ተግባር፣ በጊዜ ተግባር እና በድህረ ተግባር ሂደታዊ አቀራረብ ነው፡፡ የቋንቋ የዕውቀት ዘርፎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ማቅረቢያ ዘዴን ተከትሏል፡፡ በዚህ መሰረት የዚህ መማሪያ መጽሐፍ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# የስራ ላይ ስነምግባር

## የሚጠበቁ ውጤቶች

### ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- በጥሞና አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ፤
- የእንግዳ አቀባበል ስርዓትን በሚና ጨዋታ ታንጸባርቃላችሁ፤
- አንብባችሁ የስራ ላይ ስነምግባር ጽንሰሀሳብን ታብራራላችሁ፤
- ከጽሁፍ ውስጥ የስራ ላይ ስነምግባር ማሳያዎችን ታመለክታላችሁ፤
- የጽሁፍን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ታነባላችሁ፤
- በተለያዩ አውዶች ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፤
- አዳዲስ ሀሳቦችን በማሰስ አንቀጽ ትፅፋላችሁ፤
- የአረፍተነገር መዋቅሮችን ለይታችሁ ትጠቀማላችሁ።

### ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ይዘት የማዳመጥ ክሂላችሁን ለማዳበር የሚረዱ መልመጃዎችና ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም መምህራችሁ በሚመሯችሁና በትዕዛዛቱ መሰረት በትኩረት በማዳመጥ መልመጃዎቹንና ተግባራቱን በተገቢው መንገድ ስሩ።

# መከባበር

**ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ወደማዳመጥ ተግባሩ ከመግባታችሁ በፊት በጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ።**

1. መከባበር ምንድን ነው?
2. መከባበር ለሰው ልጆች ምን ምን ጠቀሜታ አለው?
3. ታናሽ እና ታላቅ በቤተሰብ ውስጥ እንዴት ይከባበራሉ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች እያዳመጣችሁት መልሱ።**

1. የሰው ልጅ_____እና_____ያውቃል።
2. የሰው ልጅ ለመከበር _______ ማክበር አለበት።
3. ግጭቶች እንዳይፈጠሩ ለማድረግ______እና የጋራ የሆነ_____ማስቀመጥ ያሻል።
4. መከባበር ከ_______ይጀምራል።

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት አድርጋችሁ በጽሁፍ መልሱ።**

1. የሰው ልጆች ተከባብረው በጋራ ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ ስፍራዎችን ዘርዝሩ።
2. በጋራ መጠቀሚያ ስፍራዎች ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለማስቀረት የሚረዱ የመፍትሔ ሀሳቦችን አቅርቡ።
3. በክፍል ውስጥ እርስበርስ እንዴት እንደምትከባበሩ አብራሩ።

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ከዚህ በታች የቀረበውን ተግባር መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ትዕዛዝ መሰረት በንቃት አከናውኑ።

### ተግባር አንድ

ወደ ቤተሰባችሁ እንግዳ ሲመጣ አክብራችሁ የምትቀበሉበትንና የምታስተናግዱበትን ሁኔታ በጥንድ አስቀድማችሁ በመለማመድ በሚና ጫወታ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በመተወን አሳዩ።

ክፍለጊዜ፡ ሶስት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ከዚህ በታች የቀረቡት ምንባብ እና መልመጃዎች የማንበብ ክሂላችሁን ለማዳበር የሚያግዙ ናቸው። በመሆኑም ጽሁፍን በትኩረት በማንበብ የቀረቡትን መልመጃዎች ስሩ።

### የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ‹‹ስነምግባር›› ማለት ምን ማለት ነው?
2. ሰዎች ስራ ሲሰሩ ምን ምን የስራ ላይ ስነምግባሮችን መከተል የሚገባቸው ይመስላችኋል?

# የስራ ላይ ስነምግባር

ሰዎች በሚሰሩት ስራ ደስተኛና ስኬታማ ሆነው እንዲገኙ ጠንካራ የስራ ላይ ስነምግባር ባለቤት ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል። ሁሉም የስራ መስኮች የውስጥ አሰራራቸውን በተመለከተ ተግባሪዎቻቸው እንዲኖራቸው የሚሿቸው የየራሳቸው የስራ ላይ ስነምግባሮች አሏቸው። በተለያዩ የስራ ቦታዎች በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ የስራ ላይ ስነምግባሮች አሉ። ከነዚህ መካከልም ዋነኞቹ መልካም ስነምግባር፣ ውጤታማነት፣ መተባበር፣ ታማኝነት እና ታታሪነት ናቸው።

የመልካም ስነምግባር ባለቤት የሆኑ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በስራቸው ላይም መልካም ባህሪን **የተቀዳጁ** ሆነው የሚገኙ ናቸው። የመልካም ስነምግባር ባለቤት የሆኑ ሰዎች ስራቸውን አሸንፌው በአግባቡ የሚሰሩ ሲሆን ያለውን ጫና ሌሎች እንዲሸከሙላቸው የማይፈልጉ ናቸው። ከዚህም በላይ መልካም ስነምግባር ያላቸው ሰዎች እምነት የሚጣልባቸውና ቀናነትን የተላበሱ ናቸው። የመልካም ስነምግባር ባለቤቶች እነዚህን መለያዎች ከፍ ያለ ብቃት የተላበሱ ሰራተኞች የሚጎናጸፏቸው ናቸው ብለው ያምናሉ፤ ስለሆነም ሁልጊዜም ሀቀኞችና መልካም አሳቢዎች ሆነው ይገኛሉ። ባለ መልካም ስነምግባር ሰራተኞች እነዚህን አወንታዊ **መለያዎች** በዕለት ተዕለት ውሏቸው ተግብረው ስለሚገኙም ከሌሎች ሰራተኞች በቀላሉ ተለይተው ይታወቃሉ።

መልካም ስነምግባርን የተላበሱ ሰራተኞች ሌላኛው መገለጫቸው ስራቸውን ሁልጊዜም በቅልጥፍና ስለሚከውኑ በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ መሆናቸው ነው። በዚህም የስራ ላይ ስነምግባርን ከማይከተሉ ሰራተኞች ይልቅ በራካታ ስራዎችን በተወሰኑ ጊዜያት አጠናቅቀው ይገኛሉ፤

የጀመሩትን እስኪጨርሱም **ወለም** **ዘለም** አይሉም፤ በአጠቃላይ ስራ አይወዘፍባቸውም። ይህ በከፍተኛ ደረጃ የሚመዘገብ ውጤታማነታቸው የሚመነጨውም ጠንካራ ሰራተኛ ሆኖ መገኘትን ሁልጊዜም እንደመርህ ስለሚከተሉት ነው። ይበልጥ ጠንካራ በሆኑ ቁጥር ለተቋማቸው ይበልጥ አስፈላጊ እየሆኑ እንደሚመጡም ያምናሉ።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

**ተማሪዎች እዚህ ላይ ማንበባችሁን ገታ አድርጉና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. ከላይ በቀረቡት አንቀጾች የተዳሰሱት የስራ ላይ ስነምግባሮች ምን ምን ናቸው?
2. በርካታ ስራቸውን በተወሰነ ጊዜ አጠናቅቀው ይገኛሉ የተባሉት እነማን ናቸው?
3. ጥሩ የስራ ላይ ስነምግባር የተላበሱ ሰዎች ሁልጊዜም ሀቀኞችና መልካም አሳቢዎች ሆነው የሚገኙት ለምንድን ነው?

ከውጤታማነት በተጨማሪ ከሌሎች ጋር ተባብሮ መስራት በስራ አለም ውስጥ እጅግ ጠቃሚው ጉዳይ ነው። ጥሩ የስራ ላይ ስነምግባርን የተላበሱ ሰራተኞች ደግሞ **ከባልደረቦች** ጋር ተስማምቶ በትብብር መስራትን በደንብ የሚያውቁበት ናቸው። ከሌሎች ጋር እየተናበቡ መስራት የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ስለሚረዱም በእነሱና በባልደረቦቻቸው መካከል መልካም ግንኙነትን በዘላቂነት ለመመስረትና ተባብሮ ለመስራት **ሳይታክቱ** ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። የጥሩ የስራ ላይ ስነምግባር ባለቤቶች ለስራቸው ታማኝና መታዘዝን እንደእሴት የሚቆጥሩ በመሆናቸው አብረዋቸው እንዲሰሩ የተመደቡት ሰዎች **ልግመኛ** ቢሆኑባቸው እንኳ ይህንን ባህሪያቸውን ተቋቁመው በትብብር የሚሰራበትን አውድ መፍጠር ይችሉበታል።

በሌላ በኩል የጥሩ ስራ ላይ ስነምግባር ባለቤቶች ተአማኒነትን ገንዘባቸው ያደረጉ ናቸው። ተአማኒነት የጥሩ ስራ ላይ ስነምግባር አንደኛውና ዋነኛው አካል ነው። የጥሩ ስራ ላይ ስነምግባር ባለቤቶች አንድን ነገር እናደርጋለን ብለው ካሉ ያንን ነገር በቃላቸው መሰረት ይከውኑታል። አንድን ነገር በጊዜው ማጠናቀቅን **እንደ እሴት** ስለያዙትም እፈጽመዋለሁ ያሉትን ነገር የቱንም ያህል አድካሚ ቢሆንባቸውም ባሉበት ጊዜ አጠናቅቀው ዝግጁ ያደርጋሉ። ጠንካራ የስራ ላይ ስነምግባርን የተላበሱ ሰራተኞች በአሰሪዎቻቸው እምነት የሚጣልባቸው መሆናቸውን ስለሚያውቁም ሁልጊዜም ተግባሮቻቸውን በወጉ **ለመከወን** ዝግጁነት ያላቸውና ታማኝነትን የተላበሱ ይሆናሉ።

በስራ ላይ ታታሪ ሆኖ መገኘት ሌላኛው የጥሩ ስራ ላይ ስነምግባር መገለጫ ነው። **ታታሪነት** ወይም ለያዙት ስራ መሰጠት ምንም ያህል አድካሚ ቢሆን አንድን ለመፈጸም የተያዘን ስራ አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ሳይፈጽሙ አለማቋረጥን ይመለከታል። ይህ የታታሪነት አቅም ጠናካራ የሆኑ ሰራተኞች የያዙትን ስራ አጥብቀው እንዲይዙና በየጊዜው የስራ ቦታ እየቀያየሩ **እንዳይባዝኑ** አቅም ይፈጥርላቸዋል። ስራ ወዳዶች መሆናቸውንና ተነሳሽነታቸውን አጉልተው ለማሳየትም ከተለመዱት የስራ ሰዓታት ውጪ ጭምርም ተግተው ስራቸውን የሚከውኑ ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የስራ ላይ ስነምግባሮች በሙሉ ተገቢ የሚባሉ ስነምግባሮች በመሆናቸው ሁሉም ሰው ሊጠቀምባቸውና የህይወት መርህ በማድረግ ሊይዛቸው ይገባል። በነዚህ ስነምግባሮች መመራት ግለሰባዊና ተቋማዊ ለውጥ እንዲመጣ ከማስቻሉም በላይ፣ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ በአግባቡ የሚፈጸም ከሆነ ሀገራዊ እድገትን የማስቀጠሉ **ፋይዳ** ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይሆንም።

# የድህረ ማንበብ ጥያቄዎች

## መልመጃ ሁለት

**ተከታዮቹ የምርጫ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርው የተዘጋጁ ናቸው። ምንባቡን ደግማችሁ በለሆሳስ በማንበብና ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ ጥያቄዎቹን መልሱ።**

1. ሰዎች በሚሰሩት ስራ ደስተኛና ስኬታማ ሆነው እንዲገኙ፡-
   ሀ. የትብብር መንፈስ ስለሚርቃቸው ብዙ ጊዜ ግባቸውን ሲያሳኩ አይታዩም።
   ለ. የሚደርስባቸውን አስተዳደራዊ በደል ለሚመለከተው ማሳወቅ የለባቸውም።
   ሐ. በእቅድ መመራት እና ጊዜያቸውን በአግባቡ መጠቀም አይኖርባቸውም።
   መ. ጠንካራ የስራ ላይ ስነምግባር ባለቤት ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል።
2. **'ተግባሪዎቻቸው'** (አንቀጽ 1) ሲል __________ ማለቱ ነው።
   ሀ. ፈጻሚዎቻቸው ሐ. አንባቢዎቻቸው
   ለ. መመሪያዎቻቸው መ. ጸሐፊዎቻቸው
3. **'እነዚህን መለያዎች**...' (አንቀጽ 2) የትኞቹን መለያዎች ለማለት ነው?
   ሀ. ሁሉንም ጥሩ የስራ ላይ ስነምግባሮች
   ለ. የስናፍናና ጊዜን በአግባቡ ያለመጠቀም መገለጫዎች
   ሐ. እምነት የሚጣልባቸውና ቀናነትን የተላበሱ
   መ. ተባብሮ መስራትና የተቋሙን ንብረቶች መንከባከብ

4. በምንባቡ መሰረት ከሚከተሉት አማራጮች 'አይወዘፍባቸውም' የሚለውን ቃል ሊተካ የሚችለው የቱ ነው?

   ሀ. አይከማችባቸውም  ሐ. አይደራረብባቸውም

   ለ. እዳ ውስጥ አያስገባቸውም  መ. 'ሀ' እና 'ለ'

5. 'ተአማኒነት ገንዘባቸው ያደረጉ' ሲል __________ለማለት ፈልጎ ነው።

   ሀ. ተአማኒነትን ቆጥበው ያከማቹ  ሐ. ተአማኒነታቸውን ያጓደሉ

   ለ. ተአማኒነትን የተላበሱ  መ. ተአማኒነታቸውን በብር የሸጡ

6. አንድን ለመፈጸም የተያዘን ስራ አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ሳይፈጽሙ አለማቋረጥ ምን ይባላል?

   ሀ. ተጨባጭነት  ሐ. ታታሪነት

   ለ. ተለዋዋጭነት  መ. ሀቀኝነት

7. መልካም ስነምግባርን የተላበሱ ሰራተኞች ይበልጥ ጠንካራ በሆኑ ቁጥር፡

   ሀ. እነሱ ብቻ ጠቃሚ እንደሆኑና ሌሎቹ አስፈላጊ እንዳልሆኑ ይረዳሉ።

   ለ. ለተቋማቸው ይበልጥ አስፈላጊ እየሆኑ እንደሚመጡ ያምናሉ።

   ሐ. አለመስራት ለድህነት የሚያጋልጥ መሆኑን መናገር ይጀምራሉ።

   መ. የያዙትን ስራ ትተው ሌላ ስራ ለመቀጠር ጥረት ያደርጋሉ።

ክፍለጊዜ፡ አራት

## መልመጃ ሦስት

**በ 'ሀ' ስር የተዘረዘሩትን የስራ ላይ ስነምግባሮች በ'ለ' ስር ከተሰጡ መግለጫዎቻቸው ጋር አዛምዱ።**

| 'ሀ' | 'ለ' |
| --- | --- |
| 1. ታማኝነት | ሀ. ጫናን በራስ መወጣት፣ ቀና መሆን፣ሀቀኛና መልካም አሳቢነት |

| | |
|---|---|
| 2. መተባበር | ለ. ስራን በቅልጥፍናና በጊዜ መከወን ጠንካራ ሆኖ መገኘትን እንደመርህ መቀበል |
| 3. ታታሪነት | ሐ. እየተናበቡ መስራት ያለውን ጠቀሜታ መረዳት፣ መታዘዝን እንደእሴት መቁጠር |
| 4. መልካም ስነምግባር | መ. በቃል መሰረት መከወን፣ ተግባራትን በወጉ ለመከወን ዝግጁ መሆንና መታመን |
| 5. ውጤታማነት | ሠ. ለያዙት ስራ መሰጠት፣ ስራን ሳያሳኩ አለመተው፣ ከስራ ሰዓታት ውጪ መስራት |

## መልመጃ አራት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአነስተኛ ቡድን ሁናችሁ በመነጋገር ተገቢ መልሶችን በመጻፍ መልሱ። ምላሾቻችሁንም በተወካያችሁ በኩል በንባብ ለክፍሉ አቅርቡ**

1. በምንባቡ ውስጥ ከተዋወቁት የስራ ላይ ስነምግባሮች የትኞቹ ይበልጥ አስፈላጊ ናቸው ትላላችሁ? ለምን?
2. ከምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሱት ውጪ አሉ የምትሏቸውን የስራ ላይ ስነምጋባሮች ዘርዝሩ።
3. የመጀመሪያውና የመጨረሻው አንቀጽ የያዟቸው ጭብጦች ምን እንደሆኑና አንቀጾቹ ለምን ተግባርም በጽሑፉ ውስጥ እንደገቡ አስረዱ።

ክፍለጊዜ፡ አምስት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

**በዚህ ትምህርት ክፍል የቃላት አውዳዊ ፍቺ እና ተዘውታሪ ቃላትን በአውድ መጠቀምን የተመለከተ ማስታወሻና መልመጃዎች ቀርበዋል።መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን ገለጻ መሰረት በማድረግ ጥያቄዎቹን መልሱ።**

**ማስታወሻ**

ተዘውታሪ ቃላት፡ እነዚህ ቃላት በዕለት ተዕለት የቋንቋ አጠቃቀማችን በአካባቢያችን እና በትምህርት ቤት ለተለያዩ አላማዎች የምንጠቀምባቸው ቃላት ናቸው። ለምሳሌ:- አስተማሪ፣ ትምህርት ቤት፣ መጽሀፍ፣ ራሳችንን የምናስተዋውቅባቸው ቃላት(የራስ እና የወላጅ ስም፣ የመኖሪያ አካባቢ ስም፣ እድሜ፣ ...) ይጠቀሳሉ።

## መልመጃ አምስት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ተዘውታሪ ቃላት በመምረጥ ተጓድለው የቀረቡትን አረፍተነገሮች አሟሉ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወላጆች | ጎረቤታሞች | ሀገር | ምግብ |
| ውሀ | ገበያ | ትምህርትቤት | መንገድ |

1. በአንድ አካባቢ ተጠጋግተው እየተጋገዙ የሚኖሩ ቤተሰቦች_______ይባላሉ።
2. ከ ________ለኑሯችን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በግዢ ማግኘት እንችላለን።
3. ለመጠጥ የምንጠቀመው ________ ንጹህ መሆን አለበት።
4. ልጆች_________እና መምህራን የሚመክሯቸውን ተቀብለው መተግበር አለባቸው።
5. የዕውቀት መገብያ ስፍራ__________ይባላል።
6. ሁሉም ዜጋ ለ________ ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽዖ ማበርከት አለበት።
7. የ_________ደህንነት ህጎችን ማክበር ከአደጋ ይጠብቃል።
8. የተመጣጠነ__________ለህጻናት አእምሮ ዕድገት እጅግ አስፈላጊ ነው።

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ቀደም ሲል 'የስራ ላይ ስነምግባር' በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ ተወስደዋል። እነዚህም በምንባቡ ውስጥ ተለይተው የተመለከቱ ሲሆን ወደ ምንባቡ ተመልሳችሁ አውዱን በማየት በ'ሀ' ስር የተዘረዘሩትን በ'ለ' ስር ካሉ ተዘውታሪ ፍቺያቸው ጋር አዛምዱ።**

| 'ሀ' | 'ለ' |
|---|---|
| 1. እንደመርህ | ሀ. ስራ የሚበድሉ |
| 2. ወለም ዘለም | ለ. ጠንካራ ሰራተኝነት |
| 3. ባልደረቦች | ሐ. እንደ ጠቃሚ ባህል |
| 4. ሳይታክቱ | መ. ጥቅም |
| 5. ልግመኛ | ሠ. ወዲያ ወዲህ |
| 6. ለመከወን | ረ. እንዳይለፉ |
| 7. እንዳይባዝኑ | ሰ. የስራ ጓደኞች |
| 8. ታታሪነት | ሸ. ሳይሰለቹ |
| 9. ፋይዳ | ቀ. ለመፈጸም |
| 10.እንደእሴት | በ. እንደአካሄድ |

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

ከዚህ በታች አንቀጽን የተመለከተ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። የቀረበው ማስታወሻ ላይ መምህራችሁ ማብራሪያ ከሰጧችሁ እና እናንተም ካነበባችሁት በኋላ የቀረቡትን መልመጃ እና ተግባራት በትዕዛዛቱ መሰረት ስሩ።

# አንቀጽ መጻፍ

**ማስታወሻ**

**አንቀጽ** አንድ ነጠላ ሀሳብን ለመግለጽ ሲባል፣ ስለአንድ ሀሳብ የሚያወሱ፣ ምሉዕ የሆኑ እና ተያያዥነት ያላቸው ዓረፍተነገሮች ያካተተ የፅሁፍ አካል ነው። አንቀጽ አንድ ኃይለ ቃል ብቻ የያዘ እና ይህንን ሀይለቃል የሚያጎላምሱ ከአንድ በላይ ዝርዝር ዓረፍተነገሮችን የሚይዝ ነው።

ምሳሌ፡-

*የራስን ሀሳብ በማካፈልና የሌሎችንም በመቀበል ለለውጥ መሥራት አንደኛው የሥራ ላይ ሥነምግባር ነው። የተሻለ ውጤት የሚመጣው ግለሰቦች በሚያመነጩት የተሻለ ሀሳብ ስለሆነ የተሻሉ ሀሳቦችን መርጦ ለመጠቀም መደማመጥ የግድ ይላል። ስለዚህ በውይይትና በምክክር ወቅት በስርዓት በመደማመጥ፣ አንዱ የሌላኛውን ሀሳብ አክብሮ የተሻለና ሚዛን የሚደፋውን ሀሳብ መርጦ ስራ ላይ በማዋል ውጤታማነትን ማረጋገጥ ይቻላል።*

በዚህ ምሳሌ እንደሚታየው በአንቀጹ ኃይለቃል "*የራስን ሀሳብ በማካፈልና የሌሎችንም በመቀበል ለለውጥ መሥራት የሥራ ላይ ሥነምግባር ነው።*" በሚል የሰፈረው ዋና ሀሳብ ከሱ በኋላ በመጡት መዘርዝር አረፍተነገሮች ተብራርቷል።*መዘርዝር ዓረፈተነገሮቹም ብዙ ሆነው ይህንኑ ሀይለቃል የሚያጠናክሩ ሲሆኑ የሀሳብ ተዛምዶም አላቸው።*

## መልመጃ ስድስት

**ከዚህ በታች ዓረፍተነገሮች ተዘበራርቀው ተቀምጠዋል። በቡድን በመሆን ቅደምተከተላቸውን አስተካክሉ። አንቀጽም መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

1. በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ ሌላ ትምህርትቤት ለመስራት ወስኗል።
2. አንደኛ አሮጌው ትምህርት ቤት በሚፈርስበት ጊዜ ሰፊ የመጫወቻ ሜዳ ለመስራት ጥሩ ዕድል የሚያስገኝ በመሆኑ ነው።
3. በአካባቢያችን የሚገኘው ትምህርትቤት ከማርጀቱ የተነሳ ፈራርሷል።
4. በውይይቱ ወቅትም አዲሱ ትምህርት ቤት የሚሰራበት ቦታ በአሮጌው ወይም በሌላ ስፍራ ይሁን በሚል ሁለት ሀሳብ አቀረቡ።
5. በመጨረሻም አሮጌው ትምህርት ቤት በነበረበት ስፍራ ይሰራ የሚለው ሀሳብ በአብላጫ ድምጽ ተቀባይነት አገኘ።
6. ትምህርት ቤቱ የሚሰራበትን ቦታ በተመለከተ ማህበረሰቡ ተጨማሪ ውይይት አካሄደ።
7. አራተኛ ከድሮው ትምህርት ቤት ራቅ ብሎ ሌላ ቦታ መፈለግ የማይታሰብ በመሆኑ ነበር።
8. ለዚህም በወቅቱ የተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች ቀርበው ነበር። እነዚህም፡-
9. ሶስተኛው እዚሁ አካባቢ ሌላ ቦታ እንዳይመረጥ ሰፊ ቦታ አልነበረም።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

### ተግባር ሁለት

በአነስተኛ ቡድን ሆናችሁ በክፍላችሁ በተደጋጋሚ የቤት ስራ ሳይሰራ ስለሚመጣ ወይም ሁልጊዜ ስለሚያረፍድ ጓደኛችሁ በመወያየት ችግሩ የሚፈታበትን መፍትሔ በአንድ አንቀጽ አደራጅታችሁ ከጻፋችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

### ተግባር ሦስት

መልካም ስነምግባር የሌለው ተማሪ ምን ዓይነት ባህርይ እንደሚያንጸባርቅ በቡድናችሁ ተወያይታችሁ ማስታወሻ እየያዛችሁ ተወያዩ። የያዛችሁትን ማስታወሻ መነሻ አድርጋችሁ አንድ የተሟላ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**በዚህ ትምህርት የአረፍተነገር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽን የተመለከተ ማስታወሻ እና መልመጃዎች ቀርበውላችኋል። ስለሆነም መልመጃዎቹን በትዕዛዛቱ መሰረት ስሩ።**

### ማስታወሻ

**ባለቤት እና ማሰሪያ አንቀጽ**

**ባለቤት፡** በአረፍተነገር ውስጥ ድርጊት ፈጻሚ የሆነ አካል ነው። ወይም ዓረፍተነገሩ የሚናገርለት ስም ወይም ተውላጠ ስም ነው።

**ማሰሪያ አንቀጽ፡-** በአረፍተ ነገር ውስጥ ሀሳብን የሚቋጭ ቃል ወይም ሀረግ ነው።

**ምሳሌ፡-**

ቶሎሳ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ። የመጀመሪያው የተሰመረበት ቃል የአረፍተነገሩ ባለቤት ሲሆን በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ የተሰመረበት ቃል ማሰሪያ አንቀጽ ነው።

## መልመጃ ሰባት

ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ለዩ።

**ምሳሌ፡**

*መምህራን ተማሪዎቻቸው በከፍተኛ ውጤት ሲያልፉላቸው ይደሰታሉ።*

ባለቤት፡ **መምህራን**

ማሰርያ አንቀጽ፡ **ይደሰታሉ**

1. ሀኪሞች ለታካሚዎቻቸው ምርመራ ካደረጉ በኋላ መድሀኒት ያዙላቸዋል።
2. መረዳዳት በማኅበራዊ ህይወት ውስጥ መልካም እሴት ነው።
3. በርካታ ህጻናት ያለዕድሜያቸው ስራ እንዲሰሩ ይገደዳሉ።
4. የኮረና በሽታ በዓለማችን ከፍተኛ ስጋት ሆኗል።
5. የስራ ላይ ስነምግባር በየትኛውም የስራ መስክ አስፈላጊ ነው።

ለ. ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ያላቸው አምስት አረፍተነገሮች መስርቱ።
ለምሳሌ፡ ዋቅቶላ ታታሪ አትሌት ነው።

ክፍለጊዜ፡ አሥር

ሐ. ከዚህ በታች በቀረበው ሳጥን ውስጥ የተሰጡትን ቃላት እና ሀረጋት በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ላሚቱ | በትምህርታቸው | በከፍተኛ ማዕረግ ተመረቀች |
| ኢትዮጵያ | በኮምፒውተር ጥገና ሙያ | በትምህርቱ ውጤታማ ሆኗል |
| ቶለሳ | በተለያዩ ክብረበዓላት | ይዘጋጃሉ |
| ባህላዊ ምግቦች | በርትቶ ስለምያጠና | በየቀኑ ትታለባለች |
| የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች | አምስት ሌትር ወተት | ትገኛለች |
| መገርቱና ሂርጳ | ከተወሰኑ ወራት በኋላ | ጎበዞች ናቸው |
| ታላቅ እህቴ | በአፍሪካ ቀንድ | ለክልላዊ ፈተና ይቀመጣሉ |

# ምዕራፍ ሁለት

## ባህላዊ ቅርስ

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦

- የሌሎችን ሀሳብ በጥልቀት አዳምጣችሁ ታንጸባርቃላችሁ፤
- የቃላትን ፍቺ ከምንባቡ በመነሳት ታስረዳላችሁ፤
- የባህልንና ቅርስን ጽንሰ ሀሳብ ምንነትን ታብራራላችሁ፤
- ባለሶስት አንቀጽ አመዛዛኝ ድርሰት ትጽፋላችሁ፤
- በተለያዩ አውዶች ውስጥ አዳዲስ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፤
- ውስብስብ ሁነቶችን በቅደም ተከተል ትተርካላችሁ።

### ክፍለጊዜ አንድ

### ትምህርት አንድ፦ ማዳመጥ

ከዚህ በታች የተለያዩ መልመጃዎችና ተግባራት ቀርበዋል። የቀረቡትን መልመጃዎችና ተግባራት በትዕዛዛቸው መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።



የአባ ጅፋር ቤተመንግስት

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ከማዳመጣችሁ በፊት በቃል መልሱ።**

1. በሀገራችን ከሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶች መካከል የምታውቁትን ዘርዝሩ።
2. ከላይ የቀረበውን የአባ ጅፋር ቤተመንግስት ፎቶግራፍ በመመልከት የተገነዘባችሁትን ለጓደኞቻቸው አስረዱ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን እያዳመጣችሁ በጽሁፍ መልሱ።**

1. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ __________ እና __________ ቅርስ ነው።
2. ቤተመንግስት ከባህር ጠለል ________ ሜትሮች ከፍታ ላይ ይገኛል።
3. የቤተመንግስቱ የስነህንጻ ጥበብ አብዛኛው ስራት ግብዓት_______ ነው።

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እስካሁን ሲነበብ ባዳመጣችሁት መሰረት በቃል መልስ ስጡ።**

1. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት የት ይገኛል?
2. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት ኪነህንጻ የማን አሻራ ይታይበታል?
3. የአባጅፋር ግዛት በወቅቱ ጠንክሮ የወጣበት ምክንያት ምንድን ነው?
4. አባ ጅፋር ቤተመንግስቱ የተመሰረተበትን ስፍራ የመረጡት በምን ምክንያት ነበር?

5. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት የሚያበረክተውን ባህላዊ እና ታሪካዊ ጠቀሜታዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

### ተግባር አንድ

ከአዳመጣችሁት ጽሁፍ በመነሳት የአባጅፋር ቤተመንግስት አሁን ያለበትን ሁኔታ በጥንድ ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሀሳባችሁን አጋሩ።

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## መልመጃ ሁለት

በአዳመጣችሁት ጽሁፍ ከዚህ በታች የቀረቡት ሀሳቦች ቀርበዋል። ሀሳቦቹን በማስፋት ለጓደኞቻችሁ አንጸባርቁ።

ሀ. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት መገኛ ስፍራ
ለ. የአባ ጅፋር ግዛት መጠናከር ምክንያት
ሐ. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት አሁናዊ ሁኔታ
መ. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት ጥቅም

ክፍለጊዜ፡ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ከዚህ በታች የቀረቡት ተግባራት የመናገር ክሂላችሁን ለማዳበር የሚረዱ ናቸው።ለተግባራቱ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያና በትእዛዛቱ መሰረት ተገቢ መልስ ስጡ።

### ተግባር ሁለት

እንደአባ ጅፋር ቤተመንግስት ያሉ ጥንታዊ ቅርሶችን ሁኔታ በተመለከተ ከተለያዩ ምንጮች ሀሳብ ካሰባሰባችሁ በኋላ በቡድናችሁ በመሆን ሀሳቦቹን አደራጁ፡ ከዚያም ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ አራት

### ተግባር ሶስት

የአባ ጅፋር ቤተመንግስት ለመጎብኘት ብትፈልጉ እናንተ ካላችሁበት እስከ ጅማ በመኪና ለመጓዝ በየት አቅጣጫ እንደምትጓዙ እና በጉዟችሁ የሚያጋጥሟችሁን ከተሞች እና የገጠር መንደሮች በመጥቀስ በቡድናችሁ ከተወያያችሁበት በኋላ የደረሳችሁበትን የተደራጀ ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር አራት

በቡድን ሆናችሁ በአካባቢያችሁ የሚገኝ አንድ ቅርስን ጎብኙ። ስለቅርሱ ያገኛችኋቸውን መረጃዎች በአስተዋጽኦ መልክ አደራጁ። ከዚያም የተደራጀውን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ዘግቡ።

ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ከዚህ በታች የቀረበው ምንባብ እና መልመጃዎች የማንበብ ክሂላችሁን ለማዳበር የሚያግዙ ናቸው። በመሆኑም ምንባቡን በትኩረት በማንበብ የቀረቡትን መልመጃዎች ስሩ።**

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ጽሁፉን ከማንበባችሁ በፊት በቃል መልሱ።**

1. በአካባቢያችሁ በደል የደረሰባቸው ሰዎች በደላቸውን ለማን ያመለክታሉ?
2. በሀገራችን በተለያዩ ማህበረሰቦች የሚታወቁ የግጭት ማስወገጃ ስርዓቶችን ዘርዝሩ።
3. ‹‹ሉኮ›› የሚል ቃል ሰምታችሁ የምታውቁ ከሆነ ፍቺውን ለጓደኞቻችሁ አብራሩ።

## ሉኮ (Lukoo)

የትኛውም ህብረተሰብ በውስጡ የሚፈፀመውን ወንጀል ለመቆጣጠር ተፈጽሞ ከተገኘም ለመቅጣት ሕግ መስርቶ እንደሚጠቀምበት ይታወቃል። ህብረተሰብ ህግ የሚደነግገው ባለው እውቀትና ባህል ላይ ተመስርቶ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ጥፋት የሚፈፀመው በተለያዩ ምክንያቶች ሆኖ እናገኛለን። ያለ አግባብ ሀብት ለማካበት፣ በቅናት፣ በምቀኝነት፣ በቂም በቀል፣ በድንገት (በስህተት) ወዘተ ምክንያት ወንጀል ይፈፀማል። ታድያ የሰው ባህርይ ሆኖ ጥፋት የፈፀመ ሰው በቅንነት ጥፋቱን አምኖ የሚገባውን ቅጣት ለመቀበል ፍላጎት አያሳይም፣ የሚያሳይ ቢኖርም ጥቂት ነው። በመሆኑም ከገዳ ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱ የሆነው "ሉኮ" ከዚህ ዓይነት ግንዛቤ የመነጨ ነው። "ሉኮ" የሚለው ቃል "ሉካ" (Luka) ከሚለው የኦሮምኛ ቃል የተገኘ ነው። "ሉካ" ማለት በኦሮምኛ እግር ማለት ነው። "ሉኮ" ሲባል ደግሞ ወንጀል እንዳይደበቅ የሚደረግበት በህብረተሰብ ውስጥ ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው ወንጀሉን እንዳይደብቅ የሚመረመርበት ሥርዓት ነው።

በኦሮምያ ምእራባዊ ክልል በሚገኙ የገዳ ማእከላት የሚከወነው ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ስርአት በሁለት ደረጃ ይታያል። አንዱ ያለካሣ ወይም በትንሽ ካሣ የሚያልቅ የእርቅ ሥርዓት ነው። ይህንን የእርቅ ሥርዓት እንደ ዘመኑ አነጋገር እንደ ስራ አስፈጻሚ የሚቆጠረው “ሸነቻ” (shanacha) የሚባለው አካል ይጨርሰዋል። ሸነቻ አምስት አባላት ያሉት ኮሚቴ ነው። ሌላው በትልቅ ካሳ ወይም በከባድ ቅጣት እልባት የሚያገኝ ጉዳይ ነው። ይህንን ጉዳይ የሚያየው የገዳው ማእከል “የቦ” (yabboo) /ምክር ቤት/ ነው። የምክር ቤቱ የአባላት ብዛት ማእከሉ በሚያካልለው የአካባቢ ስፋት ይወሰናል። የገዳ ማእከል የሚያካልለው አካባቢ በጣም ሰፊ ከሆነ የምክር ቤቱ አባላት እስከ 100 ይደርሳሉ። የ“የቦ” አባላት ምንም ያህል ማእከሉ የጠበበ ቢሆን ከዘጠኝ አያንሱም።

በእነዚህ የገዳ ማእከላት የሚታዩ ጉዳዮች በሉኮ እና ያለ ለኮ የሚከናወኑ ናቸው። ያለ ሉኮ የሚሆነው ጥፋተኛው ጥፋቱን ካመነ ወይም በቂ ምስክሮች ባለበት ከተፈፀመ ነው። አንድ ሰው በረቀቀ መንገድ ወንጀል ተፈጽሞበት ወንጀል የተፀመበትን አካል ወይም ሰው ካላወቀ፣ አውቆም ምስክር ከሌለው በቀጥታ ወደ ገዳ ማእከል ሂዶ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይገኛል። ከዚያ ለምክር ቤቱ የደረሰበትን በደል ያሳውቃል። የደረሰበት ጉዳት በዐይን የሚታይ ከሆነ ለምክር ቤቱ ያሳያል። የማይታይ ከሆነ ለምሳሌ ንብረት ከተሰረቀበት ንብረቱ መሰረቁን የሚያውቅለት ሰው ያቀርባል፣ ወይም በቃለ መሃላ ያረጋግጣል። ምክንያቱም በኦሮሞ ባህል መሃላ ትልቅ ቦታ አለው።

ተበዳዩ ወይም ችግር የደረሰበት ሰው ለገዳው ምክር ቤት ካሳወቀ በኋላ የሚጠረጥረው ወገን /ሰው/ ካለ እንዲናገር እድል ይሰጠዋል። የሚጠረጥረው ሰው ወይም ቤተሰብ ካለ ይናገራል። ከዚያ በኋላ የተጠረጠረው ሰው በገዳው ምክር ቤት ላይ እንዲገኝ የገዳ መሪ በሚልከው መልእክተኛ አማካይነት

ጥሪ ይደረግለታል። ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረው ሰው በገዳ ምክር ቤት ላይ ከቀረበ በኋላ የተጠረጠረበት ጉዳይ ይነገረውና መፈፀሙን ወይም አለመፈፀሙን ይጠየቃል። ካመነ ምክር ቤቱ ሌላ አካሄድ ይከተላል። ካላመነ ግን "ትምላለህ?" ይባላል። "አዎን" ካለ በአንተ መሃላ ብቻ ጉዳዩን መዝጋት ስለማንችል "ሉኮ ፊዲ" (Lukoo fidi) /ሉኮ አምጣ/ ወይም "ሉካ ደበርፈዱ" (Luka dabarfadhu) /እግርህን አሳልፈህ ስጥ/ ይባላል።

እግርህን አሳልፈህ ስጥ ማለት አንተም እንዳትጠፋ፤ በንዴት ተጨማሪ ጥፋትም እንዳታደርስ በተፈለግህ ቁጥር አንተን የሚያቀርብና ስለአንተ ንጽህና በቃለ መሃላ የሚያረጋግጥ ከዘመዶችህ ወክል ማለት ነው። እምቢ ለማለት ባህሉ ስለማይፈቅድለት ከዘመዶቹ ከሦስት እስከ አምስት የሚሆኑ ሰዎችን ይወክላል። ከዘመዶቹ የሚወክላቸው ሰዎች ዘመዶቹ ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን በጥቅም የማይደለሉ፣ በህብረተሰቡ ዘንድ ከበሬታ ያላቸው ሰዎች መሆን አለባቸው።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ሉኮ የ________ ቋንቋ ስያሜ ነው።
2. በኦሮሞ ብሔር ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ስራ አስፈጻሚ ማእከላት ________እና ________ተብለው ይጠራሉ።
3. ሸነቻ ________አባላት ያሉት ኮሚቴ ነው።
4. የየበ ማእከል አባላት ቁጥር ከ ________ ማነስ የለባቸውም።
5. በጥፋት የተጠረጠረ ሰው እግርህን አሳልፈህ ስጥ የሚባለው ጥፋቱን ________ ነው።
6. በጥፋት የተጠረጠረ ሰው ከ ________ እስከ ________ የሚሆኑ ሰዎችን አስቀድሞ ይወክላል።

**በጥፋት የተጠረጠረ ሰው ከወከለ በኋላ ውሳኔ እንዴት የሚያሰጠው ይመስላችኋል?**

ተጠርጣሪው ከዘመዶቹ /ከጎሳው/ ሰዎችን ከወከለ በኋላ ምክር ቤቱ "ዘመዳችሁ በእንዲህ ዓይነት ጉዳይ ተጠርጥሮ እምነት ክህደት ሲጠየቅ ስለካደ እናንተ ምን ትላላችሁ?" ተብሎ ይጠይቃል። የተጠርጣሪው ወገን "እናጣራለን" ብለው ጊዜ እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ። ተጠርጣሪው የወከላቸው ሰዎች ዘመዳቸውን ለማዳን ብለው **ቀልባቸው** እያወቀ በፍፁም አይምሉም። በሀሰት ከማሉ ማህበረሰቡ ከማህበራዊ ኑሮ ያገላቸዋል። ከባድ ችግር ቢደርስባቸው እንኳን ማህበረሰቡ አይደርስላቸውም። በዚህ ላይ ደግሞ ጩቡም/ሀጢያት/ ይደርስባቸዋል።

ስለዚህ የተጠረጠረበትን ጉዳይ ዘመዳቸው ፈጽሞ ከሆነ እንዲያምንና ምክር ቤቱን ይቅርታ ጠይቆ የሚወሰንበትን ቅጣት እንዲቀበል ያደርጉታል። ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ጉዳይ በፍፁም ካላደረገ አለማድረጉንም ህብረተሰቡ የሚያምን ከሆነ ዘመዶቹም ይህንን ካመኑበት ምለው ነፃ ያወጡታል። ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን አለማድረጉ ታምኖበት ነፃ ሆነ ማለት የተፈፀመው ጥፋት /ወንጀል/ ተደብቆ ይቀራል ማለት አይደለም። መላው ህብረተሰብ ኃላፊነቱን እንዲወስድ ይደረጋል። ስለዚህ ህብረተሰቡ **ውስጡን ፈትሾ** የሚጠረጥረውን ለምክር ቤቱ መጠቆም አለበት። ምክር ቤቱ **ሀቁን** ለማውጣት አዲስ በተጠረጠሩት ላይም የሉኮ ስሌቱን ይተገብራል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚከናወነው የምርመራ ስሌት ወንጀል ተደብቆ እንዳይቀር ያደርጋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ አጥፊዎች የሚፈረድባቸውን ካሣ መክፈል አንችልም ብለው እውነትን እንዳይደብቁ የተነደፈ ሌላ ስሌት መኖሩ ነው። ይህ ስሌት "ሂርጳ" የሚባል ነው። ሂርጳ የሚለውን ቃል እርዳታ ማለት ይገልፀዋል።

ስለዚህ አጥፊው የሚከፍለውን ካሣ እርዳታ ጠይቆ እንዲከፍል ባህሉ ይፈቅድለታል። የደም ካሣ /ጉማ/ ከሆነ ግን ጭራሹን ግለሰቡ ሚሊዮነር ቢሆን እንኳን ከኪሱ አይከፍልም። ክቡር የሰው ህይወት ስላ አጠፋ ሂርጰ /እርዳታ/ ጠይቆ የሰው እጅ አይቶ፣ ተጸጽቶ፣ እርዳታ ሲጠይቅም "በእኔ የደረሰው አይድረስባችሁ" ብሎ መክፈል አለበት። ይህ ስሌት ገንዘብ የሌለው ሰው ወንጀል ቢፈፅም እንኳን የምሰጠው ካሳ የለኝም ብሎ ወንጀሉን እንዳይደብቅ ያደርጋል። በሌላ በኩል ተበዳዩ ያለካሣ እንዳይቀርም ያደርጋል። እንግዲህ ሉኮ ሂርጳን በውስጡ አካቶ በእንደዚህ ዓይነት መልኩ ይከናወናል።

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ያነበባችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ።**

1. በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ወንጀል የሚፈጸመው በምን ምክንያቶች ነው?
2. ‹‹ሉኮ›› ስርዓት ምን ጊዜ ተግባራዊ ይደረጋል?
3. የሽነቻ እና የየቦ ማእከላት ኃላፊነቶች ምን ምን ናቸው?
4. በጥፋት የተጠረጠረ ሰው ‹‹ሉካ ፊዲ ወይም ደበርፊዱ›› የሚባለው ለምድን ነው?
5. የጥፋት ተጠርጣሪ ተወካዮች ኃላፊነት ምንድን ነው?
6. ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን አለማድረጉ ታምኖበት ነፃ ከሆነ በኋላ ወንጀል ተደብቆ እንዳይቀር ምን ይደረጋል?

7. አጥፊዎች የሚፈረድባቸውን ካሣ መክፈል አንችልም ብለው እውነትን እንዳይደብቁ ምን ይደረጋል?
8. የደም ካሣ /ጉማ/ ከሆነ አጥፊው ጉማውን እንዴት ይከፍላል?
9. የሂርጳ ዋና አላማዎች ምን ምን ናቸው?
10. እርዳታ ሲጠይቅም "በእኔ የደረሰው አይድረስባችሁ" ብሎ መክፈል አለበት። የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?
11. በጥፋት የተጠረጠረ ሰው መሃላ የሚፈጽመው ምን ጊዜ ነው?

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

### ተግባር አምስት

በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ስርአት በሁለት ደረጃ ይታያል። ምንባቡን በድጋሚ ካነበባችሁ በኋላ እነዚህን የግጭት ማስወገጃ ደረጃዎች አስፋፍታችሁ በቡድናችሁ ተወያዩባቸው። በመጨረሻም የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ከዚህ በታች ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እንድትሰጡ የሚያግዝ መልመጃ ቀርቦላችኋል። መልመጃውን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

### መልመጃ ሶስት

ሀ. ከዚህ በታች ለተሰመረባቸው አዳዲስ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ትርጉም ስጡ። ቃላቱን በሌላ አወድ ወይም ዓረፈተነገር ተጠቀሙ።

**ሀ. ከዚህ በታች ለተሰመረባቸው አዳዲስ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ትርጉም ስጡ። ቃላቱን በሌላ አወድ ወይም ዓረፈተነገር ተጠቀሙ።**

1. ህብረተሰብ ህግ <u>የሚደነግገው</u> ባለው እውቀትና ባህል ላይ ተመስርቶ ነው።
2. አንድ ሰው <u>በረቀቀ</u> መንገድ ወንጀል ተፈጽሞበት ከሆነ ለገዳ ምክር ቤት ያመለክታል።
3. በኦሮሞ ባህል መሃላ <u>ትልቅ ቦታ</u> አለው።
4. ተጠርጣሪው የወከላቸው ሰዎች ዘመዳቸውን ለማዳን ብለው <u>ቀልባቸው እያወቀ</u> በፍፁም አይምሉም።
4. ህብረተሰቡ <u>ውስጡን ፈትሾ</u> የሚጠረጥረውን ለምክር ቤቱ መጠቆም አለበት።
5. ምክር ቤቱ <u>ሀቁን</u> ለማውጣት አዲስ በተጠረጠሩት ላይም የሉኮ ስሌቱን ይተገብራል።

**ለ. ከዚህ በታች በ ' ሀ ' ስር ለቀረቡት ቃላት በ ' ለ ' ስር ከቀረቡት ገለጻዎች የሚስማሟቸውን በመምረጥ አዛምዱ።**

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. ሉኮ | ሀ. የደም ካሳ |
| 2. ሂርጳ | ለ. ከ9-100 አባላት ያሉት የገዳ ምክር ቤት |
| 3. ሸነቻ | ሐ. አምስት አባላት ያሉት የገዳ ኮሚቴ |
| 4. የቦ | መ. እርዳታ |
| 5. ጉማ | ሠ. ወንጀል እንዳይደበቅ ማድረጊያ ስርዓት |
| | ረ. ዕርቅ ማውረጃ ስርዓት |

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

ከዚህ በታች አመዛዛኝ ድርሰትን የተመለከተ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። የቀረበውን ማስታወሻ መምህራችሁ ማብራሪያ ሲያደርጉላችሁ በትኩረት አዳምጡ። ከዚያም በሳጥኑ ውስጥ የተቀመጡትን የመጻፍ ሂደቶችን ተከትላችሁ ተግባራቱን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

አመዛዛኝ/አከራካሪ/ድርሰት፡- አንድ ጸሀፊ አንድ የሚያከራክር ሀሳብን ይዞ በመነሳት በሀሳቡ ዙሪያ ያለውን የግል አመለካከት ሌላው ሰው እንዲቀበለው ወይም እንዲያምን በማድረግ ይጽፋል። በዚህም ጸሀፊው ያመነባቸውን ምክንያቶች፣ ማብራሪያዎችና እውነታዎች አቅርቦ ለማሳመን ጥረት የሚያደረግበት የድርሰት አይነት ነው። ድርሰት ሲጻፍም የሚከተሉትን ሂደቶች መከተል ያስፈልጋል።

- ርዕስ መምረጥ።
- በርዕሱ ሊነሱ የሚችሉ ነጥቦችን በቢጋር መልኩ መዘርዘር።
- በሀሳብ የሚመሳሰሉትን ባንድ ላይ መመደብ።
- የድርሰትን የመጀመሪያ ረቂቅ መጻፍ።
- የድርሰት ረቂቅን በማንበብ የስርዓተነጥቦችና የሰዋስው ግድፈቶችን በማረም እንደገና መጻፍ።
- ድርሰቱን ለሌላ ሰው ሰጥቶ የሀሳብ ፍሰቱ፣ ከድርጊትና ጊዜ ቅደምተከተል አጠባበቅ፣ ከስርአተ ነጥቦች አጠቃቀም አንጻር መመርመር።

## ክፍለጊዜ፡ አሥር

### ተግባር ስድስት

ሀ. ከላይ በሳጥን ውስጥ የተቀመጡትን የድርሰት መጻፊያ ቅድምተከተሎች አንብቡ። ከዚያም ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሶች አንዱን በመምረጥ ሶስት አንቀጽ ያለው አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. የቅርስ ጥበቃ
2. ቅርስና የሀገር ዕድገት

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

### ተግባር ሰባት



ከላይ ያለውን ስዕል ተመልከቱ። ስዕሉ የምን በዓል አከባበር እንደሆነ ለዩ። በበዓሉ አተገባበር ወቅት የሚፈጸሙና የሚታዩ ነገሮችን ሁሉ ጻፉ። ምን እንደሚወክሉና ምን እንደሚያመለክቱም ተወያዩ። ከዚያም ተወያይታችሁ ባገኛችሁት ሀሳብ መነሻ የስዕሉን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያስረዳ ማጠቃለያ አንቀጽ ጽፋችሁ በንባብ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ከዚህ በታች ስለአሁን ጊዜ የግስ አንጻር የተመለከተ ማስታወሻ ቀርቧል። መልመጃዎችም ቀርበዋል። መልመጃዎቹን በትዕዛዛቱ መሰረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

የአሁን ጊዜ የግስ አንጻር የተጠቀሰው ድርጊት የተፈጸመበት ጊዜ አሁን መሆኑን ወይም ተናጋሪው እየተናገረ ባለበት ጊዜ ድርጊቱ እየተከናወነ ያለ መሆኑን ያመለክታል።

ምሳሌ፡ ምሳዬን እየበላሁ ነው።

መኪናው ከአዲስ አበባ እየመጣ ነው።

መምህሩ ተማሪዎቹን እያስተማረ ነው።

### መልመጃ አራት

ሀ. ከዚህ በታች ከቀረቡት ዓረፍተነገሮች ምሳሌውን መሰረት አድርጋችሁ በአሁን ጊዜ አንጻር የተገለጹትን ለዩ።

1. ሰውዬው ትላንት ሀኪም ቤት ሄደ።
2. እናቴ ገበያ እየሄደች ነው።
3. ጓደኞቼ የቤት ስራ እየሰሩ ናቸው፡፡
4. ቤተሰቦቼን ለመጎብኘት ወደ አዲስ አበባ ይሄዳል።
5. ወንድሜ ባለፈው ዓመት በዲግሪ ተመርቋል።

6. ዜናው ተላልፏል።
7. ቶሎሳ ከእህቱ ጋር እያጠና ነው።
8. ጫልቱ ገበያ ሄደች።
9. ቀነኒሳ የማራቶን ሩጫ አሸነፈ።
10. ነጋሳ ትምህርቱን እያጠና ነው

**ለ. ከላይ በአሁን ጊዜ አንጻር ያልቀረቡትን አረፍተነገሮችን ለይታችሁ ወደ አሁን ጊዜ አንጻር ቀይራችሁ ጻፉ።**

# ምዕራፍ ሶስት

## ሰብአዊ እሴቶች

### የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- አድምጣችሁ ጽሁፍን መገምገም ትችላላችሁ፤
- ከሌሎች ጋር ምልልስ ታከናውናላችሁ፤
- ጥምር ቃላትን በአውድ ትጠቀማላችሁ፤
- የነጠላ እና የብዙ ቁጥር ስሞች ትለያላችሁ፤
- አራት አንቀጽ ያሉት ገምጋሚ አንቀጽ ትጽፋላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**‹‹ሴቶች እና የስራ ዕድል›› በሚል ርዕስ የቀረበን ጽሁፍ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ማስታወሻ በመያዝ አዳምጣችሁ የቀረቡትን ተግባራትና መልመጃዎች በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።**

## ሴቶች እና የስራ ዕድል

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በቤተሰባችሁ ወይም በጎረቤታችሁ ያስተዋላችሁት ጾታን መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል ካለ ለጓደኞቻችሁ ግለጹ።
2. በመገናኛ ብዙኃን በተደጋጋሚ ስለሴቶች እና የስራ ዕድል ሲነገር የሰማችሁትን ሀሳብ በማስታወስ ለጓደኞቻችሁ አብራሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ስለኢትዮጵያ ሴቶች አስተያየት የሰጡት እነማን ናቸው?
2. የኢትዮጵያን ሴቶች ኑሮ አስቸጋሪ የሚያደርጉ ስራዎች ምን ምን ናቸው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሠረት በቃል መልሱ።**

1. ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ዕድል የሚኖራቸው ምን ምን የስራ ዕድል ላይ ነው?
2. ሰማንያ አምስት በመቶ ሴቶች በምን ስራ ላይ የተሰማሩ ናቸው?

**ለ. ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት አድርጋችሁ ከዚህ በታች ተጓድለው የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች በሰንጠረዥ ከቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በመምረጥ አሟልታችሁ ጻፉ።**

### ተግባር አንድ

በኢትዮጵያ ሴቶች ሕይወት ከመለወጥ አንጻር መፍትሔ የምትሉትን ሀሳብ አቅርቡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| የጎላ | ስር በሰደደው | ማሽጋገርን | ሚና |
| የተቆራኙ | ከእጅ ወደ አፍ | ጨርሶ | ታዳጊ |

1. ሴቶች_________ በሆነ የእርሻ ስራ በሚተዳደሩ አርሶ አደሮች ውስጥ ይኖራሉ።
2. ሴቶች የጉልበት ስራ ከሚሰራበት የገጠሩ የግብርና ኢኮኖሚ ጋር _________ ናቸው።
3. የኢትዮጵያ ሴቶች በግብርናው ዘርፍ _________ድርሻ አላቸው።
4. _________ ባህላዊ እምነት የሴቶችን የተቀጢላነት ደረጃ አላሻሻለውም።
5. በሴቶች ላይ ያለንን አመለካከት ወደ ተሻለ ደረጃ_________ይጠይቃል፡
6. ጥሩ ገንዘብ፣ ዕውቀትን፣ መረጃ የማግኘትና የመቆጣጠር እድላቸው _________ አይኖርም።
7. ይህም በመሆኑ የግብርና ውጤቶች ምርት ገበያ ውስጥ ያላቸውን _________ ያሳንሳል።
8. በግብርናው ዘርፍ የጎላ ድርሻ ቢኖራቸውም በሌሎች_________ ሀገሮች ያላቸው ሚና የተሻለ ነው።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ከዚህ በታች ባዳመጣችሁት ምንባብና ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ባገኛችሁት መረጃዎች ላይ ተወያይታችሁ የምትሰሯቸው ተግባራት ቀርበዋል። ተግባራቱን በትዕዛዛቱ መሰረት በትኩረት ስሩ።

### ተግባር ሁለት

**ቀጥሎ በቀረበው ጥያቄ ላይ በጥንድ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለመምህራችሁ በቃል አቅርቡ።**

1. ማህበረሰባችን በሴቶች ላይ ያለው አመለካከት እንዲቀየር ምን መሰራት አለበት?
2. ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ። ስትወያዩ ማስታወሻ ያዙ። የያዛችሁትን ማስታወሻ አደራጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አሰሙ።
   ሀ. በአካባቢያችሁ በሴቶች ላይ በደሎች ሲፈጸሙ ምን ታደርጋላችሁ?
   ለ. በአካባቢያችሁ ሴቶች ያላቸው የስራ ድርሻ ምን ይመስላል? ገምግሙ።

## ክፍለጊዜ፡ ሶስት

### ተግባር ሶስት

ስለ ስርዓተ ጾታ የስነ-ዜጋ መምህራችሁን ጠይቁ። መጻህፍትም አንብቡ። ባገኛችሁት መረጃ ላይም በቡድን ተወያዩ። ከዚያም በቡድን የደረሳችሁበትን ሀሳብ በተወካያችሁ አማካኝነት በቃል አቅርቡ።

## ክፍለጊዜ፡ አራት

### ተግባር አራት

በተግባር ሶስት ስለ ‹‹ሴቶች እና የስራ ዕድል›› የስነ ዜጋ መምህራችሁን ጠይቃችሁ ወይም የተለያዩ መጻኅፍትን አንብባችሁ ያገኛችሁት ሀሳብና በዚህ ጉዳይ በአካባቢያችሁ ያለውን እውነታ በማነጻጸር ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ቀጥሎ የቀረቡት ምንባብ እና መልመጃዎች አንብባችሁ እንድትረዱ የሚያግዙ ናቸው። በመሆኑም ምንባቡን በትኩረት በማንበብ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ።

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ የቀረበውን ጽሁፍ ከማንበባችሁ በፊት በጥንድ ተወያዩና በቃል መልሱ።

1. አረጋውያን የሚባሉት በየትኛው የዕድሜ ክልል የሚገኑ ሰዎች ናቸው?
2. አረጋውያንን ለማክበር ምን ምን ተግባራትን ትፈጽማላችሁ?
3. አረጋውያንን ማክበር ጠቀሜታው ምንድን ነው?

## አረጋውያንን ማክበር

አረጋውያን በወጣትነትና **በጎልማሳነት** ዕድሜያቸው ለሀገራቸውና ለወገናቸው ጠቃሚ ተግባራትን ያከናወኑና ሰፊ የህይወት ልምድ ያካበቱ **በእድሜ የገፉ** ሰዎች ናቸው። በባህላችን መሠረት ታናናሾች ታላላቆችን ማክበር አለብን። በዕድሜ የሚበልጡንን ሰዎች በትህትና ማናገር፣ መቀበል፣ ማስተናገድና ቅድሚያ መስጠት ይጠበቅብናል። በመሆኑም በአካባቢያችን ያሉ አረጋውያን፣ አያቶች፣ አባቶች፣ እናቶች ሁሉ ሊከበሩ ይገባቸዋል። **እነሱን** ማክበር ማለት ራሳችንንም ማክበር ማለት ነው።

አረጋውያን ቀድመው ሁኔታዎችን ባያመቻቹልን ኖሮ የእኛም ህልውና አይታሰብም ነበር። እነሱን በማክበራችን በብዙ መንገድ ተጠቃሚ እንሆናለን። **ተዝቆ ከማያልቀው** የህይወት ልምዳቸው ብዙ እንማራለን።

ከነሱ የምናገኘው ትምህርት ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በማንበብ ከምናገኘው ዕውቀት ያልተናነሰ ነው። ስለሆነም አረጋውያን ጠቃሚ የማኅበረሰቡ የዕውቀት ምንጮች መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። ታዲያ እነዚህ **ዕንቁ** የዕድሜ ባለፀጎች መከበር ሲያንሳቸው ነው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከላይ ካነበባችሁት አንጻር የአጠቃላይ የምንባቡ ዓላማ ምንድን ነው ብላችሁ ትገምታላችሁ?
2. አረጋውያንን ማክበር ማለት ምን ማለት ነው?
3. አረጋውያንን ማክበር ምን ጥቅም የሚያስገኝ ይመስላችኋል?

አረጋውያንን የምናከብረው እንዲሁ መከበር ስላለባቸው ብቻ ሳይሆን፣ እነሱን በማክበር ማግኘት የሚገባውን በርካታ ቁምነገሮች ስላሉና **የሞራል** ግዴታም ስላለብን ነው። ይህም የሚጠቅመው አረጋውያኑን ብቻ ሳይሆን እኛንም ጭምር ነው። ስለዚህ የምንፈልጋቸውን ጠቃሚ ዕውቀቶችና ልምዶች ለመቅሰም አረጋውያን በሚናገሩበት ወቅት በጥሞና መከታተልና ማዳመጥ ይኖርብናል። ካዳመጥናቸው፣ በህይወት ዘመናቸው **ያካበቱትን** ዕውቀትና ልምድ ሳይሰስቱ ያካፍሉናል። በዚህም በብዙው ተጠቃሚ እንሆናለን።
አረጋውያን በኑሯቸው የተለያዩ የህይወት **ውጣውረዶችን** አልፈዋል። ደስታና መከራ፣ ማግኘትና ማጣት **ተፈራርቀውባቸዋል**። ሁሉንም የህይወት ውጣውረዶች በዘዴና በብልሃት አልፈው ዛሬ ካሉበት ደረጃ ለመድረስ በቅተዋል። ይህ ልምዳቸው የሚያጋጥሙንን ችግሮች በቀላሉ ተቋቁመን ለማለፍ አቅም ይፈጥርልናል። አረጋውያን ልምዳቸውን የሚገልፁት በፈሊጣዊ ንግግር፣ በተረትና በምሳሌ ነው። በሚተርኩበት ጊዜ በርጋታ ካዳመጥናቸው

ያልተፈቱና **ያልተመነዘሩ** ቁምነገሮችን ያሳውቁናል። ትኩረት ሰጥተን ካዳመጥናቸውና ከተከታተልናቸው ተፈላጊና **"ጠቃሚ ሰው ነኝ"** የሚል ስሜት በውስጣቸው ይፈጠራል፤ ስለእኛ የወደፊት ተስፋ ርግጠኛ ይሆናሉ። ስለሆነም ከልምዳቸው ለእኛ ይጠቅማል ያሉትን ሁሉ ሳይደብቁ ይገልፁልናል።

በተጨማሪም አረጋውያን በአካባቢያችን ካሉ በመንገድ ላይ ቅድሚያ በመስጠት ኮፍያችንን ከራሳችን ላይ በማንሳት፣ ከአንገታችን ጎንበስ በማለት ሰላምታ መስጠት፣ ከመቀመጫችን በመነሳት አክብሮታችንን መግለፅ አለብን። ይህን ስናደርግላቸው በውስጣቸው ደስታ ይፈጠራል፤ በራስ የመተማመን ስሜታቸው ከፍ ይላል። ከዚህ ላይ በማኅበረሰባችን **"የሚያድግ ልጅ አይጥላህ፣ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ"** የሚለውን አባባል ማስታወስ ያስፈልጋል። ትልቅ ቁምነገር አለው።

በአጠቃላይ አረጋውያንን ማክበር የዕለትተዕለት ተግባራችን ሊሆን ይገባል። ካለፉ በኋላ ልናገኛቸው የማንችላቸውን የዕውቀት ክምችቶች ለወደፊቱ ትውልድ ማስተላለፍ የምንችለው ተገቢውን ክብር በመስጠት ስንከባከባቸውና ከነሱ መማር ስንችል ነው።

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ያነበባችሁትን ጽሁፍ መሰረት አድርጋችሁ በጽሁፍ መልሱ።**

1. አረጋውያን ማለት ምን ማለት ነው?
2. በዕድሜ ከእኛ የሚበልጡ ሰዎችን በምን በምን አክብሮታችንን ልንገልጽ እንችላለን?

3. በአንቀጽ አንድ "እነሱን" የሚለው ተውላጠ ስም ማንን ይወክላል?
4. በአንቀጽ አምስት "**ይህን** ስናደርግላቸው..."በሚለው "**ይህን**" የሚለው ምንን ያመለክታል?
5. አረጋውያንን በማክበር አክባሪው እና ተከባሪው ምን ሊያተርፉ ይችላሉ?
6. “የሚያድግ ልጅ አይጥላህ፣ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ” የሚለውን አባባል ምን ይገልጻል?
7. ከአረጋውያን ልናገኛቸው የምንችላቸው የእውቀት ክምችት እንዳያመልጠን ምን ማድረግ አለብን?
8. አረጋውያን ልምዶቻቸውን በምን መንገድ ይገልጻሉ?

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር አምስት

**ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ማስታወሻ እየያዛችሁ በቡድን ተወያዩ። የያዛችሁትን ማስታወሻ በአንቀጽ አደራጅታችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ።**

1. ምንባቡ ስለአረጋውያን መከበር ያነሳቸውን ሀሳቦች እንዴት ትመለከቱታላችሁ? ተወያዩበት።
2. አረጋውያንን ለማክበር ምን ምን ተግባራትን ትፈጽማላችሁ?
3. ‹‹ሁሉንም የህይወት ውጣውረዶች በዘዴና በብልሃት አልፈው ዛሬ ካሉበት ደረጃ ለመድረስ በቅተዋል›› በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ ዘዴ እና ብልሃቶቹ ምን ሊሆኑ ይችላሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ? ተወያዩበት።

## ተግባር ስድስት

**ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ የተጓደሉትን ሀሳቦች የቀረበውን ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።**




**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ከዚህ ቀጥሎ ከምንባብ የወጡ ቃላትን እና ጥምርቃልን የተመለከተ መልመጃዎች ስለቀረቡ በትዕዛዛቱ መሰረት ጥያቄዎቹን ስሩ።

### መልመጃ ሰስት

ከዚህ በታች በዝርዝር የቀረቡ ቃላት አውዳዊ ፍቺን ለማግኘት ከቡድን አባላት ጋር በመተባበር ምንባቡን በድጋሚ አንብቡ፤ ከዚያም ቃላቱን ከምንባቡ ውጪ በሆኑ ሌላ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በማስገባት ተጠቀሟቸው።

| | | |
|---|---|---|
| በኅልማሳነት | ያካበቱት | ዕንቁ |
| በእድሜ የገፉ | ውጣውረዶች | ያልተመነዘሩ |
| ተዝቆ ከማያልቀው | ተፈራርቀውባቸዋል | ሞራል |

**ማስታወሻ**

ጥምርቃል፡ ከአንድ በላይ ቃላት ተቀናጅተው አንድ ትርጉም ወይም ፍቺ የሚወክሉበት ነው። ጥምርቃል እንደአንድ ቃል የሚቆጠር ሲሆን፣ የሚኖረው ፍቺም የተጣመሩት ቃላት በተናጠል ካላቸው ፍቺ የተለየ ነው።

ምሳሌ፡- ቁም + ሳጥን ⟶ ቁምሳጥን (የልብስ ማስቀመጫ)

ልብ + ወለድ ⟶ ልቦለድ (የፈጠራ ጽሁፍ)

ጥምርቃል እንደሌሎቹ ቃላት ሁሉ ለተለያዩ እርባታዎች ቅርጹን ይቀያይራል። ለምሳሌ፡ ቁምሳጥን ቁምሳጥኖች፣ ቁምሳጥኑ እየተባለ ጥምር ቃልን ማርባት ይቻላል።

## መልመጃ አራት

1. ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ጥምር ቃል የሆኑትን መርጣችሁ ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| የእንጨት አልጋ | ጥቁር ሰሌዳ | አሳት እራት | እርሶ አደር |
| ጥቅል ጎመን | ትምህርት ቤት | ሆድና ጀርባ | ብርድ ልብስ |
| ጥሩ ሰው | መልካም ሀሳብ | ሽክላ ሰሪ | ውሀ ወለድ |
| ጸረኤድስ | ብረት ድስት | ኪነጥበብ | አዋቂ ልጅ |

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## መልመጃ አምስት

1. በሳጥን ውስጥ ባሉት ጥምርቃሎች ዓረፍተነገር መስርቱ።
2. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ አምስት ጥምር ቃላትን በመጠቀም ሀሳባችሁን ግለጹ።

   ምሳሌ፡-

   እናቴ ገበያ ሄዳ ብረት ምጣድ ገዛች።

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

**ከዚህ በታች የመጻፍ ክህሎትን የሚያዳብሩ የተለያዩ ተግባራት ቀርበዋል። ተግባራቱን በትዕዛዛቱ መሰረት በትጋት ስሩ።**

### ተግባር ሰባት

"አረጋውያንን ማክበር" በሚል ርዕስ በቀረበ ጽሁፍ የአንቀጾችን ፍሬሀሳቦች በአስተዋጽኦ መልክ ጻፉ። የጻፋችሁትን የአንቀጾችን ፍሬሀሳቦች መነሻ አድርጋችሁ የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ የሚያሳይ አንቀጽ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ። ስትጽፉም ለአንቀጻችሁ ዋና ዓረፍተነገር መስርቱ።

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

### ተግባር ስምንት

ሀ. በአካባቢያችሁ ወጣቶች አረጋውያንን በማክበራቸው ያገኙትን ጥቅም ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን መረጃ በአንድ አንቀጽ አደራጅታችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ለ. በአካባቢችሁ ወጣቶች አረጋውያንን እንዴት እንደሚያከብሩ ገምግማችሁ አራት አንቀጾች ያሉት ገምጋሚ ድርሰት ጻፉ። ስትጽፉም በምዕራፍ ሁለት በክፍለ ጊዜ ዘጠኝ የተዘረዘሩትን የድርሰት መጻፊያ መንገዶች ተከተሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ክፍል ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን የተመለከተ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። ማስታወሻውንና ምሳሌውን መሰረት አድርጋችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሰረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

**ነጠላ ስም፡** በቁጥር አንድ የሆነ ስም ነው።

**ብዙ ስም፡** በቁጥር ከአንድ በላይ የሆነ ስም ነው።

ምሳሌ ፡

| ነጠላ ቁጥር ስም | ብዙ ቁጥር ስም |
|---|---|
| ተማሪ | ተማሪዎች |
| ወላጅ | ወላጆች |
| ሰው | ሰዎች |
| ቤት | ቤቶች |
| መምህር | መምህራን |
| ቃል | ቃላት |
| አንበሳ | አናብስት |

## መልመጃ ስድስት

ከዚህ በታች የቀረቡላችሁን ቃላት ነጠላና ብዙ ቁጥር በማለት ለይታችሁ ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀገራት | ምርት | ነጋዴዎች | አናብርት |
| ክፍሎች | መሬት | ዶሮች | አእዋፍ |
| እንስሳት | ጥያቄዎች | ጠረጴዛ | ባለሞያዎች |
| ምግቦች | ሰዎች | ወረቀቶች | ልብስ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## መልመጃ ሰባት

1. ከዚህ በታች የሚገኙትን ነጠላ ቁጥር ስሞች ወደ ብዙ ቁጥር ስም ከለወጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀረግ | መንግስት | ልብስ | ደብተር |
| ፈተና | ቃል | አድባር | |
| ጨዋታ | ፈረስ | ቤተሰብ | |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

2. አስር ነጠላ ቁጥር ቃላትን ለይታችሁ ወደ ብዙ ቁጥር ከቀየራችሁ በኋላ ዐረፍተነገር መስርቱባቸው።

ለምሳሌ፡- ደን ⟶ ደኖች

ከአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ወዲህ በሀገራችን ደኖች እያገገሙ ይገኛሉ።

# ምዕራፍ አራት

## አጭር ልቦለድ

### የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- አዳምጣችሁ ተመሳሳይ ታሪኮችን ትናገራላችሁ፤
- የአጭር ልቦለድ ጽንሰ ሀሳብን ታብራራላችሁ፤
- በጽሁፋዊ ቅርፅ ውስጥ አውዳዊ እና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፤
- የሀረጋት ዓይነቶችን ትለያላችሁ፡፡

ክፍለጊዜ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት መምህራችሁ "አፋልጉኝ" በሚል ርዕስ የቀረበ አጭር ልቦለድ ያነቡላችኋል። አጭር ልቦለዱን መሰረት አድርገው የወጡ የተለያዩ ጥያቄዎችም ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን በትዕዛዛቸው እና መምህራችሁ በሚያቀርቡላችሁ ገለጻ መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## አፋልጉኝ

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን አጭር ልቦለድ ከማዳመጣችሁ በፊት ተወያዩና ለመምህራችሁ ተናገሩ።

1. አጭር ልቦለድ ምን አይነት ልቦለድ ነው?

2. አጭር ልቦለድ አንብባችሁ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ አዎ ከሆነ የአጭር ልቦለዱን ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በአጭሩ ንገሩ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች የቀረቡ ጥያቄዎችን የሚነበብላችሁን ጽሁፍ እያዳመጣችሁ መልሶቹን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉ።**

1. ባዳመጣችሁት አጭር ልቦለድ ውስጥ ገጸባህርያት እነማን ናቸው?
2. ታሪኩ የተፈጸመው በምን አይነት የአየር ፀባይ አካባቢ ነው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት አጭር ልቦለድ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. የአጭር ልቦለዱ ታሪክ የተፈጸመው የት ነው?
2. ታረኩ የተፈጸመው መቼ ነው?
3. መንገደኛው ምን ምን ተግባራትን ፈጸመ?
4. በቆሎ ሻጯ ዕድሜዋ በየትኛው ህብረተሰብ ክፍል የምትመደብ ናት?
5. "ወርሃ ሰኔ" ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. መንገደኛው በቆሎ እሸቱን ሳይገዛ እንዳይሄድ ያደረገው ምንድን ነው?
7. ሴትየዋ "የመጨረሻውን ዕድሜህን የተሻለ ያድርግልህ" ስትል ምን ማለቷ ነው?
8. ሴትየዋ "በኔ ይሁንብህ።" ብላ መንገደኛውን የተማጸነችው ለምንድን ነው?

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

### ተግባር አንድ

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ኑሯቸውን ለማሻሻል ጥረት ለሚያደርጉ ዜጎች ምን አይነት ምክር ትመክራላችሁ? በቡድን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለመምህራችሁ በጽሁፍ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ ሶስት

### ተግባር ሁለት

ያዳመጣችሁትን አጭር ልቦለድ ዋና ዋና ታሪኮችን ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ መልሳችሁ ተናገሩ።

ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክፍል የተለያዩ ተግባራትና መልመጃዎች ቀርበላችኋል። ተግባራቱንና መልመጃዎቹን በትዕዛዛቸው መሰረት በትኩረት ስሩ።

### ተግባር ሶስት

እንደ ገገር እና ሻጭ ለመተወን የሚያስችላችሁ ቃለምልልስ ካዘጋጃችሁ በኋላ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተለማመዱ። ከዚያም የተለማመዳችሁትን ምልልስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተውኑ።

### ክፍለጊዜ፡ አምስት

**ተግባር አራት**

መምህራችሁ የሚጠቁሟችሁን አንድ አጭር ልቦለድ አንብባችሁ በመምጣት ታሪኩን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳጥራችሁ አቅርቡ። በታሪኩ ውስጥ ያሉትን የአጭር ልቦለዱን ገጸባህርያት ማንነት እና በልቦለዱ ውስጥ የተላበሱትን ባህርይ ግለጹ።

### ክፍለጊዜ፡ ስድስት

**ተግባር አምስት**

ከዚህ በታች የቀረበውን አጭር ታሪክ በቡድናችሁ ደጋግማችሁ ካነበባችሁት በኋላ ታሪኩን በራሳችሁ አገላለጽ መልሳችሁ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ለበጎ

አንድ ሰው ነበረ፣ በባህር ብቻውን በመርከብ እየተጓዘ በማዕበል ተመታና ጀልባው ተሰባብሮ ሰመጠበት። ሰውዬው እንደምንም እራሱን አድኖ አንድ ደሴት ላይ ያርፍና ጎጆ ነገር ሰርቶ ለቀናት ለብቻው እዛች ደሴት ላይ ኖረ። ምግቡንም አሳ እያጠመደ ብዙ ቀናትን አሳለፈ።፡አንድ ቀን አሳ ሊያጠምድ ወደ ባህሩ እየሄደ በመሀል እዚያው በህር ላይ ጪስ ይሸተዋል። ዞር ብሎ ሲመለከት ያቺ ጎጆው እየነደደች ያያታል። እየሮጠ ቢመለስም ጎጆዋን ሊያድናት አልቻለም። ለካ አሳ ለማብሰል ያቀጣጠለው እሳት ተያይዞ ጎጆውን እንድዷታል። ሰውዬውም አለቀሰ፣ ፈጣሪውን ወቀሰ፣ እንዴት እዚህ

ባህር ላይ ለብቻዬ ጥለኸኝ፣ ከቤተሰቦቼ ነጥለኸኝ ስታበቃ በስንት ልፋት የሰራኋትን ጎጆ ታቃጥልብኛለህ በማለት አምርሮ ተናገረ።
ከደቂቃዎች በኋላ አንድ ድምጽ ሰማ። ወደ ድምጹ ፊቱን ሲያዞርም አንድ ትልቅ መርከብ ወደ እሱ ሲመጣ ተመለከተ።፤ ከመርከቡ ውስጥም ሰዎች ወጥተው ሰውዬው ወዳለበት ቦታ መጡ። እሱም ወደ እዚህ ባህር ሰው ይመጣል ብዬ በፍጹም አልጠበቅሁም፣ እናንተ እንዴት ልትመጡ ቻላችሁ በማለት ጠየቃቸው። መርከበኞቹም በወዲያኛው የባህር ክፍል እየሄድን ሳለ ጪስ አይተን ልንመጣ ቻልን ብለው መለሱለት። ሰውዬውም ቀደም ሲል ፈጣሪውን በማማረሩ እየተጸጸተ ነገርግን ከአደጋ በመትረፉ እየተደሰተ ከመጡት ሰዎች ጋር በመርከቡ ተሳፍሮ ወደሚናፍቃቸው ቤተሰቦቹ ሄደ።

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

### ተግባር ስድስት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው አጭር ታሪክ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. ለ‹‹በጎ›› የሚለው ታሪክን አጠቃላይ መልእክት በአጭሩ ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።
2. ለ‹‹በጎ›› ከሚለው ታሪክ ጋር የሚመሳሰል ገጠመኝ ካላችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሩ።

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

ለ. ከዚህ በታች ስለአጭር ልቦለድ ምንነትና ባህርያት የተመለከተ አጭር ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። ማስታወሻውን በማንበብ በጥንድ ከተወያያችሁ በኋላ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልሱ።

## ማስታወሻ

### የአጭር ልቦለድ ምንነትና ባህርያት

ስለአጭር ልቦለድ ከተሰጡት ብያኔዎች መካከል የሚከተሉት ዋነኞቹ ናቸው። የመጀመሪያው አጭር ልቦለድ በዝርውና በጠበቀ አንድነት የተጻፈ፣ አብዛኛውን ጊዜ ከአስር ሺ ቃላት የማይበልጥና የፈጠራ ባህርያትን የተላበሰ ስራ ነው። ከአንድ ችግር የሚጋፈጥ፣ ስለችግሩም ውሳኔ መስጠት የሚገባው፣ ከገባባቸው አጋጣሚዎች አኳያ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ድርጊቶች የሚፈጽምን አንድ ገጸባህሪ ተውኔታዊ በሆነ አቀራረብ የሚያሣይ ነው። የሁለተኛው አጭር ልቦለድ ብያኔ ከአሰር ሺ ቃላት በላይ የማይዝ፣ አንድ ዋነኛ ግብ ለማምጣት የተዋቀረና ተውኔታዊነት የሚታይበት አጠር ያለ ትረካ ነው።

አጭር ልቦለድ በአንድ ቅጽበት በአንድ ነጠላ ሁነት ውስጥ በሚያልፍ አንድ ገጸባህሪ ላይ ያተኩራል። በአሜሪካዊው ኤድጋር አላን ፖ መቀመሩ የሚነገርለት ዋነኛው የአጭር ልቦለድ ባህሪ ነጠላ ውጤት ነው። ነጠላ ውጤት ሁሉም የአጭር ልቦለድ አካላት ተሳስረው ወደ አንድ ዋነኛ ትኩረት የሚፈስሱበትን ደራሲው በአንባቢው አእምሮ ተቀርጾ እንዲቀር የሚፈልገው አንድ ኪነጥበባዊ ግብ ነው። በአሜሪካዊው ኤድጋር አላን ፖ መቀመሩ የሚነገርለት ዋነኛው የአጭር ልቦለድ ባህሪ ነጠላ ውጤት ነው። ነጠላ ውጤት ሁሉም የአጭር ልቦለድ አካላት ተሳስረው ወደ አንድ ዋነኛ ትኩረት የሚፈስሱበትን ደራሲው በአንባቢው አእምሮ ተቀርጾ እንዲቀር የሚፈልገው አንድ ኪነጥበባዊ ግብ ነው።

1. **አጭር ልቦለድን የማይገልጸው ሀሳብ የትኛው ነው?**

ሀ. ሰብሰብ ያለ ነው። ሐ. እጥር ምጥን ያለ ነው።

ለ. ድርጊታዊነት የሚታይበት ነው። መ. ባለብዙ ታሪክ ነው።

3. በኤድጋር አላን ፖ መሰረት የአጭር ልቦለድ ባህሪ የትኛው ነው?

   ሀ. ጥድፊያ ለ. ነጠላ ውጤት ሐ. ቁጥብነት መ. ተውኔታዊነት

4. አጭር ልቦለድ ስንት ዋና ገጸባህሪያት አለው?

   ሀ. 1 ለ. 2 ሐ. 3 መ. 4

5. አጭር ልቦለድ ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች የሚለይበት ነጥብ የትኛው ነው?

   ሀ. ፈጣንነት የሚታይበት መሆኑ ሐ. በግጥም ቅርጽ የሚቀርብ መሆኑ

   ለ. ከአስር ሺ ቃላት በላይ ስለሚጻፍ መ. በርካታ ገጸባህርያት በመያዝ

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ከዚህ በታች "ክቡር ውርስ" በሚል ርዕስ አጭር ልቦለድ ቀርቦላችኋል። አጭር ልቦለዱን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ የቅድመ፣ የጊዜ እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን በትዕዛዛቸው መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

### የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. አጭር ልብ ወለድ ምንድን ነው?
2. የአጭር ልቦለድ አላባውያን የሚባሉት እነማን ናቸው?

## ክቡር ውርስ

መምህሩ ለልጆቹ የመጨረሻ ቃላቸውን በአሳዛኝ ሁኔታ እየተናዘዙ ናቸው። ልጆቼ ሆይ! በደንብ አድርጋችሁ አድምጡኝ። መልካም የሆነውን ብቻ ስሩ… ንግግራችሁ መልካም፣ ድርጊታችሁ መልካም፣ ሃሳባችሁም መልካም ይሁን። እኔ የማወርሳችሁ ትልቅ ሃብት መልካም የሆነውን ስሜን ብቻ ነው። ከማንም

እና ከምንም ነገር አብልጩ የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ… በእኔ ከእናንተ መለየት አትከፉ። በእኔ የተነሳ ‹የሌባ ልጅ› የሚላችሁ ማንም ስለሌለ ኩሩ። በእኔ ክፉ ድርጊት የተነሳ… እናንተን የሚያሳድድ ባለመኖሩ ደስ ይበላችሁ። እኔ ከእናንተ ጋር በማልኖርበት ጊዜ… በነፃነት መኖር እንድትችሉ… የቃል፣ የቁስና የገንዘብ ዕዳ ትልቅ ሸክም በእናንተ ትከሻ ላይ ባለማኖሬ… እፎይታ ይሰማችሁ። ልጆቼ ሆይ! በዚህች የስንብት ሰዓት እና… በአሁኗ የመጨረሻ እስትንፋስ መተንፈሻ ጊዜዬ… ለእናንተ የማወርሰው… በብዙ መከራዎች መሃል ፀንቼ… በሚያማልሉ ነገሮች በተሞሉ ጊዜያት ቁጥብ ሆኜ የግል ፍላጎቴን ገትቼ… በታታሪነት ያቆየሁት… በመልካም ስራ ያፈራሁትን… መልካሙ ስሜን ብቻ ነው። ልጆቼ ሆይ! ስለዕድላችሁ አትከፉ፤ ደስ ይበላችሁ እንጂ።… ከከበሩ ውርሶች ሁሉ የከበረ ፤ … ከተወደዱ ቁሶች ሁሉ የተወደደ…፣ ከሁሉም የከበረ ውርስ… መልካም የሆነ ስም ብቻ ነውና።… መልካሙን ስሜ ውረሱኝ! እናንተም መልካሞች ሁኑ… አደራ… አደራ…! ይላሉ ድምጻቸው እየተቆራረጠና የቀራቸውን እንጥፍጣፊ ጉልበት ለንግግራቸው እየተጠቀሙ።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የአጭር ልቦለዱ ዋና ገጸባህርይ ማን ናቸው?
2. ከውርሶች ሁሉ የተከበረ ውርስ ምንድን ነው?

መምህሩ ህይወታቸውን ሊነጥቅ ሲታገላቸው ለነበረው ሞት ለሚባለው ክፉ ዕጣ፤ የለሊቱ አጋማሽ ሊደርስ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ እጅ ሰጡ። ወዳጆቻቸውና ጎረቤቶቻቸውም ስለሚወድዷቸው ለእኚህ ምስኪን መምህር እንባቸውን አፈሰሱ፤ አለቀሱም። የእኚህ መምህር ቀብርም በቀጣዩ ቀን ተፈፀመ። በሚኖሩበት ጊዜ ‹አሉ› የተባሉ ህይወታቸው ባለፈ ሰዓት ‹ነበሩ› ተባለ።

የመምህሩ ልጆች ደግሞ አባታቸው ህይወታቸው ካለፈ በኋላ፤ ስለአባታቸው መልካም ስራ እና በጎ አስተዋፅኦ ፤ በከተማዋ ሰዎች የሚከበሩ እና የተወደዱ ሊሆኑ ቻሉ። አባታቸው መልካም ሰው ስለነበሩ ብቻ ፤ ልጆቹ በሰሩትም ይሁን ባልሰሩትም ስራ በከተማዋ ሰዎች ስማቸው ዘወትር በበጎ ይነሳል። የሰው ልጅም ውዳሴን የሚወድ በመሆኑ ፤ እነዚህም ልጆች ስማቸው በደግ በደጉ በመነሳቱ፤ ደስታ የማይለያቸው ሰዎች ለመሆን በቁ። ደስተኛ ሰዎች ከሌላው ሰው በበለጠ በህይወታቸው ስኬታማ የመሆን ጥሩ ዕድል አላቸው። እነዚህም ልጆች ደስተኛ ሰዎች በመሆናቸው ምክንያት የሚኖሩት ኑሮ የደመቀ፤ የሚሰሩት ስራ የሰመረ፤ እንዲሁም በስኬት ላይ ስኬት መጨመር ልማዳቸው የሆነ ጠንካራ ስብእናን የገነቡ በራሳቸው የሚተማመኑ እና የሚኮሩ ሰዎች ለመሆን በቁ።

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ባነበባችሁት አጭር ልቦለድ መሠረት በጽሁፍ መልሱ።**

1. ባነበባችሁት አጭር ልቦለድ ታሪኩ የተፈጸመው የት ነው?
2. "እናንተን የሚያሳድድ ባለመኖሩ ደስ ይበላችሁ።"ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. መምህሩ ለልጆቻቸው በሚናዘዙበት ወቅት ምን አይነት ሁኔታ ላይ ነበሩ?
4. መምህሩ መልካም ስማቸውን ያፈሩት እንዴት ነበር?
5. ጎረቤቶቻቸውና ወዳጆቻቸው ለመምህሩ ለምን አለቀሱ?

6. "ደስተኛ ሰዎች ከሌላው ሰው በበለጠ በህይወታቸው ስኬታማ የመሆን ጥሩ ዕድል አላቸው።" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ክፍለጊዜ፡ አስር

**ተግባር ሰባት**

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ። ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለክፍል ተማሪዎች በቃል አቅርቡ።**

1. የአጭር ልቦለዱ ፍሬነገር ምንድን ነው?
2. የልጆቹ የወደፊት ህይወት ምን አይነት ሆኖ ተገኘ?
3. የዋናውን ገጸባህርይ ባህርይ እንዴት ትገልጹታላችሁ?

ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## መልመጃ ሁለት

**ሀ. ምሳሌውን መሰረት አድርጋችሁ ያነበባችሁትን አጭር ልቦለድ ዋና ዋና ድርጊቶች/ታሪኮች/ ቅደምተከተላቸውን ጠብቃችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፤**

ድርጊት አንድ፣ መምህሩ ለልጆቹ ተናዘዙ።

ድርጊት ሁለት፣ ___

ድርጊት ሶስት፣ ___

ድርጊት አራት፣ ___

ድርጊት አምስት፣___

ድርጊት ስድስት፣___

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

ለ. ቀጥሎ የቀረቡት አረፍተነገሮች ከአጭር ልቦለዱ የወጡ ናቸው። የአረፍተነገሮቹን ፍቺ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

1. ድምጻቸው እየተቆራረጠና የቀራቸውን እንጥፍጣፊ ጉልበት ለንግግራቸው እየተጠቀሙ...
2. የለሊቱ አጋማሽ ሊደርስ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩት እጅ ሰጡ።
3. በከተማዋ ሰዎች ስማቸው ዘወትር በበጎ ይነሳል።
4. የሰው ልጅም ውዳሴን የሚወድ ነው።
5. እነዚህም ልጆች ስማቸው በደግ በደጉ በመነሳቱ፣ ደስታ የማይለያቸው ሰዎች ለመሆን በቁ።
6. ጠንካራ ስብእናን የገነቡ በራሳቸው የሚተማመኑ እና የሚከሩ ሰዎች ለመሆን በቁ።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ከዚህ በታች ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እንድትሰጡ የሚጠይቅ እንዲሁም ተዘውታሪ ላልሆኑ ቃላት ማስታወሻና ለቃላቱ መዝገበቃላዊ ፍቺ ስጡ የሚል መልመጃ ቀርቦላችኋል። በየመልመጃዎቹ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

### መልመጃ አራት

ሀ. የሚከተሉት አረፍተነገሮች ካዳመጣችሁት አጭር ልቦለድ የወጡ ናቸው። በአረፍተነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ትርጉም ስጡ።

1. "ሽለፈቱን <u>አትግለጠው</u> እንጂ አይደርቅም።"

2. ደመናው ሊዘረግፈው የቋጠረው ዝናብ በእርግጥም ህዋውን አክብዶታል።
3. የተጠቀለለውን የበቆሎ እሸት ለመምረጥ ሸብረክ ብዬ ቁጭ እያልኩ።
4. ከመብራት ምሰሶ ጥግ በቆሎ እሸት የሚሸጡት ሴት በዕድሜ የገፉ አዛውንት መሆናቸውን ልብ አላልሁም ነበር።
5. የሴትዮዋ "እባክህን ግዛኝ" የሚለው ተማፅኖ በቆሎ እሸቱን ሳልገዛቸው እንዳልሄድ ቀፍድዶ አሰረኝ።
6. ይኸን ባለግርማ ደመና እንዲህ እንደተራራ የቆለለው አምላክ ይርዳህ።

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት በመዝገበ ቃል ውስጥ ያላቸውን ፍቺ ፈልጋችሁ ጻፉ።**

| | |
|---|---|
| 1. ውርስ | 6. በጎ |
| 2. ነጻነት | 7. ዕዳ |
| 3. ሰመረ | 8. ክቡር |
| 4. ቁጥብ | 9. ምስኪን |
| 5. እፎይታ | 10. ውዳሴ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

## መልመጃ አምስት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡት አረፍተነገሮች ካነበባችሁት አጭር ልቦለድ የወጡ ናቸው። በአረፍተነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

1. ለእናንተ የማወርሰው... በብዙ መከራዎች መሃል ፀንቼ...
2. በሚያማልሉ ነገሮች በተሞሉ ጊዜያት ቁጥብ ሆኜ
3. የግል ፍላጎቴን ገትቼ... በታታሪነት ያቆየሁት... በመልካም ስራ ያፈራሁትን... መልካሙ ስሜን ብቻ ነው።

4. በስኬት ላይ ስኬት መጨመር <u>ልማዳቸው</u> የሆነ
5. ጠንካራ ስብእናን የገነቡ በራሳቸው የሚተማመኑ እና የሚኮሩ ሰዎች ለመሆን <u>በቁ</u>።
6. የቁስና የገንዘብ ዕዳ ትልቅ ሸክም በእናንተ <u>ትከሻ</u> ላይ ባለማኖሬ... እፎይታ ይሰማችሁ።
7. የለሊቱ አጋማሽ ሊደርስ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ <u>እጅ ሰጡ</u>።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

**ማስታወሻ**

**ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት**

ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት የምንላቸው በእለት ተእለት ንግግራችንና በጽሁፍ ውስጥ ተግባር ላይ የማይውሉ ቃላት ናቸው። እነዚህ ቃላት በተወሰኑ ሰዎች ዘንድ ብቻ የሚታወቁና በአብዛኛው ከሙያ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሀሳቦችን ለመግለጽ ሲባል ጥቅም ላይ ይውላሉ።

ለምሳሌ፡ ማሳ፣ ቀንበር፣ ጎለጎለ፣ እርቦ

ዋርድ፣ ኦፒዲ፣ ሪከቨሪ፣ ዲስፔንሰሪ

መጀመሪያ ላይ ያሉት ቃላት በእርሻ አካባቢ ያሉ ሰዎች ብቻ የሚጠቀሟቸው ሲሆኑ ሁለተኛ ላይ ያሉት ቃላት ደግሞ በህክምና ሙያ አካባቢ ያሉ ሰዎች የሚገለገሉባቸው ናቸው።

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ፡**

| | | |
|---|---|---|
| 1. እንዝርት | 3. ምጣኔ ሀብት | 5. ባሩድ |
| 2. ድግር | 4. ልሳን | 6. ድሪ ገጽ |

ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

ከዚህ በታች የመሸጋገሪያ ቃላትን የተመለከተ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። መምህራችሁ የሚሰጧችሁን ማብራሪያና የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብ መልመጃዎች በትዕዛዛቸው መሰረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

***መሸጋገሪያ ቃላት*** በጽሁፍ ውስጥ ሀሳቦች ተያያዥነትና ተከታታይነት እንዲኖራቸው፣ ተጨማሪና ተደጋጋፊ እንዲሆኑ ለማስቻል ቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተነገሮችን የሚያያይዙ ናቸው። እንዲሁም የሚቃረኑ ሀሳቦችን በንጽጽር በማቅረብ ለማያያዝ የሚያገለግሉ ናቸው።

***ለምሳሌ፡-***

*ደበሌ እና ተስፋዬ ከትምህርት ቤት መጡ።*

*አያና ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል፤ይሁን እንጂ ከሱ የተሻለ ውጤት ያመጡም አሉ።*

*ሰዎቹ የተቸገሩ ወገኖችን ከመርዳታቸውም በላይ በአካባቢው ልማት ላይ በመሳተፍም ይታወቃሉ።*

ከላይ የተሰመረባቸው መሸጋገሪያዎች ናቸው። እነዚህ መሸጋገሪያዎች ቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተነገሮችን በማያያዝ አረፍተነገሮቹ ሙሉ እንዲሆኑ አድርገዋል።

## መልመጃ ስድስት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን የመሸጋገሪያ ቃላት ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ በተጓደሉት ቦታዎች በማሟላት ጻፉ።**

| | |
|---|---|
| እንዲሁም | በተያያዘ |
| በአንጻሩ | ስለዚህ |
| ከዚያም | በመሆኑም |

1. ጠዋት ተነስቼ ፊቴን እታጠባለሁ፣ ___________ ቁርሴን እበላለሁ።
2. የሚያጠና ተማሪ ጥሩ ውጤት ያስመዘግባል፣___________ የማያጠና ተማሪ ዝቅተኛ ውጤት ይኖረዋል።
3. በየአመቱ ከሚወድመው ደን ጋር ___________ የካርቦን ልቀቱ በጣም ይጨምራል።
4. እንግዶቹ ስብሰባው ላይ ለመገኘት እየመጡ ናቸው፣___________ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅብናል።
5. እያንዳንዱ ግለሰብ አካባቢውን በማጽዳት የራሱን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል። ___________ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የበኩላቸውን ማበርከት አለባቸው።
6. ሴቶች የሀገር ዋልታ ናቸው፣___________ ሁሉም ሴቶች የትምህርት ዕድል ማግኘት አለባቸው።

**ለ. የመሸጋገሪያ ቃላትን በመጠቀም አምስት አረፍተነገሮችን መስርቱ።**

**ለምሳሌ፡**

አትሌቱ ፍጥነቱን ጨምሮ ሲሮጥ ነበር፣ ይሁንና ማሸነፍ አልቻለም።

ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ከዚህ በታች ሀረጎችን የተመለከተ ማስታወሻና መልመጃዎች ቀርበውላችኋል። መምህራችሁ የሚሰጧችሁን ማብራሪያና የቀረበውን ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ መልመጃዎቹን በትዕዛዛቸው መሰረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

ሀረጎች ከቃላት የሚመሰረቱ ሲሆን ሙሉ መልእክት ማስተላለፍ አይችሉም። አምስት የሀረግ አይነቶች አሉ። ሀረጎች ከቃላት ክፍሎች ይመሰረታሉ። ስማዊ ሀረግ ከስም፣ ግሳዊ ሀረግ ከግስ፣ ቅጽላዊ ሀረግ ከቅጽል፣ ተውሳከግሳዊ ሀረግ ከተውሳከ ግስ፣ መስተዋድዳዊ ሀረግ ከመስተዋድድ ይመሰረታሉ።

ምሳሌ፡

አንድ ሰባራ የእንጨት ወንበር- ስማዊ ሀረግ

ደብዳቤ ላከች- ግሳዊ ሀረግ

በጣም ብልጥ- ቅጽላዊ ሀረግ

ወንበር ላይ- መስተዋድዳዊ ሀረግ

በጣም ክፉኛ- ተውሳከግሳዊ ሀረግ

## መልመጃ ሰባት

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ሀረጎች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ።

1. ብልህ ተማሪ
2. ደብተሯን አጠናች
3. እንደወንድሙ የዋህ
4. እንደእሱ ክፉኛ
5. ከእኔ ጋር
6. በጣም የዋህ

7. ቤት ውስጥ
8. ምንኛ ሳዝናል
9. በፍጥነት
10. የገብስ ቆሎ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

ለ. ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ለቀረቡት የሀረግ አይነቶች በምሳሌው መሰረት ሁለት ሁለት ሀረጎችን ጻፉ።

ምሳሌ፡-
ስማዊ ሀረግ → የገብስ ጠላ
ግሳዊ ሀረግ → ታታሪ ሰው ነው
ቅጽዊ ሀረግ → በጣም ብልህ
ተውሳከግሳዊ ሀረግ → አሁን ገና
መስተዋድዳዊ ሀረግ → በመኪና

| | |
|---|---|
| ስማዊ ሀረግ | |
| | |
| ግሳዊ ሀረግ | |
| | |
| ቅጽላዊ ሀረግ | |
| | |
| ተውሳከግሳዊ ሀረግ | |
| | |
| መስተዋድዳዊ ሀረግ | |
| | |

# ምዕራፍ አምስት

## የህዝብ ብዛት

### የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- በንቃት አዳምጣችሁ የቀረበውን ጽሁፍ ትገመግማላችሁ፤
- የህዝብ ብዛት የሚለውን ጽንሰሀሳብ ታብራራላችሁ፤
- ተራኪ ድርሰት ትጽፋላችሁ፤
- የህዝብ ቁጥር በምጣኔ ሀብት እድገት ላይ ያለውን እንድምታ ትመረምራላችሁ፤
- ስሜቶቻችሁን ለመግለፅ ፍካሬያዊ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፤
- የገቢርና የተገብሮ ቃላትን በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ተጠቅማችሁ ታሳያላችሁ።

### ክፍለጊዜ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት መምህራችሁ "ወሳኝ ኩነት ምዝገባ" በሚል ርዕስ የቀረበን ጽሁፍ ያነቡላችኋል። በማስከተልም ጽሁፉን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችና ተግባራት ቀርበዋል። የቀረቡትን ጥያቄዎችና ተግባራት በትዕዛዛቸው መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ። በሚያቀርቡላችሁ ገለጻ መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

# ወሳኝ ኩነት ምዝገባ

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምንድን ነው?
2. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ምን ጥቅም ያለው ይመስላችኋል?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ኩነቶች በአንድ አገር ዜጎች የ__________፣ የ__________ እና የ__________ መስተጋብሮች ላይ ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል።
2. __________እና __________በሰው የአኗኗር ሥርዓት ውስጥ የሚከሰቱ ዋነኛ ማኅበረሰባዊና ሕጋዊ የለውጥ ጠቋሚ ወሳኝ ኩነቶች ናቸው።

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት አድርጋችሁ በቃል መልሱ።

1. በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ውስጥ የሚመዘገቡ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
2. አንድ ሰው ወሳኝ ኩነት ምዝገባን የሚያከናውነው ምን ምን ሁነቶች ሲፈጠሩ ነው?
3. ያዳመጣችሁት ጽሁፍ ፍሬሀሳብ ምንድን ነው?

**ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ የተጓደሉትን ሀሳቦች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ አሟልታችሁ ጻፉ።ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋርም ተለዋውጣችሁ አመሳክሩ።**

1. ወሣኝ ኩነት በመባል የሚታወቁት ________፣ ________ ፣ __________ እና __________ ክስተቶች ናቸው።

2. መረጃ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውልበት የአመዘጋገብና የአጠነቃቀር ሥርዓት ________ በመባል ይታወቃል።
3. የህዝብ ብዛትና እድገትን በቀጥታ ከሚያሳዩ ክስተቶች ዋነኞቹ ________ እና ________ ናቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## ተግባር አንድ

ሀ. ኩነቶች ሲከሰቱ ወደ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቢሮ በመሄድ የማያስመዘግቡ ዜጎችን ምን ትምክራላችሁ? ባለማስመዝገባቸውስ ምን ችግር የሚገጥማቸው ይመስላችኋል? በቡድን ተወያዩ። ተወያይታችሁ ያገኛችሁትን ሀሳብ በአንቀጽ አደራጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ።

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

## ተግባር ሁለት

ለ. በአካባቢያችሁ ወደ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቢሮ ሂዱ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች መነሻ አድርጋችሁ መረጃዎችን ሰብስቡ። ያገኛችኋቸውን መረጃዎች በአንቀጽ አደራጅታችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ።

1. ማህበረሰቡ ስለወሳኝ ኩነት ምዝገባ ያለው ግንዛቤ ምን ይመስላል?
2. በአብዛኛው የሚመዘገቡት ኩነቶች የትኞቹ ናቸው?
3. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ቢሮ ወሳኝ ኩነት ምዝገባን እንዴትና መቼ ያከናውናል?

ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ከዚህ በታች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት አድርጋችሁና የአካባቢያችሁን ነዋሪዎችን ጠይቃችሁ የምትሰሯቸው ተግባራት ቀርበዋል።ተግባራቱን በትዕዛዛቱ መሰረት ስሩ።

### ተግባር ሶስት

ያዳመጣችሁትን መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

1. በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ውስጥ የሚመዘገቡት ክስተቶች ወሳኝ ኩነቶች የተባሉበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. የአንድን ሀገር ህዝብ ብዛት የሚወስኑት ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
3. ወሳኝ ኩነቶች የህዝብ አስተዳደርን በሥርዓት ለመምራት መሰረቶች የሚሆኑት ለምንድን ነው?
4. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ለአንድ ሀገር የሚያስገኘው ፋይዳ ምንድን ነው?
5. በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ውስጥ የሚመዘገቡት ጉዳዮች የአንድን ሀገር ህዝብ ብዛት እንዴት ይወስኑታል?

ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር አራት

በዚህ ምዕራፍ የማዳመጥ ተግባር ወቅት መምህራችሁ ያነበቡላችሁን ጽሑፍ በተመለከተ የያዛችሁትን ማስታወሻ ለጓደኞቻችሁ አጋሩ። እናንተም ጓደኞቻችሁ ሲነግሯችሁ አዳምጡ።እናንተ የያዛችሁት ማስታወሻ ጓደኞቻችሁ ከያዙት ማስታወሻ የሚለይበትንም ተናገሩ።

ክፍለጊዜ፡ ስድስት

### ተግባር አምስት

በአካባቢያችሁ የሚገኙ ነዋሪዎችን ስለወሳኝ ኩነት ምዝገባ ያላቸውን ግንዛቤ ጠይቁ። ባገኛችሁት መረጃ ላይ በቡድን ተወያዩ።ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ቀጥሎ ምንባቡን የተመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን በትዕዛዛቱ መሰረት በትኩረት ስሩ።**

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**የሚቀጥለውን ጽሁፍ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ርእሱን ተመልክታችሁ ጽሁፉ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?
2. የህዝብ ብዛት ዕድገት ከምጣኔያዊ ሀብት እድገት ጋር ምን አይነት ግንኙነት ያለው ይመስላችኋል?
3. የሀገራችን የህዝብ ብዛት እድገት አሳሳቢ የሚሆነው ለምንድን ነው?

## የሕዝብ ቁጥር ዕድገት

በሥነሕዝብ ጥናት "የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ልማትን ያፋጥናል ወይስ ያጓትታል?" የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ነው። ይህንንም በተመለከተ አሉታዊና አዎንታዊ አስተሳሰቦች አሉ። ከአሉታዊ አስተሳሰቦች መካከል የእንግሊዛዊው 'የማልተስ' አስተሳሰብ ይጠቀሳል። ማልተስ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በምጣኔ ሀብት ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ይከራከራል። የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በታዳጊ አገሮች ማኅበራዊ፣ ምጣኔሀብታዊና ፖለቲካዊ ችግሮች እያስከተለ መሆኑንም ለማስረዳት ይሞክራል። በተለይም በምግብ አቅርቦትና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጫና በመፍጠር ረሀብና ድህነትን በእጅጉ ያስፋፋል በማለት ይከራከራል። ከዚህ የተነሳም ፈጣን ዕድገትን ለማምጣት የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን መወሰን አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን ይጠቁማል።

ከማልተስ በተቃራኒ "የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ጠቃሚ ነው" የሚል አስተሳሰብ አለ። ይህም ለምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ወሳኙ ሕዝብ ስለመሆኑ ይገልጻል። ይህን አስተሳሰብ የሚደግፉት ሊቃውንት "የሕዝብ ቁጥር ማደግ የዕውቀት አማራጮች እንዲሰፉ በማድረግ አሁን የሰው ልጆች የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ አመላካች ይሆናል" በማለት ይከራከራሉ።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የህዝብ ቁጥር ዕድገት የሚያስከትላቸው ተጽዕኖዎች ምን ምን ናቸው?
2. የሕዝብ ቁጥር ማደግ የምጣኔ ሀብት እድገትን እንዴት ይደግፋል?

ብዙ ሕዝብ ባለበት በምርት ተግባር ላይ ሊሰማራ የሚችል ብዙ የሰው ኃይል ይኖራል። የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ብዙ አምራች ኃይልን ያካተተ ሲሆንና በቂ ዕውቀትና ክህሎት ሲኖረው ለአገር ዕድገትና ልማት ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል። በተለይም በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰለጠኑ ሰዎች ቁጥር በርካታ ሲሆን የምጣኔሀብታዊ ዕድገት ይፋጠናል። ልማት በሰዎች ህይወት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ሁሉ ሰዎችም በልማት ሂደት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።

ምንም እንኳን ሕዝብ በልማት ሥራ ከፍተኛ ድርሻ ቢኖረውም በአገር ውስጥ ካሉት ተፈጥሯዊ ሀብቶች ጋር መጣጣም ይኖርበታል። ከተፈጥሯዊ ሀብቶች መካከል መሬት በዋናነት ይጠቀሳል። ሰዎች መሬትን እንዲለማም ሆነ እንዲራቆት ሊያደርጉ ይችላሉ። የሰዎች ተጠጋግቶ መኖር አካባቢን ያራቁታል። ሰዎች ለመኖሪያና ለተለያዩ ተግባራት ሲሉ ደኖችን እየመነጠሩና እየጨፈጨፉ የደን መመናመንን ያስከትላሉ። ይህም የአየር ሙቀት መጠን እንዲጨምር በማድረግ በረሃማነትን ያስፋፋል። በዚሁ የተነሳም መሬት የተፈጥሮ ለምነቷን ስለምታጣ ምርት ይቀንሳል፤ ድህነትም ይስፋፋል። ይህ እንዳይሆን በየጊዜው የሕዝብ ቆጠራ በማከናወን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለውጡን መከታተል ይገባል። በዚህ መነሻነትም የሕዝብ እድገቱን ለመወሰን ለማኅበረሰቡ ስለቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት መስጠት ይገባል። በተለይም ልጅ ሀብት ነው በሚል “አጉል ባህል” በመገፋፋት ብዙ ልጆችን የሚወልዱ ወላጆችን ማስተማር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

በአጠቃላይ ምጣኔሀብታዊ ዕድገት እንዲኖር ሀብት ያስፈልጋል። ሕዝብ ደግሞ በራሱ ሀብት ነው። የሕዝብ ቁጥር መቀነስ የተፈጥሮ ሀብቶችን አበልጽጎ ለመጠቀም የሚያስችል ሰብዓዊ ሀብት እጥረትን ይፈጥራል። በአንጻሩ ደግሞ የአገር ምጣኔ ሀብት ሊሸከመው ከሚችለው በላይ የሕዝብ ቁጥር ሲኖር የህዝቡን የኑሮ ደረጃ በመቀነስ የምግብ አቅርቦት ችግር ያስከትላል። ስለዚህ የአገርን ዕድገት ለማፋጠን የተመጣጠነ የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን በማምጣት ዜጎችን የልማት ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል።

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።

1. "ይህ እንዳይሆን..." (አንቀጽ 4) ሲል ምን እንዳይሆን ለማለት ፈልጎ ነው?
2. "በአንጻሩ ደግሞ..." (አንቀጽ 5) የሚለው የመሸጋገሪያ ቃል ቀጥሎ ምን አይነት ሀሳብ የሚቀርብ መሆኑን ያሳያል ?
3. የአንቀጽ ሁለት መልዕክት ምንድን ነው?
4. ከፍተኛ ህዝብ ተጠጋግቶ መኖሩ ምን ምን ጥቅሞችና ጉዳቶች አሉት?
5. የምንባቡ የመጨረሻው አንቀጽ የህዝብ ቁጥር በምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ያለውን ተጽዕኖ ምን በማለት ያጠቃልላል?
6. ሀገራችን ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር በተያያዘ ምን አይነት ችግር ይገጥማታል ብላችሁ ታስባላችሁ? ተወያዩበት።

7. "ልጅ ሀብት ነው" የሚለው አባባልን በመደገፍ ወይም በመቃወም ተከራከሩበት?
8. የሀገራችን የህዝብ ቁጥር ዕድገት ካለው ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታ ጋር እንዴት ይዛመዳል?

## ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልሱ።

1. ከሚከተሉት ሀሳቦች አንዱ ትክክል ነው?
   ሀ. የህዝብ ቁጥር ዕድገትን መቆጣጠር ይቻላል።
   ለ. የምግብ አቅርቦትን መቀነስ የህዝብ ቁጥርን ይጨምራል።
   ሐ. የህዝብ ቁጥር ዕድገት ምንም ጠቀሜታ የለውም።
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።
2. ህዝብና ልማት ______________________ ።
   ሀ. የተለያዩ ናቸው　　　ሐ. የማይገናኙ ናቸው
   ለ. አብረው የሚሄዱ ናቸው　　　መ. የሚነጣጠሉ ናቸው
3. ስለህዝብ ቁጥር መጨመር ትክክል የሆነው ሀሳብ የትኛው ነው?
   ሀ. በራሱ ችግር አይደለም።　　　ሐ. ህዝብ ሀብትን ያቀጭጫል።
   ለ. ሀገሮች ቦታ የላቸውም።　　　መ. እድገቱ መመጣጠን የለበትም።
4. "በዚህ መነሻነትም..." (አንቀጽ 4) ሲል በምን መነሻነት ለማለት ነው?
   ሀ. መሰረታዊ ፍላጎት　　　ሐ. ተፈጥሮ ሀብት
   ለ. የተለያዩ ዕቅዶች　　　መ. የህዝብ ቆጠራ

5. በ 'የማልተስ' አስተሳሰብ የትኛው ሀሳብ ትክክል ነው?

   ሀ. የህዝብ ቁጥር ዕድገት ጥቅም የለውም።

   ለ. የህዝም ቁጥር ዕድገት አሉታዊው ተጽዕኖ ያመዝናል።

   ሐ. የህዝብ ቁጥር አሰፈላጊ አይደለም።

   መ. የህዝብ ቁጥር ዕድገት አዎንታዊ ምላሽ አለው።

6. የህዝብ ቁጥር ዕድገት በምጣኔ ሀብት ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖን የሚገልጸው አንቀጽ የትኛው ነው?

   ሀ. አንቀጽ አንድ ሐ. አንቀጽ አራት

   ለ. አንቀጽ ሶስት መ. አንቀጽ ሁለት

7. የመጨረሻው አንቀጽ ምንባቡን ያጠቃለለው ምን አይነት አቋም ይዞ ነው?

   ሀ. የህዝብ ቁጥር በምጣኔ ሀብት ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ እንዳለው

   ለ. የህዝብ ቁጥር በምጣኔ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለው

   ሐ. የህዝብ ቁጥር ማመጣጠን እንደሚገባ

   መ. ምንም አይነት አቋም አላንጸባረቀም

ክፍለጊዜ፡ አስር

## መልመጃ ሶስት

ሐ. ምሳሌውን መሰረት አድርጋችሁ ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች መንስኤና ውጤት ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡ የሰዎች በመጠጋጋት መኖር አካባቢን ያራቁታል።

  ምክንያት፡ የሰዎች በመጠጋጋት መኖር

  ውጤት፡ የአካባቢ መራቆት፡፡

1. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በአገር ሀብት ላይ ጫና ስለሚፈጥር አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል።
2. የሕዝብ ቁጥር ማደግ የዕውቀት አማራጮች እንዲሰፉ በማድረግ አሁን የሰው ልጆች የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ አመላካች ይሆናል።
3. በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰለጠኑ ሰዎች ቁጥር በርካታ ሲሆን የምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ይፋጠናል።
4. የሥራ ዕድል ፈጠራውም በሚፈለገው መጠን ባለማደጉ ይህ የሥራ-አጥ የመሆን ዕድል ያለው ትውልድ ለፀጥታ ችግር፣ ለወንጀልና ለስደት ይዳረጋል።
5. በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ባለው የህዝብ ቁጥር የመሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት እጅግ አዳጋች ይሆናል።

## መልመጃ አራት

ሀ. ከዚህ በታች በቀረበው የቢጋር ሰንጠረዥ የህዘብ ቁጥር መጨመር የሚኖረውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ደብተራችሁ ላይ ጻፉ።



ለ. ከላይ በቀረበው የቢጋር ሰንጠረዥ ያሟላችኋቸውን ሀሳቦች መነሻ አድርጋችሁ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ከዚህ በታች ፍካሬያዊ ፍቺን የተመለከተ ማስታወሻና ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠትን የተመለከቱ መልመጃዎች ቀርበዋል። መልመጃዎቹን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

### መልመጃ አምስት

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። ለቃላቱ ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ አውዳዊ ፍች ስጡ።

1. መስተጋብር (አንቀጽ አንድ)
2. ጫና (አንቀጽ አንድ)
3. ማጣጣም (አንቀጽ አንድ)
4. ታዳጊ (አንቀጽ ሁለት)
5. ወሳኙ (አንቀጽ ሁለት)
6. ክህሎት (አንቀጽ ሶስት)
7. መጣጣም (አንቀጽ ሶስት)
8. መራቆት (አንቀጽ አራት)
9. ገቢራዊ (አንቀጽ አራት)
10. ማበልጸግ (አንቀጽ አምስት)

ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ምሳሌውን መሰረት አድርጋችሁ ተመሳሳይ ፍች ስጡና የቃላቱን ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች መስርቱ።

ምሳሌ፡ ዕድገት፡ ጭማሪ፣ ለውጥ

የአንድ ሀገር ዕድገት በዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል።

| | |
|---|---|
| 1. እድገት | 6. መከሰት |
| 2. የጎላ | 7. አስጊ |
| 3. ድርሻ | 8. ተርታ |
| 4. መጠጋጋት | 9. ስደት |
| 5. አመላካች | 10. ፈታኝ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

**ማስታወሻ**

**የቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ**

ፍካሬያዊ ፍቺ ቃላት በተጨማሪነት ወይም በተደራቢነት የሚይዙት ፍቺ ነው። እነዚህ ፍቺዎች ተናጋሪ ወይም ጸሐፊ ቃሉ እንዲይዝ ባደረገው አዲስ ፍቺ ላይ ይመሰረታል። ፍካሬያዊ ፍቺ የቃላት ተዘዋዋሪ ፍቺ በመባልም ይታወቃል።

ምሳሌ፡-

አብዛኛዎቹ የሩጫው አለም <u>አናብስት</u> የሀገሬ ልጆች ናቸው። የተሰመረበት ቃል ፍቺ ጥንካሬን ወይም ጀግንነትን ያመለክታል።

እማሬያዊ፡ አናብስት(አንበሶች) ⟶ ስጋ በል የዱር እንስሳት

ፍካሬያዊ፡ አናብስት ⟶ ጀግኖች፣አሸናፊዎች

## መልመጃ ስድስት

ሀ. በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ምሳሌውን መሰረት አድርጋችሁ ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡ ወጣቶቹ እንጀራ ፍለጋ ከሀገር ወደ ሀገር ይሄዳሉ።

| ቃል | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|
| እንጀራ | መተዳደሪያ/መኖሪያ/ |

1. ብዙ አፍሪካዊያን ወንድማማቾችን ወንበር አጋድሏቸዋል።
2. የሰዎቹ ጎጆ ስለፈረሰ ልጆቻቸው ተበታተኑ።
3. እኛ ያሞኘናት መሰለን እንጂ ልጅቷ ቆቅ ናት።
4. የክፍል አለቃችን በትምህርቱ አንበሳ ነው።
5. መናደዷን ሳትደብቅ እሳት ለብሳ እሳት ጎርሳ መጣች።

ለ. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ።

ምሳሌ፡ እስስት

እስስት መልኳን የምትቀያይር ተሳቢ እንስሳ ናት።

ሰውዬው ባህሪው እስስት ነው።

| | |
|---|---|
| 1. ንብ | 4. ጠፋ |
| 2. አይን | 5. አለፈ |
| 3. እሳት | 6. አልጋ |

ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

## መልመጃ ሰባት

ሐ. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ።

| | |
|---|---|
| 1. ጅብ | 6. አለፈ |
| 2. አህያ | 7. ደከመ |
| 3. እርግብ | 8. ብረት |
| 4. አረፈ | 9. በግ |
| 5. አባብ | 10. ጂት |

ለ. እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸውን አምስት ቃላት ፈልጋችሁ ፍቺያቸውን የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

ቀጥሎ ተራኪ ድርሰትን የተመለከተ ማስታወሻና የተለያዩ ተግባራት ቀርበዋል። መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን ማብራሪያ ካዳመጣችሁ በኋላ ተግባራቱን በትዕዛዛቱ መሰረት በሚገባ ሁኔታ አከናውኑ።

**ማስታወሻ**

**ተራኪ ድርሰት**

የተራኪ ድርሰት ዋና አላማ የድርጊት ቅደምተከተል ያላቸውን ታሪኮች ከግለሰባዊ እይታ አንጻር መተረክ ነው። ዋና ተግባሩ መንገር ስለሚፈለገው ጉዳይ መጠቀስ የሚገባቸውን ሁነቶች አንድ በአንድና በቅደምተከተል

በማንሳት አንድ ወጥ የታሪክ ቅንጫቢ ለታዳሚው ማቅረብ ነው። በማራኪ ዝርዝር ሁኔታዎች እና በሳቢ ሁነቶች ከተዋቀረ ተራኪ ጽሁፍ ለጸሃፊውም ሆነ ለአንባቢው አስደሳችና ማራኪ ይሆናል።

ምሳሌ፡-

ከዕለታት አንድ ቀን የራበው መንገደኛ የአተር እሸት ያለበት ማሳ አገኘ። ቁጭ አለና አተሩን ከነልባሱ ሲበላ ቆየ። ጠገብ ሲል ልባሱን እያነሳ መብላት ጀመረ። በጣም ሲጠግብ ደግሞ ከውስጥ የዘሩን ፍሬ እያወጣ መብላት ያዘ። የማሳው ባለቤት ከዛፍ ስር ሆና ስታየው ኖራ መንገደኛ እንደመጀመሪያውም እንደመጨረሻውም አትብላ፤እንደመካከለኛው ብላ አለች።

## ተግባር ሰባት

ከላይ የቀረበላችሁን ገለጻና ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ ስለትምህርት ቤታችሁ አመሰራረት የሚያስረዳ አንድ ተራኪ ድርሰት ጽፉችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ተግባር ስምንት

ቤተ መጻህፍ በመሄድ አንድ ተራኪ ጽሑፍ ከጋዜጣ፣ ከመጽሔት ወይም ከመጽሐፍ ላይ አንብቡ። ያነበባችሁትን ታሪክ ዋና ዋና ክንውኖችም በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ በቅደም ተከተል በማስፈር ክፍል ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

**ተግባር ዘጠኝ**

የየራሳችሁን የህይወት ታሪክ የተራኪ ድርሰት አወቃቀርን በመከተል ጽፋችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመቀያየር አስተያየት ተሰጣጡ።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

**ተግባር አስር**

በባለፈው ክፍለጊዜ ከጓደኞቻችሁ ጋር የተገማገማችሁትን መሰረት አድርጋችሁ የጻፋችሁትን ተራኪ ጽሁፍ አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

**ተግባር አስራ አንድ**

ያነበባችሁትን መሰረት አድርጋችሁ የህዝብ ቁጥር በምጣኔ ሀብት ላይ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ በራሳችሁ አገላለጽ በተወሰኑ አንቀጾች ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ የትምህርት ይዘት ስለገቢርና ተገብሮ ግሶች ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን ማብራሪያና የሚሰጧችሁን ምሳሌዎች መሰረት አድርጋችሁ የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዛቸው መሰረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

**ገቢርና የተገብሮ ግሶች**

ገቢርና ተገብሮ ግስ የምንለው ግሱ ከድርጊት ፈጻሚው ወይም ከድርጊት ተቀባዩ አንጻር የሚተይበትን ነው። ገቢር ግስ የአረፍተነገሩ ባለቤት ድርጊት ፈጻሚ የሚሆንበት ሲሆን፣ ተገብሮ ግስ ደግሞ የአረፍተነገሩ ባለቤት ድርጊት የተፈጸመበት ወይም የድርጊቱ ተቀባይ ይሆናል ማለት ነው።

ምሳሌ፡ ልጁ ብርጭቆውን ሰበረ።

ብርጭቆው ተሰበረ።

ከላይ የቀረቡትን ሁለት አረፍተነገሮች ስንመለከት በመጀመሪያው አረፍተ ነገር ‹‹ልጁ›› የሚለው ስም የአረፍተነገሩ ባለቤት ነው። በሁለተኛው አረፍተነገር ደግሞ ተሳቢ የነበረው ‹‹ብርጭቆ›› የአረፍተነገሩ ባለቤት ሆኗል። ግሶቹም 'ሰበረ' ገቢርን፣ 'ተሰበረ' ደግሞ ተገብሮን ያመለክቱ ሆነዋል።

## መልመጃ ስምንት

ሀ. ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ቃላት የገቢርና ተገብሮ ግሶች በማለት ለይታችሁ ጻፏቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አልተጨመረም | ደገመ | ፈቀደ | ተሞገተ | አመለጠ |
| ተነገረ | ተፈታ | ታረሰ | ታወቀ | በላ |
| ተፈረመ | ታረመ | መሰለ | ተመከረ | ተጠጣ |
| ተከበረ | አከለ | ተቀመረ | ሰማ | ሰበሰበ |

ለ. ከላይ በማስታወሻው የቀረበላችሁን ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ አምስት አምስት የገቢርና የተገብሮ ግሶችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮች መስርቱ።

# ምዕራፍ ስድስት

## በረሃማነት

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- ጽሁፍን አዳምጣችሁ የበረሃማነት ጽንሰሀሳብን ትተነትናላችሁ፤
- ምንባቡን አቀላጥፋችሁ በማንበብ ማጠቃለያ ትሰጣላችሁ፤
- ከቀረበ ምንባብ በረሃማነት በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ትተነትናላችሁ፤
- የገላጭ ድርሰትን መዋቅር ትለያላችሁ፤
- ስሜቶቻችሁን ለመግለጽ ፍካሬያዊ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፤
- አገልግሎታዊ ዓረፍተነገሮችን ትለያላችሁ፡፡

ክፍለጊዜ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

የተለያዩ ጥያቄዎች ለማዳመጥ የቀረበውን ጽሁፍ መሰረት አድርገው ቀጥለው ቀርበዋል። የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሰረት በትኩረት ስሩ። እንዲሁም ጽሁፉ ሲያነቡላችሁ እያዳመጣችሁ አጫጭር ማስታወሻ ያዙ።

## ጤናማ አፈር ለጤናማ ህይወት

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ጤናማ ህይወት ማለት ምን ማለት ነው?
2. በሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ፍቺ ላይ በጥንድ ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ።

ፍግ | ጤናማ አፈር
ብስባሽ | አረም
የተፈጥሮ ማዳበሪያ

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ለአርሶ አደሩ ምርት ማነስ ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው?
2. የኬሚካል ማዳበሪያዎች የሚያስከትሉት ጉዳት ምንድን ነው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት አድርጋችሁ በጽሁፍ መልሱ።**

1. በሀገራችን ግብርና ምርት ማነስ ሰበብ ሆኖ የቀጠለው ምንድን ነው?
2. የአፈርን ውኃ የማስረግ አቅምን ከፍ የሚያደርጉ ዘዴዎችን ዘርዝሩ።
3. የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከሌላው በምን ይለያል?
4. ደርቀውና ጠፍተው የነበሩ ምንጮች ተመለሱ ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. አፈሩ ለም ከሆነ ከማሳ ላይ የሚጠፉ ተክሎች ምን ምን ናቸው?

**ለ. ከዚህ በታች የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለጥያቄዎቹ ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት አድርጋችሁ ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. ለኢትዮጵያ አፈር መሸርሸር ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው?
   ሀ. ጎርፍ　　ሐ. የአስተራረስ ዘዴ
   ለ. የደን መመናመን　　መ. የአየር መዛባት?
2. ምርትን በዘላቂነት የሚጨምረው ተግባር የትኛው ነው?
   ሀ. አፈርን በፍግና በብስባሽ ማዳበር　　ሐ. ደጋግሞ ማረስ
   ለ. የኬሚካል ማዳበሪያ መጠቀም　　መ. ጸረአረም ኬሚካሎችን መጠቀም

3. የኬሚካል ማዳበሪያዎች አሉታዊ ተጽዕኖ የትኛው ነው?
   ሀ. በአፈር ውስጥ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ
   ለ. ለአፈር ለምነት ጠቃሚ የሆኑትን ደቂቅ ህዋሳትን ማጥፋት
   ሐ. ምርት መጨመሩ
   መ. በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ከዋለ አፈርን ሙት ማድረጉ
4. የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከኬሚካል ማዳበሪያ የሚለይበት ባህርይው የትኛው ነው?
   ሀ. ረጅም ጊዜ በአፈር ውስጥ መቆየቱ
   ለ. ውሃን የመያዝ አቅሙ ከፍተኛ መሆኑ
   ሐ. የአፈር መሸርሸርን የመከላከል አቅሙ ከፍተኛ መሆኑ
   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።
5. የአፈር ለምነት መጠበቅ ድምር ውጤቱ ምንድን ነው ?
   ሀ. የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው።
   ለ. ድህነት እንዲቀንስ ያደርጋል።
   ሐ. ማህበረሰቡ የተሻለ ኑሮ እንዲኖር ያደርጋል።
   መ ሁሉም መልስ ይሆናል።

ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ከዚህ ቀጥሎ እንድትናገሩ የሚያግዙ መልመጃ እና ተግባር ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም በትእዛዛቱ መሰረት በትኩረት ስሯቸው፡፡**

### መልመጃ ሁለት

**መምህራችሁ ያነበቡላችሁን ምንባብ መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ በቃል መልሱ።**

1. ‹ጤናማ አፈርን እንዴት መፍጠር ይቻላል?

2. የተፈጥሮና የኬሚካል ማዳበሪያ ልዩነታቸውን ተንትኑ።
3. የተፈጥሮ ማዳበሪያ ጥቅሙን መዝናችሁ ተናገሩ?
4. የጤናማ አፈር ጥቅሙ ምንድን ነው?
5. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

## ተግባር አንድ

**የሚከተሉትን ተግባራት በትዕዛዛቸው መሰረት ስሩ።**

1. በምትኖሩበት አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬታቸው ለም እንዲሆን ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናውኑ ጠይቁ። ያገኛችሁት መረጃ ላይም በጥንድ ተወያዩ። ተወያይታችሁ ያገኛችሁትን ሀሳብ ጨምቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቡድን ተወካያችሁ አቅርቡ።
2. የተፈጥሮና የኬሚካል ማዳበሪያ በግብርናው ምርት ላይ ያላቸውን ጠቀሜታ በማወዳደርና በማነጻጸር በአንቀጽ አደራጅታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ ሶስት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**የተለያዩ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው ቀጥለው ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን በትዕዛዛቸው መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።**

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ ተወያዩና የተወያያችሁትን በቃል ተናገሩ።**

1.ከዚህ በታች ስለቀረበው ስዕል የተረዳችሁትን ለጓደኛችሁ አስረዱ፡፡

2. በረሀማነትና ድርቅ የሚያስከትሏቸው ተጽዕኖዎች ምን ምን ናቸው?
3. ርዕሱን በመመልከት በምንባቡ ውስጥ ምን ምን ሀሳቦች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?



## በረሃማነትና ድርቅ

በሀገራችን ላይ በበረሃማነትና ድርቅ መስፋፋት ምክንያት ከፍተኛ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ቀውስ ተከስቷል። በማስከተልም ላይ ይገኛል። ለምሳሌ በረሃማነቱና ድርቁ በተስፋፋባቸው አካባቢዎች ነዋሪዎች ተረጋግተው መኖር እንዳይችሉ አድርጓል። በተለይም አርብተው የሚኖሩ ዜጎቻችን በውኃና ግጦሽ እጥረት ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው እንዲኖሩ አስገድዷቸዋል። ይህም ዜጎች በአንድ አካባቢ በመኖር የመሰረተ ልማት አውታሮች የሆኑትን እንደ መብራት፣ ውኃና የመንገድ አገልግሎት እንዳያገኙም ተጽዕኖ ፈጥሮባቸዋል። በተጨማሪም የወተትና ስጋ ምርታቸው በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ አድርጓል፣ እንስሶቻቸውም በሚፈለገው መጠን የመራባት ፍጥነታቸው እንዲቀንስ አድርጓል። የግብርናው ምርትም እንዲቀንስ በማድረግ የምግብ እጥረት ተከስቷል።

በበረሃማነትና ድርቅ መስፋፋት የሰው ልጆች ጤናም እክል እንዲገጥመው ምክንያት ሆኗል ። በበረሃማነት መስፋፋት ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ስለሚፈጠር ሰዎች ሁልጊዜ ምቾት እንዳይሰማቸው ያደርጋል። ይህም ውሎ ሲያድር የሰው ልጆች ለተለያዩ በሽታዎች እንዲጋለጡ ያደርጋል።

በተዘዋዋሪ የበረሃማነትና ድርቅ መስፋፈት ለአካባቢችንም ሆነ ለአለማችን የአየር ንብረት ለውጥ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋል። በዚህም ደግሞ ወቅቱን ላልጠበቀ፣ ከሚጠበቀው በታችና ለከባድ ዝናብ መዝነብ ምክንያት ስለሚሆን ዜጎች ከባድ የድርቅና የጎርፍ አደጋ ያጋጥማቸዋል። ይህም የግብርና ምርት በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ ስለሚያደርግ የምግብ እጥረት እንዲከሰት ያደርጋል።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ሀ. ባነበባችሁት የምንባቡ ክፍል በረሃማነት የሚያስከትለው ችግር ምንድነው?
ለ. በረሃማነትን የሚያስከትሉ መንስኤዎች ምን ምን ናቸው?ግምቱ።

ለበረሃማነትና ድርቅ መስፋፋት መከሰት ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ናቸው ብሎ መፈረጅ ይቻላል። ሰው ሰራሽ የምንላቸው ሰዎች ለተለያዩ አላማዎች ደኖችን መጨፍጨፍና መመንጠር፣ ወደ ከባቢ አየር የተቃጠለ አየር መልቀቅ፣ መሬትንና ውኃን በአግባቡ ያለመጠቀም ናቸው።ተፈጥሯዊ የምንላቸው ደግሞ በተፈትሮ የሚከሰቱ ሲሆን እነዚህም እንደእሳተ ጎሞራ፣ የመሬት መንሸራተትና መሳሳሉት ናቸው።

በረሃማነትንና የድርቅ መስፋፋትን ለመከላከል ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለበት። ለመሆኑ ምን ማድረግ አለብን? በየአካባቢችን ያለማቋረጥ በተለያየ ምክንያት የተራቆቱና የተጎዱ

መሬቶችን በደን መሸፈን፣ ያሉትን የደን ሀብቶች ጠንካራ ጥበቃና ክልከላ ማድረግ፣ በየአካባቢያችን በክረምት ወቅት ውኃን ማቆር ይገባናል። በደምሳሳው ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ ህብረተሰብን ማስተማር መተኪያ የሌለው የመፍትሄ ሀሳብ ነው።

## ክፍለጊዜ አራት

# የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ ሰስት

ሀ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በጽሁፍ መልሱ።

1. የበረሃማነትና ድርቅ መስፋፋት የአየር ንብረት ለውጥ እንዲከሰት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ የሚገልጽ አንቀጽ የትኛው ነው ?
2. ሶስተኛው አንቀጽ መልዕክቱ ምንድን ነው?
3. "ይህም ውሎ ሲያድር" ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ለበረሃማነትና ድርቅ መስፋፋት ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶችን ዘርዝሩ።
5. ጸሀፊው ምን አይነት ሀሳብ በማቅረብ ጽሁፉን አጠቃለለ?

ለ. ከዚህ በታች የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለጥያቄዎቹ ያነበባችሁትን ምንባብ መሰረት አድርጋችሁ ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልሱ።

1. "የሰው ልጆች ጤናም እክል እንዲገጥመው ምክንያት ሆኗል።" ሲል ምን ማለቱ ነው?
   ሀ. ሰው ልጅ ጤና ጥሩ ነው ማለት ነው።
   ለ. ሰው ልጅ ጤና መልካም ነው ማለት ነው።
   ሐ. የሰው ልጅ ጤና አሳሳቢ አይደለም ማለት ነው።
   መ. የስወ ልጅ ጤና ችግር ይገጥመዋል ማለት ነው።

2. "ይህ ደግሞ ወቅቱን ላልጠበቀ..."በሚለው ውስጥ "ይህ" የሚለው ምንን ይወክላል?

ሀ. ዛፎችን ማብቀል ሐ. በረሃማነትና ድርቅ

ለ. ደንና እርሻን ማጣመር መ. የአየር ንብረት ለውጥ

3. በምንባቡ መሰረት ምርት የማይጨምረው ተግባር የትኛው ነው?

ሀ. አፈሩ እንዳይከላ መርዳት

ለ. ውኃን በአግባቡ ማቆር

ሐ. ዘላቂነት ያለዉ የመሬት አጠቃቀም

መ. የተፈጥሮ አካባቢ ማጠናከር

4. በምንባቡ መሰረት የትኛው ሀሳብ ትክክል ነው?

ሀ. የበረሃማነትና ድርቅ መስፋፋት ከቦታ ቦታ አይለያይም።

ለ. ዛፎችን መትከል የመሬትን እርጥበት ከፍ ያደርጋል።

ሐ. በረሀማነት በአብዛኛው በተፈጥሮ ምክንያት ይከሰታል።

መ. የአፈር መከላት የምርት መቀነስን አያስከትልም።

5. በመሬት ለምነት ማጣት የሚመጣውን ችግር ለመቋቋም ወሳኙ መፍትሄ ምንድን ነው?

ሀ. የመሬት ለምንትን በዘላቂነት መጠበቅ

ለ. የህብረተሰብን ንቃተ ህሊና መጨመር

ሐ. የመሬትን ለምንት የሚያስጠብቁ ሌሎች ዘዴዎችን መጠቀም

መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።

### ተግባር ሁለት

1. በአካባቢያችሁ በረሃማነትና ድርቅ እንዲስፋ የሚያደርጉ ተግባራትን ለይታችሁ በመፍትሄዎቻቸው ላይ ከተወያያችሁ በኋላ በጽሁፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ።
2. በሀገራችን በየአመቱ የሚከናወኑ የችግኝ ተከላ ተግባራትን በረሃማነትንና ድርቅን ከመከላከል አንጻት እንዴት ትገመግሙታላችሁ?
3. ‹‹በደምሳሳው ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ ህብረተሰብን ማስተማር መተኪያ የሌለው የመፍትሄ ሀሳብ ነው።›› በሚል በምንባቡ የመጨረሻ አንቀጽ በማጠቃለያነት የቀረበውን ዓረፍተነገር በቡድናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ አስፋፍታችሁ እና አሻሽላችሁ እንደገና ጻፉት፤ ጽሁፋችሁንም ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ቀጥሎ ፍካሬያው ፍቺን የተመለከተ ማስታወሻና ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ የሚሉ መልመጃዎች  ቀርበዋል። መምህራችሁ የሚያደርጉላችሁን ማብራሪያና የቀረበላችሁን ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ መልመጃዎቹን በትዕዛዛቸው መሰረት ስሩ።

### መልመጃ አራት

ሀ. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። ስለዚህ በ ‹‹ሀ››ረድፍ ያሉትን በ‹‹ለ››ረድፍ ካሉት ጋር ተመሳሳይ ፍቺያቸውን አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ለምነት | ሀ. ሲቆይ |
| 2. ተጋላጭ | ለ. መያዝ |
| 3. ቀውስ | ሐ. ተጠቂ |
| 4. ዕጥረት | መ. ማነስ |
| 5. ውሎ ሲያድር | ሠ. የተጎሳቆሉ |
| 6. ላሰለሰ | ረ. ብስባሽ ያለው |
| 7. ማቆር | ሰ. ሳያቋርጥ |
| 8. የተራቆቱ | ሸ. ችግር |
| | ቀ. ከርሞ |

## ማስታወሻ

### የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

እማሬያዊ ፍቺ ቃሉ ሲባል ወይም ሲጠራ ወደ አእምሯችን የሚመጣው የቃሉ የመጀመሪያ ትርጉም ነው። ይህም የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ነው። ፍካሬያዊ ፍች ደግሞ የአንድ ቃል ተጨማሪ/ተደራቢ ትርጉም ነው። ይህም ግለሰቡ ቃሉ ለወከለው ነገር የሚኖረው አተያይ/አመለካከት፣ ዝንባሌና እምነት ላይ ይመሰረታል።

ለምሳሌ፡- ሰውዬው ቁልፍ ጣለ።

ሰውዬው በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ቁልፍ ሰው ነው።

ከላይ ‹‹ቁልፍ›› የሚለው ቃል በሁለቱ አረፍተነገሮች ውስጥ የተለያየ ትርጉም አለው። በመጀመሪያው አረፍተነገር የቤት መክፈቻ የሚል ትርጉም ሲኖረው ይህም ቀጥተኛ/እማሬዊ ፍቺው ነው። በሁለተኛው አረፍተነገር እጅግ የሚፈለግ/ዋነኛ ሰው የሚል ትርጉም ሲኖረው ይህም ተጨማሪ ወይም ፍካሬያዊው ፍቺ ነው።

## መልመጃ አምስት

ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ።

| ቃል | እማሬያዊ ፍቺ | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|
| እሳት | የሚያቃጥል/ነበልባል | ሀይለኛ |
| ድንጋይ | ________ | ________ |
| እባብ | ________ | ________ |
| ቆቅ | ________ | ________ |
| አይን | ________ | ________ |
| እንጀራ | ________ | ________ |

ክፍለጊዜ ስድስት

## መልመጃ ስድስት

ከዚህ በታች ጥንድ ጥንድ ሆነው በቀረቡ አረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት እማሬዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ።

1.ሰውየው ንብ በቀፎው ውስጥ ያዘ።

ሰውዬው ንብ የሆነች ልጅ አለችው።

2.ሰዎቹ ቤት ገነቡ።

ልጁ ቤት መሰረተ።

3.ልጁ ከቤት ጠፋ ።

የሴትየዋ ህይወት ጠፋ።

4. ሴትየዋ ውሃ ቀዳች።
   ወንድሜ ደንግጦ ውሃ ሆነ።
5. አባቴ ዛፍ ተክሎ መጣ።
   ጓደኛዬ ቁመቱ ዛፍ ነው።

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

### ክፍለጊዜ ሰባት

ቀጥሎ ገላጭ ድርሰትን የተመለከተ ማስታወሻና ተግባራት ቀርበዋል። መምህራችሁ የሚያደርጉላችሁን ማብራሪያና የቀረበላችሁን ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ ተግባራቱን በትዕዛዛቸው መሰረት በትኩረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

**ገላጭ ድርሰት**

የገላጭ ድርሰት ዋነኛ አላማው መልእክትን ማስተላለፍ ስለሆነ ለቃላት ምርጫ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ሀሳቦቹንም በምክንያትና ውጤት፣ በማወዳደርና ማነጻጸር፣ተረክን፣ ብያኔን፣ ሂደታዊ ትንተናን ይጠቀማል። እያንዳንዳቸውን በተናጠል ስንመለከት፡-

**ምክንያትንና ውጤት፡-** ክስተቶች ተከታትለው በሚመጡበት ጊዜ የመጀመሪያው ለሁለተኛው ክስተት መምጣት ምክንያት በመሆን ሀሳቦች ሲደራጁ ነው።

**ማወዳደርና ማነጻጸር፡-** በተለያዩ ነገሮች መካከል ተመሳስሎና በተመሳሳይ ነገሮች መካከል ልዩነትን የማሳያ የአጻጻፍ ስልት ነው።

**ተርክ/ሀተታ፡-** አንድ ነገር ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ያለውን ሂደት እየተነተነ ይተርካል። ትንተናውም በጊዜና በቦታ ወይም በአፈጻጸም ቅደምተከተል ላይ የተመሰረተ ነው።

**ብያኔ፡-** የአንድን ነገር ምንነት ወይም ምን ማለትነት፣ በሌላ አማራጭ የአንድን ነገር ምን አለመሆን ላይ ያተኩራል።

## ተግባር ሶስት

ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት ርዕሶች መነሻ አንድ ገላጭ ድርሰት ጽፋችሁ በመምጣት የጻፋችሁትን ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመቀያየር የድርሰቱን መዋቅር ተገማገሙ፡፡ ስትጽፉም በምዕራፍ ሁለት በክፍለጊዜ ዘጠኝ የተቀመጡትን የድርሰት መጻፊያ ቅደምተከተሎች ተከተሉ። እንዲሁም መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን ሞዴል ጽሁፍ መሰረት በማድረግ ጻፉ፡፡

- አረንጓዴ አሻራ
- የከተማ እርሻ
- ሀገር በቀል ዛፎች
- የአካባቢ ጽዳት

ለ. ከላይ የተገማገማችሁትን ገላጭ ድርሰት እንደገና አስተካክላችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ቀጥሎ አገልግሎታዊ ዓረፍተነገሮችን የተመለከተ ማስታወሻና መልመጃዎች ቀርበዋል። መምህራችሁ የሚያደርጉላችሁን ማብራሪያና የቀረበላችሁን ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ መልመጃዎቹን በትዕዛዛቸው መሰረት ስሩ።

### ማስታወሻ

**አገልግሎታዊ አረፍተነገሮች**

አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮች፡ በአራት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

ሀተታዊ አረፍተ ነገር፡- ቀጥተኛ ሀሳብ የሚገለጽበት ነው።

ምሳሌ፡ ቶሌራ ጎበዝ ሾፌር ነው።

ጥያቄያዊ አረፍተ ነገር፡ ምላሽ የሚሻ ሀሳብ የሚገለጽበት ነው።

ለምሳሌ፡- ለምን የቤት ስራ አልሰራህም?

ትእዛዛዊ አረፍተ ነገር፡ አንድ ሰው አንድን ስራ በትብብር ወይም አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ እንዲሰራ ለማድረግ መልእክት የሚተላለፍበት አረፍተ ነገር ነው።

ምሳሌ፡ ያዋስሽኝን መጽሀፍ አመጣሁልሽ።

አጋናኝ አረፍተነገር፡ መደነቅን፣ መገረምን፣ መደንገጥንና የመሳሰሉትን ስሜቶች ለመግለጽ እንጠቀምበታለን።

ምሳሌ፡- እንዴት ያለ ጭንቅላት ሰጥቷታል!

## መልመጃ ስድስት

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ዐረፍተነገሮች ሀተታዊ፣ ጥያቄዊ፣ ትዕዛዛዊና አጋናኝ በማለት ለዩ።

1. ወንድሜ በሩን ዝጋ።
2. ጫልቺሳ ወደቤተሰቦቹ ገባ
3. አንቺ መቼ ትመረቂያለሽ?
4. እንዴት ይገርማል!
5. ዛሬ መጽሀፍ አነባለሁ።
6. ስራ ስለምሄድ ቁርሴን ስጪኝ።
7. ድግስ ድንቅ ነው!
8. የመጽሃፉ ታሪክ ጥሩ ነው?

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### መልመጃ ሰባት

ከላይ የተሰጠውን ማስታወሻና ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ ለእያንዳንዳቸው አገልግሎታዊ አረፍተነገሮች ሶስት ሶስት ምሳሌ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

# ምዕራፍ ሰባት

# የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

### ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- መረጃ ሰጪ ጽሁፍን በጥልቀት በማዳመጥ ተግባራዊ ታደርጋላችሁ።
- ከቀረበ ምንባብ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ጽንሰሃሳብንና የሚያስከትለውን ተጽእኖ ታብራራላችሁ፤
- በአንድ ጉዳይ ላይ ትደራደራላችሁ፤
- ቃላትን ከተቃራኒ ፍቺያቸው ጋር ታዛምዳላችሁ፤
- ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ይጠቀማሉ፤
- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን ለይተው ይጠቀማሉ።

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

የተለያዩ ጥያቄዎች ለማዳመጥ የቀረበውን ጽሁፍ መሰረት አድርገው ቀጥለው ቀርበዋል። የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሰረት በትኩረት ስሩ። እንዲሁም ጽሁፉ ሲያነቡላችሁ እያዳመጣችሁ አጫጭር ማስታወሻ ያዙ።

## የህጻናት መብቶች

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ህጻናት ከአቅማቸው በላይ የተለያዩ ስራዎች ሲሰሩ ካስተዋላችሁ ለጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡
2. በአካባቢያችሁ የህጻናትን መብቶች የማያከብሩ አካላት እነማን ናቸው?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ የተጓደሉትን ቃላት እያዳመጣችሁ አሟሉ።**

1. በቀላሉ በበሽታዎች ________።
2. ህጻናት በእሴቶችና በባህል ________ ይኖርባቸዋል።
3. ሞራላዊና መንፈሳዊ ________ እንዲኖራቸው በእሴቶችና በባህል መበልጸግ ይኖርባቸዋል።
4. ከማንኛውም አይነት ጥቃት ________ በጥቅሉ ጥበቃ የማግኘት ተብለው የሚታወቁ በርካታ መብቶች አሏቸው።
5. ሞራላቸውንና መንፈሳቸው ________ ባጠቃላይ ኑሮአቸውንና ህይወታቸውን የሚያጨልሙ አደጋዎች ናቸው።

### ክፍለጊዜ አንድ

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. መምህራችሁ ምንባቡን ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ አዳምጣችሁ ከዚህ በታች በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ በተወካያችሁ አማካኝነት በቃል አቅርቡ።**

1. ህጻናት ህይወታቸውን ለሚፈታተኑ በርካታ አደጋዎች የሚጋለጡት እንዴት ነው?
2. ህጻናት ለምን ለምን አደጋዎች ሊጋለጡ ይችላሉ?
3. የህጻናት የዕድገት መብቶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
4. ህጻናት ሞራላዊና መንፈሳዊ ብቃት እንዲኖራቸው ምን መሆን ይኖርባቸዋል?

5. ባዳመጣችሁት ጽሁፍ የተጠቀሱት የህጻናት መብቶች ምን ምን ናቸው?

**ለ. ያዳመጣችሁትን መሰረት አድርጋችሁ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. ህጻናት አእምሯቸው እንዲበለጽግ ምን ያስፈልጋቸዋል?

   ሀ. ስልጠናዎች        ሐ. ቁጥጥር

   ለ. ጨዋታዎች        መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

2. ህጻናት ከማንኛውም ጥቃት የሚታደጉበት መብት ምን ይሰኛል?

   ሀ. ማደግ        ሐ. በህይወት የመኖር

   ለ. ጥበቃ        መ. ትምህርት የማግኘት

3. ህጻናት መልካም ዜጎች እንዲሆኑ ምን መሆን አለባቸው?

   ሀ. አመለካከቶቻቸው መጥራትና መጎልበት አለበት።

   ለ. ጤናማ ሆነው ማደግ ይኖርባቸዋል።

   ሐ. ከአደጋ መጠበቅ አለባቸው።

   መ. በህይወት መኖር አለባቸው።

4. ‹‹ሞራላቸውንና መንፈሳቸውን የሚያላሽቁ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

   ሀ. ሞራላቸውንና መንፈሳቸውን የሚያጠናክሩ ማለት ነው።

   ለ. ሞራላቸውንና መንፈሳቸውን ከፍ የሚያደርጉ ማለት ነው።

   ሐ. ሞራላቸውንና መንፈሳቸውን የሚጎዱ ማለት ነው።

   መ. ሞራላቸውንና መንፈሳቸውን የሚያበለጽጉ ማለት ነው።

5. ህጻናት መብቶቻቸው በቀላሉ የሚጣሱት ለምንድን ነው?

   ሀ. እድሜያቸውለጋ ስለሆነ        ሐ. ራሳቸውን መከላከል ስለማይችሉ

   ለ. የዳበረ ማህበራዊ ህይወት ስለሌላቸው        መ. ሁሉም መልስ ነው።

### ተግባር አንድ

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ እየተወያያችሁ ማስታወሻ ያዙ። የያዛችሁትን ማስታወሻም በአስተዋጽኦ መልክ አደራጅታችሁ አንቀጽ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

1. ህጻናት ሀገራቸውን እንዲወዱ ምን ምን ስራዎች መሰራት አለባቸው?
2. በአካባቢያችሁ የህጻናት መብት ሲጣስ ብትመለከቱ ምን ታደርጋላችሁ?

ክፍለጊዜ፡ ሦስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ቀጥሎ የተለያዩ ተግበራት ቀርበዋል። ተግባራቱን መምህራችሁ በሚነግሯችሁና በትዕዛዛቱ መሰረት ስሩ።

### ተግባር ሁለት

**"ህጻናት ሲያጠፉ መቀጣት አለባቸው? ወይስ የለባቸውም?" የሚሉትን ሀሳቦች አንደኛውን ደግፋችሁ ሌላይኛውን ተቃውማችሁ በቡድን መስርቱና ተከራከሩ። ክርክሩ ውስጥ ያልተሳተፋችሁ ተከራካሪዎች ያቀረቡት ሀሳብ ምክንያታዊ መሆናቸውና አለመሆናቸው ላይ ሀሳብ በመስጠት ተሳተፉ።**

በክርክር ጊዜ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ስጡ።

- በቂ ዝግጅት ማድረግ
- ዳኞችን መምረጥ
- ከምነደግፈውና ከምንቃወመው ሀሳብ ላይ ያተኩሩ ፍሬሀሳቦችን ብቻ መናገር
- የሚቀርቡ ሀሳቦችን በማስረጃ ማስደገፍ
- ተራን ጠብቆ መናገር
- ለሌላው ሀሳብ ክብር መስጠት
- ለተቃዋሚ ቡድን ሀሳብ ተገቢና በቂ ምላሽ መስጠት

ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**የተለያዩ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው ቀጥለው ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን በትዕዛዛቸው መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።**

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ከዚህ በታች የቀረበውን ስዕል ተመልክታችሁ ስዕሉ ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ በቃል ተናገሩ።
2. ርዕሱን በመመልከት በምንባቡ ውስጥ ምን ምን ሀሳቦች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?



# የሕጻናት መብትና የጉልበት ብዝበዛ

ዓለም አቀፍ የህጻናት መብቶች ስምምነት ሕጻናት ከተለያዩ ጥቃቶች መጠበቅ እንዳለባቸው ይገልጻል። የአለም አገራት ይህንን ስምምነት የአገራቸውን ህግ አካል በማድረግ አጽድቀዋል። በዚህ መሰረት ህጻናት ያለምንም ልዩነት ጥራት ያለው ትምህርት እያገኙ የማደግ መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል። እንደዚሁም ከጥቃት፣ ከእንግልት፣ ከጭንቀት ከአቅም በላይ የሆነ ስራ ከመስራት፣ ከረሀብና ፣ከእርዛት ነጻ ሆነው እንዲያድጉ ሊደረግ ይገባል።

የተለያዩ አካላት በሕጻናት ላይ የመብት ጥሰት በመፈጸም የተለያዩ ጥቃቶችን እያደረሱ ይገኛሉ። ቤተሰብ ደሃ በመሆኑ ጉልበታቸውን ይፈልግና አቅማቸውን ባላገናዘበ ስራ ላይ ያሰማራቸዋል። በዚህ ሰበብ ህጻናት የትምህርት ዕድል ያጣሉ። ሕጻናት በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ከገቡ በቂ ምግብ፣ ልብስ፣ ለኑሮ አመቺ የሆነ አያያዝ በማጣት ለረሃብ ይጋለጣሉ። ከችግሩ ክብደት የተነሳም ቤተሰባቸውን እየረዱ ራሳቸውንም ጭምር ለማኖር ሲሉ እድሜያቸውን በማይመጥኑ የተለያዩ ስራዎች ላይ ተሰማርተው የሚሰቃዩ ህጻናት በርካታ ናቸው። ለምሳሌ በገጠር እድሜንና የአካል ጥንካሬን በሚጠይቁ የግብርና ስራዎች ላይ ህጻናት ተሰማርተው ይታያሉ።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ባነበባችሁት የምንባብ ክፍል የህጻናት መብቶች ምን ምን ናቸው?
2. የተቀረው የምንባብ ክፍል ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

በሌላ በኩል እያወቁ እነዚህን የሕጻናት መብቶች የሚጥሱ ሰዎችም አሉ። ይኸውም በተለያዩ ፋብሪካዎችና በመኖሪ ቤቶች ውስጥ መብታቸውን መጠየቅም ሆነ ማስከበር የማይችሉ ህጻናትን ቀጥረው የሚበዘብዟቸው በርካቶች ናቸው። ከአቅማቸው በላይ የሆኑ ስራዎችን ከማሰራታቸውም በላይ ተገቢ ክፍያም አይከፍሏቸውም። ይህ ሁኔታ በአካልም ሆነ በአእምሮ እድገታቸው ላይ ተጽእኖ ከማሳደሩም በላይ የመማር መብታቸውንም ያደናቅፋል። ከዚህም ሌላ ባንዳንድ አገሮች ህጻናትን በማስገደድ ወይም በማታለል በጦርነት ላይ እንዲሳተፉ የሚመለምሉና አስታጥቀው ወደ ጦርነት የሚልኩም አሉ። ይህ ደግሞ የህጻናትን በህይወት መኖር መብት የሚጻረር ነው።

ህጻናት እንክብካቤ አግኝተው ካደጉ ለራሳቸውም ሆነ ለአገራቸው ጠቃሚ ስራዎችን መስራት ይችላሉ።ለህጻናት የሚደረገው እንካብካቤ ከቤተሰብ ሊጀምር ይችላል። የህዝብና የመንግስት ድርሻም እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም። ህጻናት አገር ተረካቢ የሚሆኑት ከአስተዳደጋቸው ጀምሮ መብቶቻቸው ከተከበሩላቸው ነው። በአካላቸውም ሆነ በሞራላቸው ላይ ከሚፈጸሙ ጥቃቶች መጠበቅ አለባቸው። ህጻናት በመሆናቸው ጥፋት ሊፈጽሙ ይችላሉ። በዚህ አይነት አጋጣሚ ከጥፋታቸው እንዲመለሱ መመከር ይኖርባቸዋል። ሁሉንም ጥፋቶች ለማረም ሲባል መቀጣት የለባቸውም።

የህጻናትን ሞራል መንካት የወደፊት ህይወታቸውን ስለሚያደናቅፍ መሰደብ፣ መደብደብ፣ መናቅና መሳቀቅ አይኖርባቸውም። በተቻለ መጠን በቤተሰባቸው ንብረት እኩል የመጠቀም መብት ሊያገኙ ይገባል። እንክብካቤ እየተደረገላቸውና መብታቸው እየተጠበቀላቸው ከብዝበዛ ነጻ ሆነው ካደጉ የነገ ሀገር ተረካቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ክፍለጊዜ፡ አምስት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በጽሁፍ መልሱ።

1. በአንቀጽ አንድ "በተመሳሳይ" የሚለው ቃል ምን አይነት ሀሳቦችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ዋለ ነው?
2. "ህጻናት ከእርዛት ነጻ ሆነው እንዲድጉ ሊደረግ ይገባል።" ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. "ይህ ደግሞ የህጻናትን በህይወት የመኖር መብት የሚጻረር ነው።" በሚለው ውስጥ "ይህ" የሚለው የትኛውን ለማለት ነው?
4. ህጻናት እንክብካቤ አግኝተው ካደጉ ምን ይሆናሉ?
5. "አለም አቀፍ የህጻናት መብቶች ስምምነት ህጻናት ከምን ከምን ሁኔታዎች መጠበቅ አለባቸው" በማለት ይደነግጋል?
6. በአካባቢያችሁ የህጻናት መብቶች አጠባበቅ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ገምግማችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ለ. በ ‹‹ሀ ››ስር የቀረቡት የምንባቡ አንቀጾች የሚያስተላልፉትን መልዕክት በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት አማራጮች በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አንቀጽ አንድ | ሀ. ስለአለምአቀፍ የህጻናት መብቶች ስምምነት |
| 2. አንቀጽ ሁለት | ለ. ስለህጻን ምንነት |
| 3. አንቀጽ ሶስት | ሐ. የህጻናት ሰብአዊ መብት መከበር ጥቅም |
| 4. አንቀጽ አራት | መ. ስለህጻናት ሰብአዊ መብት መጠበቅ |
| 5. አንቀጽ አምስት | ሠ. በህጻናት ላይ ስለሚፈጸሙ ሰብአዊ ጥሰቶች |

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

ሐ. ከዚህ በታች የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለጥያቄዎቹ ያነበባችሁትን ምንባብ መሰረት አድርጋችሁ ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልሱ።

1. ከምንባቡ አንጻር የህጻናት መብት ጥሰት የማይገለጽበት ተግባር የትኛው ነው?

   ሀ. ሞራላቸውን መንካት ሐ.የወላጆቻቸውን ሀብት እኩል መጠቀም

   ለ. ትምህርት እንዲማሩ ዕድል መስጠት መ. የጉልበት ስራ ማሰራት

2. ከምንባቡ አንቀጾች ህጻናት ለሚያጠፉት ጥፋት ሁሉ መቀጣት የለባቸውም በማለት የሚገልጸው አንቀጽ የትኛው ነው?

   ሀ. አንቀጽ አንድ ሐ. አንቀጽ ሶስት

   ለ. አንቀጽ ሁለት መ. አንቀጽ አራት

3. በአራተኛው አንቀጽ "በዚህ አይነት አጋጣሚ" ሲል የትኛውን አጋጣሚ ለማለት ነው?

   ሀ. የጉልበት ስራ ሲሰሩ ሐ. በሀይል ሲቀጡ

   ለ. ጥፋት በሚያጠፉበት ጊዜ መ. ሲመናጨቁ

4. በአራተኛው አንቀጽ "እነዚህን የህጻናት መብቶች..." በሚለው የትኞቹን የህጻናት መብቶች ለማለት ነው?

    ሀ. በህይወት መኖር — ሐ. በአእምሮ መበልጸግ

    ለ. ትምህርት መማር — መ. ከአቅማቸው በላይ ያለመስራት

5. "ይህ ደግሞ የህጻናትን በህይወት የመኖር መብት የሚጻረር ነው።"ሲል ምን ማለቱ ነው?

    ሀ. ህጻናት ላይ ጉዳት ያደርሳል።

    ለ. ህጻናት በህይወት የመኖር መብትን ይጋፋል።

    ሐ. ህጻናት በህይወት እንዲኖሩ ያደርጋል።

    መ. ጥሩ ህይወት እንዳይኖሩ ያደርጋል።

### ተግባር ሦስት

በየአካባቢያችሁ የህጻናት መብቶች አጠባበቅ ምን እንደሚመስል በቡድናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን በአንቀፅ አደራጅታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

**ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ የሚል መልመጃ ቀጥሎ ቀርቧል። መልመጃውን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ፡፤**

### መልመጃ ሰስት

ሀ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ትርጉም ስጡ።

1. የተለያዩ አካላት በሕጻናት ላይ የመብት ጥሰት በመፈጸም የተለያዩ ጥቃቶችን እያደረሱ ይገኛሉ።
2. ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል የህጻናትን መብት ለማስከበር በዚህ ህግ የመገዛት ግዴታ አለበት።
3. ይህ ደግሞ የህጻናትን በህይወት መኖር መብት የሚጻረር ነው።
4. ሁሉንም ጥፋቶች ለማረም ሲባል መቀጣት የለባቸውም።
5. እንክብካቤ እየተደረገላቸውና መብታቸው እየተጠበቀላቸው ከብዝበዛ ነጻ ሆነው ካደጉ የሀገር ተረካቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
6. የህዝብና የመንግስት ድርሻም እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም።

ለ. በ‹‹ሀ››ስር ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ከ‹‹ለ›› ስር በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ብስል | ሀ. ምኞት |
| 2. ጠንካራ | ለ. ጎጂ |
| 3. አድልኦ | ሐ. ልማት |
| 4. ማጽደቅ | መ. ጥሬ |
| 5. ግዴታ | ሠ. ደካማ |
| 6. ነጻነት | ረ. እኩልነት |
| 7. መናቅ | ሰ. ፍላጎት |
| 8. ስቃይ | ሸ. ባርነት |
| 9. ጠቃሚ | ቀ. መከበር |
| 10. ጥፋት | በ. ማፍረስ |

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

**ቀጥለው የተለያዩ ተግባራት ቀርበዋል። ተግባራቱን በትዕዛዛቸው መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።**

### ተግባር አራት

ሀ. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በአካባቢያችሁ የሚተገበሩ የህጻናት መብቶችን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

ለምሳሌ፡- ትምህርት መማር

ለ. ‹‹የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ›› የሚለውን ምንባብ ደግማችሁ በማንበብ የየአንቀጾቹን ዋና ዋና ሀሳቦች በቅደምተከተል ጻፉ።

ሐ. ከላይ የያዛችሁትን የአንቀጾችን ዋና ዋና ሀሳቦች መነሻ በማድረግ በራሳችሁ አገላለጽ የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ የሚሳይ አንድ አንቀጽ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ፈሊጣዊ አነጋገሮች፡- ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከሁለት ቃላት የሚመሰረቱ ሲሆን ትርጉሙም ከሁለቱ ቃላት ትርጉም ውጪ የሆነ ነው።

ምሳሌ፡- ሆደ ሰፊ ——ቻይ፣ ታጋሽ

ልበ ሙሉ——ደፋር፣ የማይፈራ፣ በራሱ የሚተማመን

ሆድና ጀርባ——የማይስማማ

### መልመጃ አራት

ሀ. የምታውቋቸውን አምስት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ጻፉና ፍቺያቸውን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**በዚህ ትምህርት ክፍል አገልግሎታዊ ዓረፍተነገሮችን እንድትጠቀሙ የሚረዳ መልመጃ ስለቀረበ በትኩረት ስሩ።**

### መልመጃ አምስት

**በሰንጠረዡ የቀረቡትን ቃላት በማገጣጠም ሀተታ፣ ጥያቄ፣ ትእዛዝ እና አጋኖኣዊ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሁላችንም | ከክፍል ተማሪዎች | ተመረቀ |
| ኀበዙ ጫላ | በማራቶን ሩጫ | ማክበር አለባቸው |
| የቤት ስራቸሁን | የትምህርት ቤቱን ስነምግባር | ዘብ መቆም አለብን |
| አትሌቱ | ያለ | ስሩ |
| ተማሪዎች | በምን ትምህርት | ጉድ ነው |
| ወንድምህ | በጥንቃቄ | አንደኛ ወጣ |
| እንዴት | ለሰላም | ሪከርድ ሰበረ |

# ምዕራፍ ስምንት

## ሰላም

### የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- ጽሁፍን አዳምጣችሁ ትተነትናላችሁ፤
- የሰላምን አስፈላጊነት ታብራራላችሁ፤
- የጽሁፉን ፍሬ ሀሳብ አንብባችሁ ማጠቃለያ ትሰጣላችሁ፤
- በጽሁፍ ውስጥ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን ትጠቀማላችሁ፤
- በጽሁፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፤
- ውስብስብ አረፍተነገሮችን ትመሰርታላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ የትምህርት ክፍል የተለያዩ የማዳመጥ መልመጃዎች ቀርበዋል። መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ጽሁፍ መሰረት አድርጋችሁ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ስሩ።

## ሰላም በቤተሰብ መካከል

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ሰላም በቤተሰብ ውስጥ እንዴት ይፈጠራል?
2. ሰላምን ማምጣት የሚችለው ማን ነው?
3. ርዕሱን ተመልክታችሁ ጽሁፉ ስለምን እንደሆነ ገምቱ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከአዳመጣችሁት ምንባብ ሰላም ምን መሆኑን ተረዳችሁ?
2. የሰላም እጦት በሰው ልጆች ህይወት ላይ የሚያመጣቸው ችግሮች ምን ምን ናቸው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት አድርጋችሁ በጽሁፍ መልሱ።**

1. ሰላም በቤተሰብ መካከል ከጠፋ ምን ሊከሰት ይችላል?
2. ሰላምን የሚያደፈርሱ ተግባራት ምን ምን ናቸው?
3. የሰላም ባለቤት ማን ነው ትላላችሁ?
4. ወላጆች የልጆቻቸውን መልካም ስነምግባር ማየት ከፈለጉ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

**ለ. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት አድርጋችሁ ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ትርጉም ስጡ።**

1. የሚሹት
2. ጥረት
3. ለማዳ
4. የሚታወክ
5. ለማንገስ
6. ስብዕና
7. በማነጽ
8. የገርነት
9. ዕገዛ
10. ሚዛን

### ተግባር አንድ

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን እየተወያያችሁ ማስታወሻ ያዙና የማስታወሻውን ፍሬ ሀሳብ በቃል አቅርቡ።**

1. የመገናኛ ብዙኃን ሰላምን በማምጣቱ ሂደት ምን ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ?
2. በቤተሰብ አባላት መካከል ግጭትን በማስወገድ እርስበርስ መተሳሰብና መከባበርን ማስፈን የሚቻለው እንዴት ነው?

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ያዳመጣችሁትን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ተግባራትና በአካባቢችሁ ያሉ አዛውንቶች ጠይቃችሁ የምትሰሯቸው ተግባራት ቀርበዋል። ተግባራቱን በመመሪያዎቹ መሰረት በትኩረት ስሩ።

### ተግባር ሁለት

**ሀ. ያዳመጣችሁትን መሰረት አድርጋችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።**

1. ‘ሰላም ለማንገስ የሰዎች ስብዕና መከበር አለበት’ ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. የማህበረሰቡን ሰላም ሊያሳጡ የሚችሉ ተግባራት ምን ምን ናቸው?
3. ሰላም እንዳይኖር የሚያደርጉ አካላት እነማን ናቸው?
4. ያዳመጣችሁት ምንባብ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?

## ተግባር ሶስት

**ከዚህ በታች የቀረቡላችሁን ጥያቄዎች በየጥያቄዎቹ የተሰጠውን መመሪያ ተከትላችሁ ስሩ።**

1. በቤተሰባችሁ ዘንድ አለመግባባት ቢፈጠር ምን ታደርጋላችሁ? ተወያዩበት።
2. ከምንባቡ አንጻር ቤተሰቦቻችሁ በስነምግባር ታንጻችሁ እንድታድጉ ያደረጉላችሁን አስተዋጽኦ ገምግሙ።
3. ወላጆች ልጆቻቸው በመልካም ስነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ማድረግ ባለባቸው ተግባራት ላይ በጥንድ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።
4. በአካባቢያችሁ አለመግባባትን ለማስወገድ ጥቅም ላይ የሚውሉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶችን አዛውንቶችን ጠይቁ። ያገኛችሁትን መረጃ ለቡድን አባላታችሁ ተራ በተራ ተናገሩ። ከዚያም ለቡድን አባላቱ ከቀረቡት አንዱን መርጣችሁ ለክፍሉ ተማሪዎች በቃል አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

## ተግባር አራት

**ሀ. ሰላምን እንዴት ማምጣት እንደሚቻል የሰነዜጋ መምህራችሁን ጠይቁ። ከመጻህፍትም አንብቡ፡ ባገኛችኋቸው መረጃዎች ላይ በቡድንም ተወያዩ። የደረሳችሁበትንም የጋራ ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።**

ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ምንባብ እና መልመጃዎች አንብባችሁ እንድትረዱ የሚያግዙ ናቸው። ስለዚህ ምንባቡን በትኩረት በማንበብ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ።**

## የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. ስዕሉ ምንን ይወክላል?

ለ. ርዕሱን ተመልክታችሁ በምንባቡ ውስጥ ምን ምን ሀሳቦች ይነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ሐ. ሰላም ዋጋው እንዴት ይገለጻል?



## ሰላም

ሰላም ምንድን ነው? ሰላም በስምምነትና በአንድነት አብሮ መኖር ማለት ነው። ሰላም ማለት ‹‹ፍጹም፣ ጤና፣ ዕረፍት፣ ዕርቅ፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ደኅንነት፣ ተድላ፣ ደስታ፣ ሰላምታ፣ የቡራኬ የምርቃት ቃል፣ ሰው ሲገናኝ ሲለያይ የሚለው የሚናገረው ወይም የሚጽፈው ነው›› በማለት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የሰላምን ፍቺ በእንዲህ መልኩ ገልጸውታል።

ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት ነው። ለዚህም ነው ሰዎች ሲገናኙ ቅድሚያ ስለሰላማቸው ሁኔታ የሚጠያየቁት። ጠዋት ከእንቅልፋቸው ተነስተው “በሰላም አውለኝ”፣ ማታ ሲተኙም “በሰላም ያዋልከኝ በሰላም አሳድረኝ” ብለው ምስጋናቸውን የሚገልጹትም የሰላምን ትልቅ ዋጋ በመረዳት ነው። እናም ሁሉም ሰው ሊባል በሚችል መልኩ ሰላም በህይወቱ ላይ ትልቅ ውድ ዋጋ ያለው ነገር መሆኑን ይገነዘባል፣ ለሰላሙም ዘብ ይቆማል። ስለዚህ የሰው ልጆች በምንኖረው ሕይወት ውስጥ እጅጉን ከሚያስፈልገን ነገር ዋነኛው ሰላም ነው። ፍጥረታት እንዲኖሩ የሚያስፈልገው ሰላም ነው፣ ያለ ሰላም ልንኖር አንችልም።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ሀ. ሰላም ምንድን ነው?

ለ. ሰዎች የሰላምን ዋጋ ስለተረዱ ምን ይላሉ?

ሐ. የተቀረው የምንባብ ክፍል ስለሰላም ምን የሚያወሳ ይመስላችኋል? ገምቱ።

ሆኖም ከብዙዎች በተቃራኒ ሰላምን ለማደፍረስ የሚተጉ ኃይሎችም አሉ። በእነዚህ አይነት ሰዎች የተነሳ በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚገኙ ህዝቦች ሰላምና መረጋጋት እንዲርቃቸውና በአንጻሩ ጦርነት፣ የእርስ በርስ ግጭት፣ ሽብርተኝነትና ወንጀል ተንሰራፍተው የሰዎች ዕለታዊ ኑሮ እንዲታወክ ምክንያት ይሆናሉ። በሰላም እጦት ምክንያት የሚሊዮኖች ህይወት ጠፍቷል፣ የንብረት ውድመትም ተከስቷል፣ እየተከሰተም ነው። የ2017 አለማቀፍ የሰላም ዘገባ እንደሚያሳየው በአለም አቀፍ ደረጃ በሰላም እጦት ምክንያት በየዓመቱ 13 ነጥብ 6 ትሪሊየን ዶላር ኪሳራ እየተስተናገደ ነው። በግለሰብ ደረጃ በእያንዳንዱ ቀን አንድ ሰው ማግኘት ከሚገባው ውስጥ 5 ዶላር ያጣል ማለት ነው። ባጠቃላይ የሰላም መናጋት ሞት፣ አካላዊ ጥቃት፣ መፈናቀል፣ ስደት፣ ወረርሽኝና ርሃብ እንዲነግሱ በር ይከፍታል።

ክፍለጊዜ፡ አምስት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ባነበባችሁት ጽሁፍ መሰረት በጽሁፍ መልሱ።

1. የአንደኛው አንቀጽ ሀይለቃል ምንድን ነው?
2. የሁለተኛው አንቀጽ ፍሬ ሀሳቡ ምንድን ነው?
3. ሰላምን ሊተኩ የሚችሉ ቃላትን ዘርዝሩ።
4. በሶስተኛው አንቀጽ "በእነዚህ አይነት ሰዎች..." የሚለው የትኞቹን ሰዎች ለማለት ነው?
5. ሰዎች ሁልጊዜ ስለሰላም የሚጠያየቁት ለምንድን ነው?
6. "ለሰላሙም ዘብ ይቆማል" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. በ ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡት የምንባቡ አንቀጾች የሚያስተላልፉትን መልዕክት በ ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት መልዕክቶችን በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አንቀጽ አንድ | ሀ. በሰላም እጦት የሴቶችና ህጻናት ጉዳት |
| 2. አንቀጽ ሁለት | ለ. ዜጎቻቸው ምን አይነት ችግር ውስጥ እንዳሉ |
| 3. አንቀጽ ሶስት | ሐ. ስለሰላም ምንነት |
| 4. አንቀጽ አራት | መ. ሰላም ለሰው ልጅ መሰረታዊ ነገር መሆኑን |
| | ሠ. የሰላም ዕጦት የሚስከትለው ችግር |

**ሐ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት የምርጫ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. በምንባቡ መሰረት የትኛው ሀሳብ ትክክል ነው?

   ሀ. ሰላም ፍቅር ነው　　ለ. ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት ነው

   ሐ. ሰላም ትልቅ ዋጋ አለው　　መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

2. ሰላም በሌለበት ሰዓት የበለጠ ችግር ውስጥ የሚገቡት የትኞቹ የሕብረተሰብ ክፍሎች ናቸው?

   ሀ. ወጣቶች　　ሐ. ሴቶች　　ለ. ህጻናት　　መ. ለ ና ሐ

3. የሰላም እጦት ምን ምን ማህበራዊ ቀውሶችን ያስከትላል?

   ሀ. ሰዎች ከፍተኛ የስነልቦና ቀውስ ውስጥ ይገባሉ።

   ለ. ህዝቡ ለሞትና ለስደት ይዳረጋል።

   ሐ. የህይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት ይከሰታል።

   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።

4. ሰላም ምንድን ነው?

   ሀ. በስምምነትና በአንድነት መኖር ማለት ነው።

   ለ. ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት ነው።

   ሐ. ሰላም ፍቅር ማለት ነው።

   መ. ሁሉም መልስ ይሆናል።

## ተግባር አምስት

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ማስታወሻ እየያዛችሁ በጥንድ ተወያዩ።ከዚያም የያዛችሁትን ማስታወሻ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አቅርቡ።**

1. የሀገርን ሰላም የመጠበቅ ኃላፊነት የማነው ትላላችሁ? ለምን?

2. በአንድ ሀገር ውስጥ የሰላም አለመኖር የሚያስከትለውን ችግር በተመለከተ ተወያዩና በተወካያችሁ በኩል ለክፍሉ አቅርቡ።
3. አካባቢያችሁ ሰላም እንዲሆን ነዋሪዎች እየፈጸሟቸው ያሉትን ተግባራት በመገምገም የመጡትን ውጤቶች ተንትኑ።

ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ከዚህ በታች ለተዘውታሪ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት የሚል መልመጃ እና ማስታወሻ ቀርቧል። የቀረበላችሁን ማስታወሻ ካነበባችሁ በኋላ መልመጃውን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

**ተዘውታሪ ቃላት፡-** እነዚህ ቃላት በዕለት ተዕለት የተግባቦት ሂደት ውስጥ የምንጠቀምባቸው ቃላት ናቸው። ለምሳሌ፡- ምግብ፣ ገበያ፣ መጽሀፍ፣ ጠዋት፣ ሰኞ ወዘተ ናቸው።

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ተዘውታሪ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

1. ሰላም በስምምነትና በአንድነት <u>አብሮ</u> መኖር ማለት ነው።
2. ሰላምን ለማደፍረስ <u>የሚተጉ</u> ኃይሎች ሊኖሩ ይችላሉ።

3. በሰላም እጦት የሚሊዮኖች ህይወት መጥፋትና የንብረት <u>ውድመት</u> ተከስቷል፣ እየተከሰተም ነው።
4. ሽብርተኝነትና ወንጀለኝነት <u>ተንሰራፍተው</u> የሰዎችን ዕለታዊ ኑሮ እንዲታወክ ምክንያት ሆነዋል።

## መልመጃ አራት

ለ. ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት 'ሰላምን የተመለከቱ' እና 'ሰላምን የማይገልጹ' በማለት ለይታችሁ ጻፏቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተድላ | ረብሻ | ረሀብ | እርዛት | ግጭት |
| ምስጋና | ጥላቻ | መተሳሰብ | መረጋጋት | ወንጀል |
| ጭንቀት | አንድነት | ደህንነት | መውደም | ስድብ |
| ፍቅር | ስደት | መፈናቀል | ሽብርተኝነት | ጥቃት |
| ቀውስ | ዕረፍት | ዕርቅ | ጤና | ምርቃት |

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

ከዚህ በታች በሰላም ላይ ማጠቃለያ መጻፍና ስርአተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ መጠቀም የሚል መልመጃ ቀርቦላችኋል። ተግባሩንና መልመጃውን በመመሪያዎቹ መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## ተግባር ስድስት

ሀ. ከዚህ በታች ከቀረቡት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ አንቀጽ ጻፉ።

1. በቤተሰብ መካከል ሰላም ማምጣትን በተመለከተ

2. የሰላምን አስፈላጊነት በተመለከተ

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

### ማስታወሻ

**ስርዓተ ነጥቦችን በጹሁፍ ውስጥ መጠቀም**

**ስርዓተ ነጥቦች** በንግግር ቋንቋ ወቅት በድምጽ አወጣጥ፣ በፊት ገጽታ፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ ወዘተ እየታጀበ የሚቀርበውን ሀሳብ በጽሑፍ ውስጥ ስሜቱን ሳይለቅ እንዲቀርብ ለማድረግ ያገለግላሉ። ስርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ አለመጠቀም የፍቺ ለውጥ ከማስከተሉም በላይ በጽሑፍ የሚቀርበው ሀሳብም የተሟላ እንዳይሆን ያደርገዋል። ስለሆነም ስርአተነጥቦችን ስንጠቀም መርጠንና በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል። በአማርኛ ቋንቋ አገልግሎት የሚሰጡ የተለያየ የስርዓተነጥብ አይነቶች አሉ። ከነዚህ መካከልም ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝ (፥)፣ አራት ነጥብ(።)፣ የጥያቄ ምልክት(?)፣ ቃለ አጋኖ (!) ወዘተ ይጠቀሳሉ።

ለምሳሌ

**አራት ነጥብ (።)**

በአረፍተ ነገር ውስጥ ሀሳብ ለመቋጨት ያገለግላል።

ሀ. ዋቅቶላ ቤተሰቦቹ ጋ ሄደ።

ለ. ደራርቱ ትላንትና ከአምቦ መጣች።

**ነጠላ ሰረዝ/፣/**

በአረፍተነገር ውስጥ በተከታታይ ለተመሳሳይ ተግባር የገቡ ቃላት ወይም ሀረጎችን ለመለየት ያገለግላል።

ለምሳሌ

ሀ. እናቴ ሽንኩርት፣ ባቄላ፣ ቃሪያ፣ ቲማቲምና በቆሎ እሸት ገዝታ መጣች።

ለ. ጠዋት ፊቴን ታጥቤ፣ ቁርሴን በልቼ፣ ቦርሳዬን ይዤ ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ።

**ጥያቄ ምልክት/?/**

ምላሽ የሚሻ ሀሳብ ያለው አረፍተነገር መጨረሻ ላይ የሚገባ ምልክት ነው።

ለምሳሌ

ሀ. አንቺ መቼ ትመጭያለሽ?

ለ. ወዴት እየሄድክ ነው?

## መልመጃ አምስት

**ሀ. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተነገሮች የተጓደሉትን ሥርዓተ ነጥቦች በማሟላት ደግማችሁ ጻፏቸው።**

ለምሳሌ፡- ፌትያ ሁልጊዜ ጠዋት መጸዳጃ ቤት ሄዳ፣ ፊቷን ታጥባ፣ ቁርሷን በልታ ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለች።

1. መስከረም ወንዞች የሚቀንሱበት አበቦች የሚፈኩበት መስኩ የሚለመልምበትና ትምህርት ቤቶች የሚከፈቱበት ወር ነው
2. ሞቱማ እግር ኳስ መጫወት መጽሀፍ ማንበብ በእግር መጓዝና መዝናናት ይወዳል

3. ወደ ፊንፊኔ የሄዱት መቼ ነው
4. ወጣ ብለሽ ለምን ከጓደኞችሽ ጋር አትጫወቺም
5. ሂድና ዳቦ ሽንኩርት ቃሪያ እና ጎመን ገዝተህ ና

ለ. ቀጥሎ በቀረበው አንቀጽ የተጓደሉትን ስርኣተ ነጥቦች አሟሉ።

እናቴ ታታሪ ነጋዴ ነች ሁልጊዜ በአካባቢችን የሚገኙ የቅርብ ወረዳ ገበያዎች እየተዘዋወረች ትነግዳለች ከዚያ ስትመለስ ደግሞ እኛን ትጎበኘንና ወደ ሱቋ ትመለሳለች ከምትነግዳቸው የዕቃ አይነቶች መካከል ጥቂቶቹ ጨርቃጨርቅ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ አልባሳት ጫማዎችና የጸጉር ቅባቶች በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ከዚህ በታች ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን የተመለከተ ማስታወሻና መልመጃ ቀርቧል። መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን ማብራሪያና ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ የቀረበውን መልመጃ ስሩ።

### ውስብስብ አረፍተነገሮችን መመስረት

ማስታወሻ

**ውስብስብ አረፍተነገር**

ውስብስብ አረፍተነገር በውስጡ አንድ እና ከአንድ በላይ የሆነ ጥገኛ ሀረግ ያለው የአረፍተነገር አይነት ነው። ይህም ማለት ውስብስብ አረፍተነገር ከአንድ በላይ ግስ ወይም ማሰሪያ አንቀጽ ያለው የአረፍተነገር አይነት ነው ማለት ነው።

ምሳሌ፡-

ጋሩማ ትምህርት ቤት ሄዶ መጣ።

## መልመጃ ስድስት

ሀ. ከላይ የቀረበውን ምሳሌና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ አምስት አምስት ውስብስብ አረፍተነገሮችን መስርቱ።

ለ. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስብስብ አረፍተነገር የሆኑትን ለዩ።

1. አበበ ምሳውን በልቶ ሄደ።
2. እሱ ፊቱን ታጥቦ ቁርሱን በላ።
3. ታላቅ እህቴ ልብስ ገዛችልኝ።
4. ጓደኞቼ በትምህርት ጎበዝ ናቸው።
5. ዘመዶቼ ለልደት ቀኔ ስጦታ ገዝተው ሰጡኝ።
6. ዛሬ ስልክ ተደውሎልኛል።
7. ልብሶቼንና ጫማዎቼን አጥቤ እረፍት ወሰድኩኝ።
8. የቤት ስራዬን ሁልጊዜ ጠንክሬ ሰርቼ ውጤት ማምጣት እፈልጋለሁ።
9. ዛሬ ወደ ትምህርት ቤት በመኪና ሄድኩኝ።
10. እህቴ ዘንድሮ የእሬቻ በዓልን ልታከብር ነው።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የአየር ንብረት

### የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- የጽሁፍን ሀሳብ በማዳመጥ ዋጋ ትሰጣላችሁ፤
- የአየር ንብረት ጽንሰሀሳብን አንብባችሁ ትረዳላችሁ፤
- ለተለያዩ አላማዎች ምንባብ ታነባላችሁ፤
- የምስሎችን ዝርዝር ማብራሪያዎች ትጽፋላችሁ፤
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን አገባባዊ ፍቺ ትጠቀማላችሁ፤
- ውስብስብ አረፍተነገሮችን ትመሰርታላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ መልመጃዎች ቀርበዋል። በትኩረት በማዳመጥ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ ስሩ።

### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የአካባቢያችን ሙቀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው ለምን ይመስላችኋል?
2. የአየር ንብረት ምን ማለት ነው?

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የአየር ንብረት ለውጥን እንዴት መቀነስ ይቻላል?
2. የአየር ንብረት ለውጥን እነማን ይከላከሉ?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን መሰረት በማድረግ በቃል መልስ ስጡ።

1. የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተላቸው ተጽዕኖዎች ምን ምን ናቸው?
2. የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ ይገባቸዋል?
3. ደኖች የተቃጠለ ጋዝን በምናቸው ይይዛሉ?
4. ካርቦን ወደ አየር እንዲለቀቅ የሚያደርጉ ተግባራት ምን ምን ናቸው?
5. የደኖች መመናመን ለምርት መቀነስ ሰበብ የሚሆነው እንዴት ነው?
6. ለአየር ንብረት ለውጥ መከሰት ዋነኛ ምክንያት ምን ይመስላችኋል?

### ተግባር አንድ

ሀ. በአካባቢያችሁ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚተገበሩ ተግባራትን ውጤታማነታቸውን ገምግማችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ለ. ለሀገራችን አሳሳቢ የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ዘላቂነት ባለው መልክ ለመቀነስ በግላችሁ ምን እንደምታደርጉ በጥንድ ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

### ክፍለጊዜ ሁለት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መነሻነት ተግባራት ቀርበዋል። ተግባራቱን ትኩረት ሰጥታችሁ አከናውኑ።

## ተግባር ሁለት

ሀ. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት አድርጋችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በተወካያችሁ አማካኝነት በቃል አቅርቡ።

1. ሲነበብላችሁ ያዳመጣችሁት ጽሁፍ ፍሬ ነገር ምንድን ነው?
2. በደን መጨፍጨፍ ምክንያት ኢትዮጵያ ላይ የታዩ ክስተቶች ምን ምን ናቸው?
3. የካርቦን መጨመር ከደን መጨፍጨፍ ጋር እንዴት ይያያዛል?

ለ. "የአየር ንብረት ለውጥ በሀገራት ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል" ለዚህ መንስኤው ማነው? የበለጸጉ ሀገራት ወይስ ታዳጊ ሀገራት?አንደኛውን ደግፋችሁ ሌላውን በመቃወም ቡድን መስርታችሁ ተከራከሩ። ክርክሩ ውስጥ ያልተሳተፋችሁ ተከራካሪዎች ያቀረቡት ሀሳብ ምን ያህል ምክንያታዊ መሆን አለመሆናቸው ላይ አስተያየት በመስጠት ተሳተፉ። በክርክሩ ወቅትም በምዕራፍ ሰባት ክፍለ ጊዜ ሶስት ስር የተቀመጡትን የክርክር ማድረጊያ ነጥቦችን ተከተሉ።

## ተግባር ሶስት

ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ እየተወያያችሁ። ማስታወሻ በአስተዋጽኦ መልክ ያዙ። የያዛችሁትን ማስታወሻም በቃል አቅርቡ።

1. በክልላችን የአየር ብክለት ተጽዕኖ ለመቀነስ ምን ምን ተግባራት እየተፈጸሙ ናቸው?

2. የአየር ብክለትን ለመቀነስ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ምን ምን ናቸው?
3. በምንባቡ ውስጥ የአየር ንብረትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ናቸው ተብለው የተጠቆሙ የመፍትሄ ሀሳቦች በአካባቢያችሁ በትክክል የሚተገበሩ መሆናቸውን በመገምገም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ክፍለጊዜ ሦስት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ከዚህ በታች የቀረቡት ምንባብ እና መልመጃዎች የአንብቦ መረዳት ክሂላችሁን እንድትጠቀሙ የሚረዱ በመሆናቸው ጥያቄዎቹን በትኩረት በመስራት መልስ ስጡ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ከዚህ በታች የቀረበውን ስዕል በመመልከት ስዕሉ ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ስለአየር ብክለት ምን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
3. ርዕሱን በመመልከት በምንባቡ ውስጥ ምን ምን ሀሳቦች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?



# የአየር ብክለት

የአየር ብክለት በአለማችን እጅግ አሳሳቢ ከሆኑ ጉዳዮች ዋነኛው ነው።በእኛም ሀገር ቢሆን የአየር ብክለት መዘዝ በሀገራችን ህዝቦች ላይ ብርቱ ክንዱን በማሳረፍ ላይ ይገኛል። በክልላችን ኦሮሚያም ይህ ችግር ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ በቅርብ ጊዜ ካጋጠሙት አደጋዎች መረዳት ይቻላል። የአየር ብክለት በክልላችን ምን አይነት ተጽዕኖ እንዳስከተለ፣ ይህንን አሳሳቢ ችግር ለመቅረፍም የክልላችን ህዝቦች ምን ምን ተግባራትን እየፈጸሙ እንዳሉ በዝርዝር እንመለከታለን።

የአየር ብክለት በክልላችን የተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ተጽዕኖዎችን አስከትሏል። ከነዚህም የዝናብ ወቅትን ማዛባት ዋነኛው ነው። ይህም ማለት ወቅቱን ጠብቆ መዝነብ የነበረበት ዝናብ ዘግይቶ ወይም ቀድሞ ሲዘንብ ማለት ነው። ይህ ደግሞ በተለይም በግብርናው ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፣ በማሳደርም ይገኛል። ወቅቱን ጠብቆ መዝነብ የነበረበት ዝናብ ወቅቱን አሳልፎ ወይም ዘግይቶ በመዝነብ የዘር ወቅትን ያዛባል።ይህ ደግሞ የግብርናው ምርት እንዲቀንስ ያደርጋል። ይህም አርሶአደሩን ለምግብ እጥረት ይዳረጋል። በተዘዋዋሪም በከተማ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎችም በቂ የሆነ የምግብ እህል አቅርቦ እንዳያገኙ ያደርጋል።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የአየር ንብረት ለውጥ በክልላችን የፈጠራቸውን ተጽዕኖዎች ዘርዝሩ።
2. ወቅቱን ጠብቆ የማይዘንብ ዝናብ ምን ያስከትላል?

በተጨማሪም በአርብቶ አደርነት የሚተዳደሩ የክልላችን የህብረተሰብ ክፍሎችም የዚህ ገፈት ቀማሽ ናቸው። በአየር ብክለት ምክንያት በቂ ዝናብ

ባለመዝነቡ እንስሳቶቻቸው በቂ የግጦሽ ሳር አያገኙም። ይህ ደግሞ እንስሳቶቻቸው በሚፈለገው መጠን እንዳይራቡ ተጽዕኖ አሳድሯል። በርካታ እንስሳትም እንዲሞቱ ይሆናል፤ የስጋና ወተት ምርታቸውም ይቀንሳል። ይህም በአርብቶ አደሩ ህይወት ላይ ይህ ነው የማይባል አኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ አስከትሏል። ለዚህም በክልላችን ባሉ የባሌ ቆላማ አካባቢዎች፣ ጉጂ፣ ቦረና፣ በምስራቅ ሸዋ ፈንታሌ ተደጋጋሚ የሆኑ የድርቅ አደጋዎች ማሳያዎች ናቸው።

የአየር ብክለት የደቀነብንን አደጋ ለመቀነስ ሁሉን አቀፍ ርብርብ በመደረግ ላይ ይገኛል። ከነዚህም በመላው የክልላችን አካባቢዎች በተለይም ይህ ችግር የሚጠነክርባቸው አካባቢዎች የተራቆቱና ተዳፋት የሆኑ መሬቶች ላይ እርከን በመስራት ውኃ እንዲያቁሩ ተደርገዋል።እንዲሁም በየአመቱ በክልላችን እጅግ ብዙ ችግኞች እየተተከሉ ይገኛሉ። የተተከሉትም ችግኞች በአግባቡ ጸድቀው እንዲያድጉ ጠንካራ ጥበቃና አንክብካቤ እየተደረገላቸው ነው። በተጨማሪም በየቤታችና በየአካባቢችን የአየር ብክለትን ለመቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራት እየተተገበሩ ናቸው። ከነዚህም መካከል፡-በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ካርቦንን ከሚያመነጩ የሀይል ማግኛ መንገዶች እንዲላቀቁና በምትኩ ታዳሽ የሀይል ምንጮችን እንዲጠቀሙ ተደርገዋል። የሚቀጣጠሉ ነገሮችን ከማቃጠል እንዲበሰብሱ በመደረግ ላይ ናቸው።

ባጠቃላይ የአየር ብክለት የሚያስከትለውን ችግር በመገንዘብ ማህበረሰቡን ማስተማር መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው። ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በየአካባቢው ችግኞችን መትከል፣ ደኖችን መንከባከብ ልማዱ ሊያደርገው ይገባል። ይህም በአየር ብክለት ምክንያት ወደፊት የሚያጋጥመንን አደጋ ያስቀርልናል።

ክፍለጊዜ አራት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።**

1. ለአየር ብክለት መንስኤ የሚሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. በአየር ብክለት ምክንያት ይበልጥ ተጎጂ የሚሆኑት እነማን ናቸው?
3. የአየር ብክለት በግብርና ምርት ላይ ያስከተላቸውን ተጽዕኖዎች ዘረዝሩ።

**ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. "ይህ ችግር ምን ያህል አሳሳቢ..." በሚለው ውስጥ "ይህ ችግር" የሚለው የትኛውን ችግር ለማለት ነው?

   ሀ. የግብርና ምርት መቀነስ　　ሐ. የአየር ብክለት

   ለ. የእንስሳት እርባታ መቀነስ　　መ. የተሽከርካሪዎች ብዛት

2. "ለዚህም በክልላችን ባሉ የባሌ ቆላማ አካባቢዎች..." በሚለው "ለዚህም" የሚለው ምን አይነት ሀሳብን ለመግለጽ ነው?

   ሀ. ተጨማሪ ሀሳብን　　ለ. ምሳሌ የሚሆን ሀሳብን

   ሐ. ተቃራኒ ሀሳብን　　መ. ዝርዝር ሀሳቦችን

3. በአየር ብክለት የበለጠ ተጎጂ የማይሆኑት የትኞቹ ናቸው?

   ሀ. የህዝብ ብዛታቸው ከፍተኛ የሆኑ ከተሞች

   ለ. በማደግ ላይ ያሉት ሀገራት

   ሐ. ያደጉት ሀገራት

   መ. አነስተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች

4. የአየር ብክለትን ለመቀነስ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች የሚዳስሰው አንቀጽ የትኛው ነው?

   ሀ. አንቀጽ አንድ ለ. አንቀጽ ሁለት

   ሐ. አንቀጽ ሶስት መ. አንቀጽ አራት

5. ‹‹ታዳሽ ኃይል›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

   ሀ. በጊዜ ሂደት የሚያልቅ ማለት ነው።

   ለ. የማያልቅ የሀይል ምንጭ ማለት ነው።

   ሐ. የማይተካ የሀይል ምንጭ ማለት ነው።

   መ. የሚተካ የሀይል ምንጭ ማለት ነው።

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ቀጥሎ ተዘውታሪ ስላለሆኑ ቃላት አገባባዊ ፍቺ ስለሚል ማስታወሻና መልመጃ ቀርቧል። የቀረበላችሁን ማስታወሻ ካነበባችሁ በኋላ መልመጃውን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

1. በእኛም ሀገር ቢሆን የአየር ብክለት መዘዝ በሀገራችን ህዝቦች ላይ <u>ብርቱ ክንዱን</u> በማሳረፍ ላይ ይገኛል።
2. በክልላችን ኦሮሚያም የአየር ብክለት ምን ያህል <u>አሳሳቢ</u> እንደሆነ በቅርብ ጊዜ ካጋጠሙት አደጋዎች መረዳት ይቻላል።

3. ከሰልን ለማብሰያም ሆነ ለማሞቂያ ከመጠቀም ተላቆ ንፁሕ የኃይል ምንጭ የመጠቀም ዕድል...
4. ይህንን አሳሳቢ ችግር ለመቅረፍም የክልላችን ህዝቦች ምን ምን ተግባራትን እየፈጸሙ እንዳሉ በዝርዝር እንመለከታለን።
5. በአርብቶ አደርነት የሚተዳደሩ የክልላችን የህብረተሰብ ክፍሎችም የዚህ ገፈት ቀማሽ ናቸው።
6. የተራቆቱና ተዳፋት የሆኑ መሬቶች ላይ እርከን በመስራት ውኃ እንዲያቁሩ ተደርገዋል።
7. ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በየአካባቢው ችግኞችን መትከል፣ ደኖችን መንከባከብ ልማዱ ሊያደርግ ይገባዋል።

## ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

| | |
|---|---|
| 1. አማራጭ | 6. ማሳያ |
| 2. መገደብ | 7. ማቆር |
| 3. ዕክል | 8. ተዳፋት |
| 4. መዛባት | 9. ቀውስ |
| 5. መበከል | 10. እርከን |

### ማስታወሻ

**ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት**

ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ውስጥ አዘውትረን የማንጠቀማቸው ቃላት ናቸው። የነዚህን ቃላት ትርጉም ለመረዳትም ቃላቱ የገቡበትን አረፍተነገሮችና የተነገሩበትን አውድ መመልከትና መረዳት ይገባል።

ለምሳሌ:- የአየር ብክለትን ለመከላከል ታዳሽ የሀይል አማራጭን መጠቀም ግዴታ ነው።

ጽዱ የኃይል ምንጮችን መጠቀም ያስፈልጋል።

ከላይ የተሰመረባቸው ቃላት ብዙ ጊዜ የማንጠቀማቸው ቃላት ናቸው። ስለዚህ እንዲህ አይነት ቃላት ትርጉማቸውን ለመለየት አገባባቸውን መመልከት አለብን።

## መልመጃ አራት

**ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተነገሮች ለተሰመረባቸው ተዘውታሪ ላልሆኑ ቃላት አውዳዊ ትርጉም ስጡ።**

1. ተማሪው ትምህርቱን ትቶ ወደ ቤቱ ከነፈ።
2. ሾፌሮቹ ከጫኑት ዕቃ ላይ ቀሽበው ሸጡ።
3. የባህል ልብስ ሰሪው ለብዙ ሰዎች ኩታ ሰርቶ ሰጣቸው።
4. መምህሩ ቀሽት ስለሆነ ተማሪዎች ብዙ ይወዱታል።
5. ልጅየው ሱስ ስላለበት ሁልጊዜ እናትየውን ገንዘብ ይቀፍላል።

### ክፍለጊዜ፡ ስድስት

**በምታውቋቸው ተዘውታሪ ባልሆኑ ቃላት ዓረፍተነገር መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

### ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ትምህርት አምስት- መጻፍ

ከዚህ በታች የመጻፍ ክህሎታችሁን የሚያዳብሩ የተለያዩ ተግባራት ቀርበዋል። ተግባራቱን በታዘዛችሁት መሰረት በአግባቡ አከናውኑ።

### ተግባር አራት

ከላይ በምንባቡ ውስጥ የተካተተውን ስዕል ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

### ተግባር አምስት

ስለአየር ንብረት የምታውቁትን ከምንባቡ ያገኛችሁትን አዳዲስ ሀሳቦች መነሻ አድርጋችሁ አንድ ማጠቃለያ አንቀጽ በጥንድ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ በማሳየት የተሰጣችሁን አስተያየት በማስተካከል ደግማችሁ ጻፉ።

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ክፍል ውስብስብ አረፍተነገሮችን ለይታችሁ እንድትጠቀሙ የሚረዳ መልመጃ ስለቀረበላችሁ በትኩረት ስሩ፡፡

### መልመጃ አምስት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ግሶች በመጠቀም ውስብስብ አረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡ (የግሶችን ቅርጽ መለዋወጥ ይቻላል)፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ገዛ | አነጠፈ | አነበበ | ሄደ |
| ተኮሰ | ቆረጠ | ሰበረ | አጠበ |
| አጸዳ | ሰረዘ | ጻፈ | ለበሰ |

ምሳሌ፡ (አጠበ፣ ተኮሰ፣ ለበሰ) ፈይሳ ልብሱን አጥቦ እና ተኩሶ ለበሰ፡፡

(አነጠፈ፣ተኛ) አለሚ አልጋዋን አንጥፋ ተኛች፡፡

# ምዕራፍ አስር

## ተውኔት

### የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- የሚደመጠውን ምንባብ አዳምጣችሁ ትንታኔ ትሰጣላችሁ፤
- የተውኔትን ጽንሰሀሳብ በተመለከተ ታብራራላችሁ፤
- የተውኔት አላባውያንን ትገልጻላችሁ፤
- በጽሁፍ ውስጥ የተለያዩ አያያዦችን ትጠቀማላችሁ፤
- ተመሳሳይ ቃለ ተውኔትን ትፈጥራላችሁ፤
- ሀሳባችሁን ለመግለጽ ዘይቤአዊ አገላለጾችን ትጠቀማላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ የትምህርት ይዘት መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ጭውውት መሰረት አድርገው ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥቄዎቹን በትዕዛዙ መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ፡፤

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ጭውውት ምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ አንድ ተውኔት በመድረክ ላይ ሲከወን ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ? ተመልክታችሁ የምታውቁ ከሆነ ምን ምን ሁኔታዎችን ተመለከታችሁ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ባዳመጣችሁት ጭውውት ውስጥ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?
2. የተቀረው የታሪኩ ክፍል እንዴት የሚጠናቀቅ ይመስላችኋል?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ያዳመጣችሁትን ጭውውት መሰረት አድርጋችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ያዳመጣችሁት ቃለተውኔት ውስጥ ያለው ታሪክ የተፈጸመው የት ነው?
2. ወሮ. ታሪኳ የተሸፋፈኑትን ነጠላ ገልጣ ያየችው ማነች ?
3. "በትልቅ ትንሹ ፈጣሪን ማማረር የለብዎትም" ያለው ማነው?
4. ወሮ. ታሪኳ፡ "አይ ቀጄልዬ! በጊዜ በሰበሰበኝ ምንኛ ደግ ነበር ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
5. የወሮ. ታሪኳ የጥርስ በሽታ ምን ደረጃ ላይ የሚገኝ ይመስላችኋል?
6. ያዳመጣችሁት ጭውውት ፍሬ ሀሳብ ምን ሆኖ አገኛችሁ? በአጭሩ ግለጹ።

### ተግባር አንድ

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ከጭውወቱ የወጡ ናቸው። በቡድን በመሆን በዓረፍተነገሮቹ ፍቺ ላይ ተወያዩ።ተወያይታችሁ ያገኛችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።**

1. "መቼም ከትናንትናው ዛሬ መለስ ብሎልኛል"?
2. "የሱ ቸርነት አያልቅም፣ አሁን ደግሞ ተንፈስ አደረገኝ።"

**ለ. ወሮ. ታሪኳ ከሌሎቹ ተዋንያን ጋር ያላቸውን ዝምድናና ቅርርብ ግለጹ።**

ክፍለጊዜ ሁለት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር ሁለት

ሀ. መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ያዳመጣችሁትን የጭውውት ታሪክ በቃላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩ።

ለ. ቀጥሎ የቀረቡት ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች ከጭውውቱ የተወሰዱ ናቸው። በምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮቹም ፍቺ ላይ በቡድን ተወያዩ። ተወያይታችሁ ያገኛችሁትንም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡

1. ኑሮ ኑሮ ከመሬት፣ ዞሮ ዞሮ ከቤት
2. እግዜር በትር ሲቆርጥ ቆላ አይወርድም
3. ልጅ ከጦረው ጥርስ የጦረው
4. ሆደ ባሻ
5. ሆደ ሰፊ
6. አንገታቸውን ደፍተው

ሐ. ከላይ የቀረቡትን የምሳሌያዊና የፈሊጣዊ አነጋገሮችን አጠቃቀም የሚያሳዩ አውዶችን በጥንድ ሆናችሁ በመፍጠር ለክፍል ተማሪዎች በቃል አሰሙ።

ክፍለጊዜ፡ ሶስት

## ተግባር ሶስት

ሀ. ያዳመጣችሁትን ጭውውት መሰረት አድርጋችሁ ወ/ሮ ታሪኳ ምን ይሆኑ ይሆን? የተቀረው የጭውውት ክፍል እንዴት የሚጠናቀቅ ይመስላችኋል?በቡድን ከተነጋገራችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።

ለ. ቀጥሎ በቀረቡት ርዕሶች መነሻ ከ3-5 ደቂቃ የሚረዝም አንድ ጭውውት ጻፉ። /በጭውውቱ ውስጥ ምሳሌዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን መጠቀማችሁን አስተውሉ/። የጻፋችሁትን ጭውውት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተለማመዱ።የተለማመዳችሁትን በክፍላችሁ ተማሪዎች ፊት ተውኑ።

### አማራጭ ርዕሶች

1. የጥበቃ ሰራተኛ፣ ተገልጋይና አለቃ
2. ርዕሰ መምህር፣ ወላጅና ተማሪ
3. ሽማግሌ፣ በዳይና ተበዳይ
4. እራሳችሁ የመረጣችሁት ርዕስ

ክፍለጊዜ፡ አራት

## መልመጃ ሁለት

ሠ. አንድ ቃለተውኔት ከማህበራዊ ድረገጾች ወይም ከመጻህፍት አንብቡ። ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች መነሻነትም ስላነበባችሁት ቃለተውኔት ለቡድን አባላቶቻችሁ ንገሩ። እናንተም ጓደኞቻችሁ ሲነግሯችሁ አዳምጡና ከእናንተ የሚለዩበትን ተናገሩ።

1. በቃለተውኔት ውስጥ የተሳተፉ ተዋንያን እነማን ናቸው?
2. በቃለተውኔቱ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ታሪኮች ምን ምን ናቸው?
3. በቃለተውኔቱ ውስጥ ያሉ ታሪኮች የትና መቼ ተፈጸሙ?
4. የቃለ ተውኔቱ ጭብጥ ምንድን ነው?
5. ጭውውቱን እያዝናና ከማስተማርአንጻር እንዴት ትገመግማላችሁ?

ክፍለጊዜ፡ አምስት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት፣ እያነበባችሁና አንብባችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ የምትመልሷቸው የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን በትዕዛዛቸው መሰረት በንቃት መልሱ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ስለ ቃለተውኔት ምን ታውቃላችሁ?
ለ. ስዕሉን ተመልክታችሁ ስለ ተውኔት ምን ማለት ትችላላችሁ?



## ቅድሚያ ለትምህርት

አዛውንት፡ "አንድ ጉዳይ አለኝ እፈልግዎታለሁ" ካልከኝ ቆየህ አይደል ልጄ?

ወጣት፡ "አዎ ቆየት ብሏል፤ እስካሁን ከቆየሁት አይበልጥም፤ እታገሳቸዋለሁ፤ ፋታ የማይሰጥ ጉዳይ አጋጥምዎ ይሆናል" ብዬ ነው።"

**አዛውንት፡** "ለመሆኑ የፈለከኝ በደህና ነው?

**ወጣት፡** በደህና ነው፤ እንዲያው ለምን አንድ ውሃ አጣጪዬን አልፈልግም የሚል ሀሳብ ከታየኝ ሰንበት ብሏል።

**አዛውንት፡** "ነገሩ ጥሩ ነው።በየትኛዋ ፊት ላይ ነው ቀልብህ የወደቀው?"

**ወጣት፡** "እዚህ የጎረቤታችን ልጅ፣ አያንቱ የምትባለዋ ልጃገረድ ውለው ሳያድሩ ይጠይቁልኝ፤ እሺም ያስብሉልኝ።"

**አዛውንት፡** "እሺ ላሰኛት እሞክራለሁ።"

**ወጣት፡** "ደህና ይዋሉ፤ መልሱን ቶሎ ብለው ያድርሱኝ"

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አዛውንቱ ይሳካላቸው ይሆን?
2. ወጣቱ ትዳር የፈለገው ለምንድን ነው?

**አዛውንቱ፡** "የእርስዎን ልጅ አቶ ቶላ ዋቅጋሪ ልጅዎን ለልጄ ይላሉ።"

**የአያንቱ እናት፡** አንገታቸውን ደፍተው አይናቸውን መሬት ላይ ተክለው ዝም ይላሉ።

**አዛውንቱ፡** "ዝምድናዬን ላጠንክር ብለው ነው እንጂ እርስዎን ለማስከፋት ብለው አይደለም"

**አዛውንቱ፡** (ረጋ ደፈር በማለት መልስ ይሰጣሉ)"የእርስዎም ልጅ እየተማረች ስለሆነ፣ የአቶ ቶላ ዋቅጋሪ ልጅም እየተማረ ስለሆነ በዚያ ላይ ሁለቱም በትምህርታቸው እሳት የላሱ እሳት የጎረሱ ስለሆኑ ሁለቱም ተረዳድተው ጥሩ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ በማለት ነው። በዚያ ላይ ... የአቶ ቶላ ዋቅጋሪ ልጅ ልበ ሙሉና በትምህርቱም ምስጉን ልጅ መሆኑን መቼም አይጠፋሽም"

**የአያንቱ እናት፡** "እሺ. የኔ አባት የልጄን ውሳኔ ማክበር ስላለብኝ እሷን ላማክራት፣ ከሶስት ቀን በኋላ ብቅ ብለው ይጠይቁኝ"

**አዛውንት፡** "እዚህ ቤት እንዴት አደራችሁ? ይኸው በቀጠሯችን መሰረት ተመልሰን መጣን።"

**አዛውንት፡** "የአያንቱ እናት የደረሳችሁበትን ውሳኔ አሳውቁን"

**የአያንቱ እናት፡** "አይ ልጄ በጄ አልልም አለች፣መማር እፈልጋለሁ ብላ እያለቀሰች ነገረችኝ።"

**አዛውንት፡** በጣም ጥሩ ነው። እኔም ብሆን ይህ ጉዳይ አሁን እየገባኝ መጥቷል። ስንትና ስንት ልጆቻችንን ከትምህርት እያደናቀፍን ያለጊዜያቸው ወደ ትዳር እንዲገቡ ስንፈርድባቸው ነበር። አሁን ግን ይበቃል።

**የአያንቱ እናት፡** ልክ ብለዋል። ለልጆቻችን ዘብ ልንቆም ይገባል። ያለእድሜና ከትምህርት በፊት ጋብቻ ይብቃ እንበል።

(ምንጭ፡ ከአማርኛ የተማሪ መጽሀፍ 9ኛ ክፍል 2004 ዓ.ም 1ኛ ዕትም ተሻሽሎና እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ።)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።**

1. አያንቱና ወጣቱ ምን አይነት ተማሪ ናቸው?
2. ቃለተውኔቱ ውስጥ የቀረቡት አዛውንቱ፣ ወጣቱ፣ የአያንቱ እናት ምን ይባላሉ?
3. ወጣቱ ሚስት ለማግባት የፈለገው ለምንድን ነው?

**ለ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. በቃለተውኔቱ ውስጥ ለታሪኩ መፈጠር ሰበብ የሆነው ማነው?

   ሀ. አዛውንቱ　　　　ሐ. አያንቱ

   ለ. ወጣቱ　　　　መ. የአያንቱ እናት

2. አያንቱ ትምህርቴን መማር እፈልጋለሁ፤ በጂ አልልም ስትል ምን ማለቷ ነው?

   ሀ. ፈቃደኛ አይደለሁም።　　　　ሐ. ልማከር ማለቷ ነው።

   ለ. መወሰን አልቻልኩም።　　　　መ. ምንም ማለት አልፈልግም።

3. የአያንቱ እናት ልጃቸው ለትዳር ሲጠየቁ የገቡበት ስሜት ምን አይነት ነው?

   ሀ. የማይታወቅ።　　　　ሐ. ደስተኛ

   ለ. ቁጣና መከፋት　　　　መ. ሀዘን

### ክፍለጊዜ፡ ስድስት

**ሐ. ምሳሌውን መሰረት አድርጋችሁ የተውኔቱን ዋና ዋና ድርጊቶች ቅደምተከተላቸውን ጠብቃችሁ ጻፉ።**

ድርጊት አንድ፣ ወጣቱ ሊያገባት የፈለጋትን ልጃገረድ ቤተሰቦች አዛውንቱ እንዲለምንለት ተማጸነ።

ድርጊት ሁለት፡________________________________

ድርጊት ሶስት፡________________________________

ድርጊት አራት፡________________________________

ድርጊት አምስት፡________________________________

**መ. ከዚህ በታች ከተውኔቱ የተወሰዱ የተዋንያኑ ምልልሶች ተደባልቀው ቀርበዋል። ቃለተውኔቱን ደግማችሁ በማንበብ ምልልሶቹ የማን እንደሆኑ ለይታችሁ ጻፉ።**

1. "ልጅዎን ለልጄ ይላሉ።"
2. "ነገሩ ጥሩ ነው።"
3. "ሁለቱም ተረዳድተው ጥሩ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ በማለት ነው"
4. "ከሶስት ቀን በኋላ ብቅ ብለው ይጠይቁኝ"
5. "ደህና ይዋሉ፤ መልሱን ቶሎ ብለው ያድርሱኝ"

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ከዚህ በታች ለቃላት ተመሳሳይና አውዳዊ ትርጉም ስጡ የሚል መልመጃና ዘይቤያዊ አገላለጾችን የተመለከተ ማስታወሻም ቀርቧል።ማስታወሻውን ካነባባችሁ በኋላ መልመጃዎቹን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ከምንባቡ ውስጥ ፍቺ የሚሆኗቸውን ቃላት ፈልጋችሁ ጻፉ።**

| | |
|---|---|
| 1. ተጋግዘው | 6. አልፈልግም |
| 2. መጠበቅ | 7. ውለው ሳያድሩ |
| 3. መሟገት | 8. ጫን አድርጌ |
| 4. መስተንጎል | 9. ማገዝ |
| 5. ተጎድታ | 10. ቁምስቅል |

**ለ. በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ትርጉም ስጡ።**

1. እታገሳቸዋለሁ፡ፋታ የማይሰጥ ጉዳይ አጋጥሞዎ ይሆናል።
2. እንዲያው ብቸኝነት ሲከብደኝ ጊዜ ለምን አንድ ውሃ አጣጪዬን አልፈልግም የሚል ሀሳብ ከታየኝ ሰንበት ብሏል።።
3. አንገታቸውን ደፍተው ዝም ብለው ብቻቸውን የሆኑ በሚመስል ካሳባቸው ጋር መሟገት ስለጀመሩ አዛውንቱ ይቀጥላሉ።
4. የአያንቱ እናት እሺ ይበሉኝና አሳርጌ ልሂድ፣ ቀጠሮ ይስጡኝ።
5. ለልጁ ነግሬያት አላስጨንቃትም ብለው በውሳኔያቸውም ይጸናሉ፡

ሐ. በምንባቡ ውስጥ የሚገኙትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከለያችሁ በኋላ ፍቺ ስጡ።

ለምሳሌ፡ቀልብህ የወደቀበት፡ የወደድከው፣ የከጀለው

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

**ማስታወሻ**

**ዘይቤያዊ አገላለጽ**

ዘይቤዊ አገላለጽ አንድን በንግግር ወይም በጽሁፍ የሚቀርብን ሀሳብ አድምቆና አግዝፎ ለማቅረብ ሲባል ቃላት ከተለምዷዊው ወይም ዘወትራዊው ከሆነው አጠቃቀማቸው ለየት ያለ አጠቃቀምን ስንከተል ነው። ይህም ማለት አንድን ሀሳብ አጉልቶና አድምቆ ተመልካቹም ሆነ ሰሚው በቀላሉ መረዳት እንዲችል ያግዘዋል። ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ የዘይቤ አይነቶች አሉ።

**አነጻጻሪ ዘይቤ፡** ሁለት በአፈጣጠራቸው የማይመሳሰሉና የተለያዩ ነገሮችን በመውሰድ በማነጻጸሪያ ቃላት(እንደ፣ ያህል፣ ይመስላል ወዘተ) እየተጠቀመ የሚያነጻጽርና የሚያወዳድር የዘይቤ አይነት ነው።

**ለዋጭ ዘይቤ፡** ይህ ዘይቤ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን ወስዶ የአንዱን ባህርይ ለሌላው በመስጠት የሚያቀርብ የዘይቤ አይነት ነው።

ምሳሌ፡- አራርሳ አሳማ ነው።

- እጁ በረዶ ሆነ።

**ሰውኛ ዘይቤ፡** የሰውን ልዩ ልዩ ባህርያት፣ ድርጊትና ችሎታ ሰው ላልሆኑ ነገሮች በመስጠት የሚፈጠር ዘይቤ ነው።

ምሳሌ፡ - "ለሰው ሞት አነሰው "አለች ቀበሮ!

-ጀምበር ፊት ነሳቻት።

**መ. የሚከተሉትን አገላለጾች አነጻጻሪ፣ ለዋጭና ሰውኛ ዘይቤ በማለት ለይታችሁ ጻፉ።**

1. ሰውነቷ እሳት ሆነ።
2. ተዋጊ በሬ ይመስል እየተንደረደረ መጣ።
3. ቀኑ ሲያለቅስ ዋለ።
4. እህቴ እንደእርግብ የዋህ ነች።
5. ተማሪዋ ቆቅ ናት።
6. "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" አለች አህያ።
7. እንጀራዋ የውሻ ምላስ ታክላለች።
8. ሴትየዋ ኤሊ ናት።

**ሠ. አነጻጻሪ፣ ለዋጭና ሰውኛ ዘይቤን ተጠቅማችሁ ሁለት ሁለት ዓረፍተነገር መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

ቀጥሎ እንድትጽፉ የሚጋብዟችሁ የተለያዩ የመጻፍ ተግባራት ቀርበዋል። ተግባራቱ በሚያዟችሁ መሰረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

### ተግባር ሶስት

ሀ. በማዳመጥ ትምህርት ወቅት ያዳመጣችሁትን ጭውውት መልዕክቱን በማስታወስ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ በራሳችሁ አገላለጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

### ተግባር አራት

ለ. የራሳችሁን አንድ አጭር ቃለ ተውኔት በቡድን ጽፋችሁ በመለማመድ ክፍል ውስጥ ተውኑ።

ክፍለጊዜ፡ አስር

### ተግባር አምስት

ሀ. ከላይ የቀረበውን ቃለተውኔት ደግማችሁ በማንበብ ወይም በማስታወስ የቃለ ተውኔቱን ጭብጥ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ለ. ከላይ ባነበባችሁት ቃለተውኔት ውስጥ ያሉትን ተዋንያንን ወክሉ። ከዚያም ተዋንያኑ ወክለው የተጫወቱትን ምልልስ በራሳችሁ አገላላጽ ጻፉ።መድረክ ላይ ለማቅረብም ተለማማዱ። የተለማመዳችሁትን ቃለተውኔትም ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን ለክፍሉ ተማሪዎች አቅርቡ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

### ተግባር ስድስት

ስለተውኔት ምንነትና አላባውያን የተመለከተ ማስታወሻ ከዚህ በታች ቀርቦላችኋል። ማስታወሻውን አንብባችሁ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን በአንቀጽ አደራጅታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

### ማስታወሻ

**የተውኔት ምንነትና አላባውያን**

ተውኔት የስነጽሁፍ ዘሮች በአያሌው የተለየ ነው። ተውኔት ድርጊትን መድረክ ላይ ስለሚያቀርብ የተመልካቹን ትኩረት የመሳብ ከፍተኛ ሀይል አለው፤ መድረኩ በመብራት የደመቀ፣ አዳራሹ በጨለማ የተዋጠ፣ ሁሉም ጸጥ ረጭ ያለ፣ በዙሪያው ምንም ድምጽ የማይሰማበት ነው።

ተውኔት ገጸባህርያቱ ሰዋዊ ድርጊቶች ሲፈጽሙ የሚታዩበትና የተመልካችንም ተሳትፎ የሚጠይቅ ስለሆነ ድርጊታዊነት ይታይበታል። በተዋንያኑ ተመስለው የሚቀርቡት ገጸባህርያት ከተመልካቹ ጋራ ፊት ለፊት በመተያየት ማንነታቸውን ያሳያሉ። በተቀረጹበት ሁኔታና በገቡበት ሁነት ውስጥ ሆነው ሀሳባቸውን ለተመልካቹ ይገልጻሉ። ደስታ ሀዘናቸውን ያሰማሉ። ተመልካቹም የሀዘናቸው ተካፋይ የደስታቸው ተጋሪ ይሆናል።

ተውኔት በአጠቃላይ ህይወትን ከበፊቱ ይበልጥ እንድናጤን የማድረግ አቅም ያለው ኪነጥበብ ነው። ይህን ሁሉ ሲያደርግ እንደ ረጅምና አጭር ልቦለድ ስለገጸባህርያቱ ድርጊት አያወራም፤ አይተርትም። በገሀድ እንቅስቃሴ ያሳያል እንጂ። ገጸባህርያቱን በአይነህሊና ሳይሆኑ በእውኑ አይናችን እንድናያቸው በእዝነህሊና ሳይሆን በእውኑ ጆሯችን እንድሰማቸው ያደርጋል።ባጠቃላይ ከላይ በዝርዝር የቀረበው የተውኔት አላባውያን ተዋንያን፣ ታሪክ፣ መቼት፣ ግጭትና የመሳሰሉት መሆናቸውን ያስረዳናል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ቀጥሎ አያያዥ ቃላትን ተጠቅሞ ዓረፍተነገሮችን ማሟላትና መመስረት የሚሉ መልመጃዎች ቀርበዋል።መልመጃውን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

### የተለያዩ አያያዥ ቃላትን በጽሁፍ ውስጥ መጠቀም

**መልመጃ አራት**

ሀ. ከዚህ በታች የተለያዩ አያያዥ ቃላት ቀርበዋል። በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች ተገቢ የሆኑ አያያዥ ቃላት በመምረጥ አረፍተነገሮቹን አሟሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ይሁን እንጂ | በመሆኑም | ቢሆንም |
| ነገር ግን | እንጂ | ደግሞ |
| ስለዚህ | ግን | እና |

1. መምህሩ ይመጣል _________ ሊቆይ ይችላል።
2. ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ጠንክረው አጥንተዋል፤አነስተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች _________ ምንም አላጠኑም።
3. ልቦለድ ከማህበረሰቡ ባህልና እሴት ከታየና ከተሰማ ነገር ወይም ካልተፈጸመ _________ በሰው ልጅ ገጠመኝ ሊሆን የሚችል ታሪክን ይጽፋል።
4. ገበሬው ከፍተኛ ምርት አስገብቷል።_________ማበረታቻ በከፍተኛ ደረጃ ሊሰጠው ይገባዋል።
5. መምህር ተማሪው ሲሳሳት ተገቢውን እገዛ ያደርጋል_________ ማንቋሸሽ አይገባውም።
6. ወንድሞቹ_________ጓደኞቹ አንድ ላይ ሆነው የንግድ ስራ ጀመሩ።
7. መኪናው በፍጥነት የሚሄድ _________ በተፈለገው ሰዓት _________ አይደርስም መድረስ አልቻለም።

ለ. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ አምስት አምስት አያያዦችን ምረጡ። በመቀጠልም የመረጣችኋቸው አያያዦቹ ለምን ተግባር እንደሚውሉ ለዩና ሁለት ሁለት አረፍተነገሮችን መስርቱባቸው።